የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለሴቶች

# ከዕንቁ የከበረች

## የልባም ሴት ባሕርያት
## ምሳሌ 31


የመጀመሪያው እትም 1992 ዓ.ም.
ሁለተኛውና የተሻሻለው እትም 1993 ዓ.ም.

ኤስ.አይ.ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በቡድን ሆነው የሠሩ ሰዎች ጥረት ውጤት ነው። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሰዎች መጽሐፉን በመጻፍ፣ ረቂቅ ጽሑፉን በማረም እና በመተርጎም ተባብረዋል።

ራሄል ፒንዳ

ሱዛና ኖክ

ሶፊያ ሙሉ

ራሄል አሸብር

ጀረልዲን ኮተረል

መሓሪ ታደሰ

ዘነበ ገብረሐና

ዓለማየሁ ማሞ

# ማውጫ

ገጽ


መግቢያና ለመሪዎች ዕርዳታ ........................................................1
ምዕራፍ 1 ከዕንቁ የተመረጠች........................................................5
ምዕራፍ 2 በእግዚአብሔር ጸጋ ትኖራለች ......................................14
ምዕራፍ 3 እምነት ይጣልባታል.......................................................23
ምዕራፍ 4 ትጉሕ ሠራተኛ ናት.......................................................30
ምዕራፍ 5 በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች ........................................39
ምዕራፍ 6 አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች ..........................................47
ምዕራፍ 7 ሌሎችን በጥበብ ታስተምራለች.....................................55
ምዕራፍ 8 ባሏን እንደሚገባ ትንከባከባለች ...................................65
ምዕራፍ 9 እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች .........................................76
ምዕራፍ 10 እግዚአብሔርን ትፈራለች.............................................83
/ፈሪሀ እግዚአብሔር አላት/

# መግቢያና ለመሪዎች ዕርዳታ

## በሴቶች መካከል ያለ ልዩ ግንኙነት

እግዚአብሔር ሴቶችን ሲፈጥር ከወንዶች በተለየ መንገድ ነው የፈጠራቸው። ልዩነቶቹም በሰውነት ቅርጽ አቀማመጥ ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብና ስሜትም ጭምር ነው። በተጨማሪም ሴቶች በአጠቃላይ ተግባራቸውና ኃላፊነታቸው ከወንዶች ይለያሉ። ችግሮቻቸውና ትኩረታቸውም እንዲሁ ከወንዶች የተለየ ነው። በእነዚህም ልዩነቶች ምክንያት ሴቶች ከሴቶች ጋር በሚገርም ሁኔታ (ከወንዶች ጋር ሊኖራቸው በማይችለው መልኩ) ይጎዳኛሉ።

ሴቶች ለዕርዳታ ለማጽናናት ወይም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት ሲሰባሰቡ ለየት ያለ ነገር ይከናወናል። ችግራቸውን፥ ጉዳዮቻቸውን፥ ደስታቸውንና ድላቸውን እርስ በርሳቸው ሲወያዩ በመግባባትና ጎዶሎአቸውን በሚሞላ መልኩ ይረዳዳሉ። ስሜታቸውን፥ ችግራቸውን፥ የኑሮ ውጣ ውረዳቸውንና አሳባቸውን በግልጽ የሚነጋገሩት እርስ በርሳቸው ስለሚግባቡ ነው። ስለሚጋፈጧቸው ነገሮች የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን አንድ ላይ ሲያጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎችን ከሕይወታቸው ጋር እንዴት ማዛመድ እንዳለባቸው ሊረዳዱ ይችላሉ። በዚህ ዓይነቱ ቡድን ሴቶች በክርስትና ሕይወታቸው እንዲያድጉ እርስ በርስ ሊረዳዱ ይችላሉ።

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ሴቶች በግል ሳይሆን በቡድን ሆነው እንዲያጠኑት ነው። መጽሐፉ የተዘጋጀው ሴቶች በኅብረት ሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አብረው እግዚአብሔርን ስለምትፈራ ሴት ባሕርይ እንዲወያዩ ነው። ሴቶች ለአንዳንድ ጥያቄዎቻቸው መልስና ምሪትን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማግኘት የተረዱትን ከራሳቸው ሕይወት ጋር እንዲያዛምዱ ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረትን መምራት

ይህንን መጽሐፍ የሚያጠኑ ሴቶችን የምትመሪ ከሆነ ጌታ እንዲረዳሽ በእግዚአብሔር መታመን ጠቃሚ ነው። እግዚአብሔር ጥበብና ምሪት እንዲሰጥሽ መጸለይሽን እርግጠኛ ሁኚ። ጥበብን ከጠየቅነው እግዚአብሔር እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል (ያዕ. 1፡5ን አንብቢ)።

እንደምሪትሽ ያለሽን ሚና መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪ መሆን ከአስተማሪነት የተለየ ነው። ሌሎችን ሴቶች «ማስተማር» አያስፈልግሽም። የአንቺ ሥራ በየምዕራፉ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ እንድትወያዩ ኅብረቱን መምራት ነው። ይህን እንዴት ነው የምታደርጊው? እንዴት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረትን

እንደምትመሪና ይህንን መጽሐፍ እንዴት መጠቀም እንዳለብሽ የሚያስረዱ መመሪያዎች ቀጥለው ቀርበዋል።

## ለመሪው መመሪያዎች

1. ከእያንዳንዱ ኅብረት ጋር ከመገናኘትሽ በፊት የምታስተምሪውን ክፍል በሚገባ አጥኚ። የምታጠኚው እንዲገባሽና እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጠይቂ። የተረዳሽውን ከራስሽ ሕይወት ጋር አዛምጂ።
2. ስትሰበሰቡ ሁሉም ሴቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ ሞክሪ። ሁልጊዜ አንቺ ብቻ አታስተምሪ፤ አትናገሪም፤ ሌሎች ሴቶች አሳባቸውንና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አበረታቻቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አንዳችን ከአንዳችን መማራችን በጣም ጠቃሚ ነው።
3. በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ እያንዳንዳቸው መልስ የሚሰጡበት ጥያቄ አለ። ለጥያቄዎቹ አንቺ ብቻ መልስ አትስጭ። በዚህ ፈንታ እያንዳንዳቸው የጻፉትን መልስ እንዲናገሩ ጠይቂያቸው። መልስ ለመስጠት ፈቃደኞች ካልሆኑ የአንዷን ሴት ስም በመጥራት ምን እንደመለሰች ልትጠይቂ ትችያለሽ።
4. ሴትየዋም መልስ ስትሰጥ መልሷን በጥሩ መንፈስ ተቀበዪ። ለምሳሌ «ጌታ ይባርክሽ! ጥሩ መልስ ነው» በያት። በጥሩ መንፈስ ምላሽ ከሰጠሻት ሌሎች ሴቶች መልስ እንዲመልሱ ያበረታታቻዋል። የሚሰጡት መልስ ትክክል ቢሆንም ባይሆንም ችግር እንደሌለው አስታውቂያቸው። ጠቃሚው ነገር ስለ ሁኔታዎች በመነጋገር እርስ በርስ መማማራችሁ ነው።
5. በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት ብዙ ጥያቄዎች ከአንድ በላይ መልስ ሊኖራቸው ይችላል። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ከአንድ ሴት ብቻ ሳይሆን ከብዙዎች መስማቱ ጥሩ ነው። አንድ ሴት ከመለሰችና አንቺም ከአበረታታሻት በኋላ አንድ ሁለት ሴቶችን መልስ እንዲሰጡ ጠይቂያቸው።
6. አንዳንዴ ምናልባት አንዷ ሴት ከጥያቄው የራቀ መልስ ልትሰጥ ትችል ይሆናል። እንዳታሳፍሪያት ተጠንቀቂ። አሳቧን ስላካፈለች አመስግኛት። ቀጥለሽም የተለየ አሳብ ያለው ሰው እንዳለ ጠይቂ። ሌላኛዋ ሴት ትክክለኛ መልስ ካልሰጠች ቀጥተኛ መልስ የሚሰጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እንድትመለከት አድርጊ። ምክንያቱም የኅብረቱ አባላት ትክክለኛውን መልስ መረዳት ይኖርባቸዋል።

7. በቡድንሽ ውስጥ ብዙም የማትናገር ዝምተኛ ሴት ካለች ከቡድኑ አባላት ጋር እንድትለማመድ ጊዜ ስጪያት።

8. በቡድንሽ ውስጥ ከሚገባው በላይ በማውራት ሌሎቹን ሴቶች አላናግር ያለች ሴት ካለች ቀስ ብለሽ አቋርጫትና እንዲህ በያት «እስቴር ስለሰጠሽው አስተያየት አመሰግናለሁ፤ ስለዚህ ጉዳይ ሌሎች ሰዎች ያላቸውን አስተያየት ደግሞ እንስማ። እስኪ ጽዮን ስለዚህ ጉዳይ ምን ትያለሽ?»

9. ውይይቱን በምዕራፉ ርእስ ላይ የተወሰነ ለማድረግ ሞክሪ። ውይይቱ ከርእስ ከወጣ ሴቶቹን ቀስ ብለሽ በምዕራፉ ላይ ወዳለው ርእስ መልሺያቸው።

10. ለጥያቄዎች ሁሉ መልስ መስጠት አልችል ይሆናል ብለሽ አትጨነቂ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ለመምራት የግድ የሁሉንም ጥያቄ መልስ ማወቅ የለብሽም። አንድ ሰው ጥያቄ ቢጠይቅና አንቺ መልሱን ካላወቅሺው በቡድኑ ካሉት አባላት መመለስ የሚችል ሰው እንዳለ ጠይቂ። በኋላ ከቤተክርስቲያን ሽማግሌ ወይንም ከሌላ ሰው በመጠየቅ መልሱን ማግኘት ትችያለሽ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍን ለመጠቀም የሚያገለግል መመሪያ

1. ይህንን መጽሐፍ በኅብረት ለማጥናት ቀጣይ የሆነ ሳምንታዊ ጊዜ መድቢ። ለእያንዳንዱ የጥናት ጊዜ ከአንድ ተኩል እስከ ሁለት ሰዓት ያህል ለመመደብ አቅጂ። ይህ መጽሐፍ ዐሥር ምዕራፎች አሉት። ይሁን እንጂ ጥቂቶቹን ምዕራፎች በአንድ ሳምንት ለመጨረስ ስለማይቻል ከዐሥር ጊዜ በላይ መገናኘት ይኖርባችኋል።

2. እያንዳንዷ ሴት ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ መጽሐፍ በግል መግዛት ይኖርባታል። ምናልባት ለአንዳንዶቹ ሊያስቸግር ከቻለ ጥናቱ የሚጀምረው ከተወሰነ ሳምንት በኋላ መሆኑን በማስገንዘብ በየሳምንቱ አንድ አንድ ብር በማጠራቀም መጽሐፉን ለመግዛት የሚያቅዱበት ጊዜ እንዲኖራቸው አድርጊ። እያንዳንዷ ሴት የራሷ የሆነ መጽሐፍ ቢኖራት ጠቀሜታው የላቀ ነው።

3. በጥናቱ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች በየሳምንቱ የሚሠራ የቤት ሥራ እንዳለ ግልጽ አድርጊ። በኅብረት ተሰብስበው ምዕራፉን ከመወያየታቸው በፊት ሁሉም በግላቸው ማንበብና ለጥያቄዎች መልስ መጻፍ ይኖርባቸዋል። ይህም ለሴትየዋ ጠቀሜታ

አለው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብና ያነበቡትን ከሕይወታቸው ጋር ለማዛመድ ስለሚጠቅም ነው። በዚህ የጥናት መጽሐፍ በደንብ መጠቀም የሚችሉት ጊዜ ሰጥተው የየሳምንቱን የቤት ሥራ ሲሠሩ ነው።

4. የቤት ሥራቸውን ተግተው እንዲሠሩ በየሳምንቱ ማስታወስ ይኖርብሻል። በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በግላቸው እንዲያነቡና እንዲያጠኑ ከማበረታታት አትቆጠቢ። ጊዜ ለማይኖራቸው ሴቶች ግን በየቀኑ ለዐሥራ አምስት ደቂቃ ምዕራፉን እያነበቡ ጥያቄ እንዲሠሩ አሳስቢያቸው። አብዛኛውን ጊዜ ሁሉንም ምዕራፍ በአንዴ ከማጥናት ጥቂት ደቂቃዎች በየቀኑ ማጥናት ቀለል ያለ ይሆናል።

5. ለእያንዳንዱ የጥናት ጊዜ ሀያ ደቂቃ ያህል በማስቀረት በምንባቡ ውስጥ የተማሩትን እንዲወያዩና የጸሎት ርእስ እንዲለዋወጡ አድርጊ። አብዛኛውን ጊዜ ወደ ትንሽ ኅብረት በመከፋፈል ይህንን ማድረጉ ጥሩ ነው። ምክንያቱም ሁሉም እንዲናገሩ ዕድል ስለሚሰጣቸው ነው። በትልቅ ኅብረት ግን በቂ ጊዜ ላይኖር ይችል ይሆናል። ምናልባትም በትልቅ ኅብረት መካከል አሳባቸውን ለማቅረብ ይርበተበቱና ይጨነቁ ይሆናል።

ኅብረቱን ከሁለት እስከ ሦስት ባልበለጡ ሴቶች ከፋፍዪ። ቀጥለሽም የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ንገሪያቸው።

ሀ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ የእኔ ምላሽ የሚል ክፍል አለ። ይህ ክፍል በእዚያ ምዕራፍ ውስጥ ምን እንዳጠኑ እንዲያስቡና ስላጠኑት እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡና እንዲጸልዩ ይረዳቸዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ የጻፉትን በትንሹ ኅብረታቸው ውስጥ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩበት። ይህ በክርስትና ዕድገታቸው ውስጥ አንድዋ ለአንድዋ ትጸልይ ዘንድና አንዱ ሌላዋን ታጽናናት ዘንድ ነው።

ለ. እርስ በርሳቸው የጸሎት ርእስ እንዲለዋወጡ አድርጊ። እያንዳንዳቸውም በተቀበሉት የጸሎት ርእስ ላይ ሳምንቱን ሙሉ እንዲጸልዩ አበረታቺ።

6. ምሪትና ማስተዋልን ከእግዚአብሔር እንድትቀበዪ በየሳምንቱ መጸለይ እንዳለብሽ አስታውሺ። እንዲሁም በኅብረቱ ውስጥ ለሚገኙ እኅቶች በሙሉ ጸልዪ። እግዚአብሔር ልባቸውንና ሕይወታቸውን እንዲለውጥ ጠይቂው፤ በዚህም እያንዳንዱ አባል በእውነተኛ ፍቅር እርስ በርሳቸው እንዲቀባበሉ ጸልዪ።

እግዚአብሔር ይባርክሽ ያበርታሽም።

## ምዕራፍ 1

# ከዕንቁ የተመረጠች

**መዝሙር 138(139)፥ 14ን በልብሽ አጥኚ።**

**«ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ግሩምና ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።»**

## የዕንቁ ዋጋ

*የለበሰው ጥቁር ስለሆነ ድቅድቅ ባለው ጨለማ እየተራመደ ወደ ቤት ሲያመራ ለማየት አዳጋች ነበር። ባለቤቶቹ በአከባቢው እንደሌሉ ያውቃል። ጠጋ ብሎ የመኝታ ቤቱን መስኮት በጥንቃቄ ከፈተውና ተንጠላጥሎ ወደ ውስጥ ገባ። የፈለገውን እስኪያገኝ ድረስ የጠረጴዛ መሳቢያዎቹን አተረማመሳቸው። የኋላ ኋላ በአልማዝና በውድ ዕንቁዎች የታጨቀውን ትንሽ ከረጢት አገኘ። ፖሊስ ቢይዘው ለረጅም ዓመታት በወህኒ እንደሚማቅቅ ያውቃል። ነገር ግን «ይህን የመሰለ ዕንቁ ካገኘሁ የፈለገው ይምጣ እንጂ . . .» ብሎ አሰበ። ከረጢቷን አጣጥፎ ጃኬቱ ውስጥ ከተታትና በገባበት መስኮት ዘሎ በመውጣት በጨለማው ውስጥ ተፈተለከ።*

ለምንድን ነው የዕንቁዎች ዋጋ እንዲህ የተወደደው? ምናልባት በጣም ስለሚያምሩና እንደ ልብ ስለማይገኙ ይሆናል። በዓለም ዙሪያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ዕንቁዎችን ይፈልጋሉ። የጣት ቀለበት፥ የጆሮ ጌጥ፥ የአንገት ጌጥ አሠርተው ያደርጓቸዋል። እንዲሁም በነገሥታትና ንግሥቶች ዘውድ ላይ ያስቀምጧቸዋል። በአንዳንድ አገሮች ትንንሽ ዕንቁዎችን በግምባራቸው ላይ አልያም በዕምብርታቸው ላይ በማጣበቅ ያጌጡባቸዋል።

ዕንቁዎች በዓለም ዙሪያ ተፈላጊነት ስላላቸው በየአገሩ ዕንቁዎችን ሲያሳድዱ የሚኖሩ ሰዎች አሉ። ዕንቁዎችን ማግኘት ቀላል ሥራ አይደለም። ዛሬ በደቡብ አፍሪካ የማዕድን ጉድጓድ ቆፋሪዎች አንድ መጠነኛ ቀለበት ለመሥራት የሚያስችል ዕንቁ ለማግኘት 226,800 ኪሎ የሚመዝን ዓለትና ምናምን ዝቀው ማውጣት ይኖርባቸዋል።

በዓለማችን ዕንቁዎች በጣም ተፈላጊ ናቸው። የብሉይ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን እንዲሁ በጣም ተፈላጊ ነበሩ በብሉይ ኪዳን ውስጥ «ውድ» ወይም «ዋጋው የላቀ» የሚለው ቃል ከ37 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። ከእነዚህ መሃል 22ቱ የተጠቀሱት ከዕንቁ ጋር ተያይዘው ነው።

የመጽሐፈ ምሳሌ 31ኛ ምዕራፍ «ከዕንቁ ስለምትበልጥ ሴት» ይነግረናል። እንደዚች ሴት መሆን የማይፈልግ ማንም የለም። ምሳሌ 31 የዚህችን ልባም ሴት ባሕርያትና መልካም ምሳሌ ሥዕል ይሰጠናል። በዚህ የጥናት መጽሐፍ እነዚህን መልካም ባሕርያትና ምግባሮች እየመረመርን በራሳችን ሕይወት እንዴት እንደምናዳብረው እናያለን።

## ታሪካዊ ዳራውን መመልከት፤ ለምንና እንዴት እንደ ተጻፈ መረዳት

ምሳሌ 31 ለምንና እንዴት እንደ ተጻፈ ለማየት ትንሽ ጊዜ መውሰድ ያስፈልጋል። የምዕራፉ የመጀመሪያ ቁጥር ስለ ጸሐፊው ይናገራል።

*«እናቱ እርሱን ያስተማረችበት የንጉሥ ልሙኤል ቃል።»*

ይላል። ይህንን ቁጥር ስንመለከት ምዕራፉ የተጻፈው በንጉሥ ልሙኤል እንደሆነ እናያለን። እናቱ ስለሴቶች ያስተማረችውን እውነት አስፍሯል። ምንም እንኳ ስለ ንጉሥ ልሙኤል ጠለቅ ያለ መረጃ ባይኖረንም እናቱ ግን በልጇ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረችበት ግልጽ ነው። የንጉሥ ልሙኤል እናት እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ስለነበረች ስለ ሴትነት የተናገረቻቸው ቃላት ከእግዚአብሔር የተሰጡት በመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተካትተዋል።

እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ለመሆን ይህንን ምዕራፍ ማጥናት ከመጀመራችን በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሴትነታችንና ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ኅብረት የሚናገረውን በቅድሚያ እንመልከት።

## አንቺ ማን ነሽ?

አንቺ ማን ነሽ? በዚህች ዓለም እንዴት ልትኖሪ ቻልሽ? ከሕይወትሽ ጀርባ አንድ መተግበር ያለበት ዕቅድ ይኖር ይሆን? እስኪ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእነዚህ ጥያቄዎች ምን እንደሚል እንመልከት።

መዝሙር 138(139)፥13–16 አንብቢና ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ጻፊ።

እንዴት ነው የተፈጠርሽውና የተሠራሽው? ______________________

ቁጥር 14 ላይ «ግሩምና ድንቅ ሆነሽ» እንደተፈጠርሽ ይናገራል። ይሄ ምን ማለት ይመስልሻል?

እግዚአብሔር ለሕይወትሽ ዕቅድ አለው? ____________________

ይህ ዕቅድ ሙሉ ሕይወትሽን ያካትታል ወይስ ከሕይወትሽ የተወሰኑትን ጊዜያት ብቻ ነው? (ቁ:16) ____________________

## አንቺ ዋጋ አለሽ

ከተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዳየሽው ለእግዚአብሔር የተለየሽ ሰው ነሽ። ግሩምና ድንቅ አድርጎ ፈጥሮሻል። ስለዚህም በእርሱ ፊት ትልቅ ዋጋ አለሽ።

በእግዚአብሔር ዓይን ያለን ዋጋና ዓለም ሰዎችን የምትገምትበት ዋጋ ይለያያል። በዓለም ውስጥ አንድን ሴት ትልቅ ዋጋ ከሚያሰጧት ነገሮች ጥቂቶቹ ምን ምን ናቸው?

____________________

____________________

በኢትዮጵያ ሴቶች ዋጋ እንዳላቸው ያስባሉ ወይስ ራሳቸውን ዋጋ ቢስ እንደሆኑ አድርገው ያስባሉ?

____________________

ለምን እንደዚህ ያስባሉ?

____________________

ዓለም የሴቶችን ማንነት የምትለካው ውጫዊ ማንነታቸውን አይታ ነው። ውበት፥ ሀብት፥ መከናወን፥ ችሎታ - ዓለም የሰውን ማንነት ከምትመዝንባቸው መንገዶች አንዳንዶቹ ናቸው። እግዚአብሔር ግን እኛን የሚያይበት የተለየ መንገድ አለው። ሰው የማያየውን ያያል። ወደፊት ሊወጣ የሚችል የእርሱን ውበት ነጸብራቅ በእኛ ውስጥ ያያል።

አንዳንዶቻችን አፈጣጠራችን በዓለም ዓይን ተቀባይነት አያስጠንም። ምናልባት የአካል ጉዳተኛ እንሆናለን። ወይም ጠበብት አንሆን ይሆናል። አለያም ቆንጆ አይደለንም እንበል። እግዚአብሔር ግን ውጫዊ ማንነታችንን አያይም። እግዚአብሔር ከዚያ ያለፈን ነገር ያያል።

ቆንጆ ሥዕል ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ስታዪ ትኩረትሽ በምን ላይ ይሆናል? – በሥዕሉ ላይ ወይስ በሥዕሉ ዙሪያ ባለው ፍሬም? እርግጥ ነው የምታተኩሪው ሥዕሉ ላይ ነው። ምክንያቱም ጠቃሚው ክፍል ያ ነውና። ውጫዊ አካላችን ልክ እግዚአብሔር እኛን እንደ ገለጠበት የምስሉ ፍሬም ነው። የእኛ ሕይወት ልክ እግዚአብሔር እንደ ሠራው ሥዕል ነው።

ምንም እንኳን ፍጹም የሆንሽ ባይመስልሽም እግዚአብሔር እንደፈጠረሽና እንደሚወድሽ አስታውሺ። ከመወለድሽ በፊት ስለ አንቺ ያውቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር እኛን ዓለም ሳይፈጠር በፊት ያውቀናል። ኤፌ.1፡4ን አንብቢ። ለእግዚአብሔር ከቀይ ዕንቁ ይልቅ የተመረጥን ነን / ዋጋ አለን/።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በማየት የእግዚአብሔርን ጥልቅ ፍቅር የበለጠ ልንረዳ እንችላለን። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቢና ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚናገሩትን ጻፊ፡–

መዝ.33(34)፡18 ________________

ኢሳ.40፡11 ________________

ኢሳ.49፡15–16 ________________

ሮሜ.8፡35–39 ________________

## እግዚአብሔር እንደሚወደን አረጋግጧል

እግዚአብሔር እንደሚወደን እንዴት እናውቃለን? እርሱ ስላለ ብቻ? አይደለም። ይህንን የምናውቀው እግዚአብሔር እኛን እንደሚወደን ስለተናገረ ብቻ ሳይሆን – እኛን መውደዱን ለመግለጽ አንድያ ልጁን ልክ በመስቀል ላይ ስለሞተልን ነው። ዮሐ.1፡1–4ንና 1፡14ን አንብቢ። ቁጥር 14 እንደሚነግረን ዮሐንስ «ቃል» እያለ የሚጠራው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ በመካከላችን ኖረ። ዮሐ. 1፡1–4ና 1፡14 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ (ቃል) ምን ይናገራል? በእነዚህ ቁጥሮች ስለ ጌታ ኢየሱስ የተነገሩትን ዘርዝሪ /ቢያንስ ቢያንስ 7 ነገሮችን ለማግኘት ሞክሪ)።

________________

________________

________________

እነዚህ እና በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ ሌሎች ብዙ ጥቅሶች ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ይነግሩናል። ከዘመናት በፊት ይኖር እንደነበር በግልጽ ሰፍሯል። እንዲሁም ኢየሱስ ወደ ምድር እንደመጣና በመካከላችን እንደኖረ ይነግሩናል። ለምን ይህን አደረገ? ዮሐ. 10:10ን አንብቢና ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ ጻፊ፡-

ኢየሱስ «ሕይወት እንዲሆንላችሁ . . . . » ሲል ምን ማለቱ ነው? እኛ ሕይወት የለንምን? እንበላለን፥ እንሄዳለን፥ እንተነፍሳለን – ታዲያ ሕይወት ማለት ይህ አይደለም? ኢየሱስ የሚናገረው ስለ አካላዊ ሕይወት ሳይሆን ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ነበር። ምንም እንኳ በአካል ብንኖርም (እንኖራለን፥ እንተነፍሳለን) ያለ እግዚአብሔር በመንፈሳችን ሙታን እንደሆንን ኢየሱስ ያውቅ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው በመንፈስ የሞትንበት ምክንያት በኃጢአታችን ነው።

ሮሜ 3:23ን አንብቢ። በዚህ ጥቅስ መሠረት ኃጢአትን የሠራ ማን ነው? ______________________________

አንቺ ኃጢአት ሠርተሻል? ____________________

በዚህ ጥቅስ መሠረት የኃጢአት ውጤት ምንድን ነው? ________

ኃጢአት ስለሠራን የኃጢአትን ዋጋ እንከፍላለን። ያ ቅጣት ምንድን ነው? ሮሜ 6:23ን አንብበሽ ስለ ኃጢአት ዋጋ ምን ምን መከፈል እንዳለበት ጻፊ፡-

እንዳነበብሽው የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። ይህ ማለት ሁላችንም በኃጢአታችን ምክንያት በመንፈሳችን ሙታን ነን። መንፈሳዊ ሞት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ተቋርጧል ማለት ነው (በዚህም የእግዚአብሔር ክብር ጎድሎአል)። ወደ እግዚአብሔር በራሳችን ጥረት ልንደርስ ስለማንችል ከኃጢአት መቼም ቢሆን ነፃ መሆን አንችልም።

ነገር ግን ያው ጥቅስ (ሮሜ 6:23) እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ነፃ ስጦታ ይናገራል።

የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ምንድን ነው? ______________________

ስጦታው የመጣው በማን በኩል ነው? ______________________

ሮሜ 5፡8ን ና 1ኛ ጴጥ. 3፡18ን አንብቢ። ወደ እግዚአብሔር በመምጣት የዘላለም ሕይወት እንድናገኝ ኢየሱስ ምን አደረገ?

______________________________________________

ሮሜ 10፡9–13ን ና ዮሐ. 3፡16ን አንብቢ። የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ አለብሽ?

______________________________________________

______________________________________________

ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖርሽና የዘላለም ሕይወት እንድታገኚ ክርስቶስ ኢየሱስን ወደ ሕይወትሽ በመጋበዝ መቀበል እንዳለብሽ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ዮሐ. 1፡12)። ኢየሱስ አምላክ እንደሆነና ስለ ኃጢአትሽ እንደሞተ ማመን ብቻ በቂ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል አጋንንትም ይህንን ያምናሉ (ያዕ.2፡19)።

*ራሷን አሟት ወደ አንድ ሐኪም ስለሄደች ሴት አንድ ታሪክ ይነገራል። ሐኪሙ ከበሽታዋ እንደሚያድናት በመግለጽ መድኃኒቱን ሰጣት። ሴትየዋም መድኃኒቱ እንደሚፈውሳት አመነች። ስለዚህም መድኃኒቱን ወስዳ በቤቷ ካለ መደርደሪያ ላይ አስቀመጠችው፥ መድኃኒቱንም እያየች እንዲህ አለች። «መድኃኒቱ ከራስ ምታቴ እንደሚያሽለኝ አምናለሁ» ነገር ግን መድኃኒቱን አልዋጠችም።*

ራስ ምታቷ ሊፈወስ ይችላልን? ፈጽሞ አይችልም። ራስ ምታቷ እንዲለቅቃት መድኃኒቱን መዋጥ አለባት።

ልክ እንደዚሁ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ማወቁ ብቻ በቂ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሕይወትሽ በመጋበዝ የኃጢአት ይቅርታንና የዘላለም ሕይወት ስጦታን ልትቀበዪ ያስፈልጋል። የዘላለም ሕይወት ለማግኘት የሚከተሉትን መፈጸም አለብሽ፡–

1. ኃጢአተኛ እንደሆንሽና የኢየሱስ ምሕረት እንደሚያስፈልግሽ እመኚ።
2. ስለ ኃጢአትሽ ይቅርታ በመጠየቅ ከኃጢአት ጎዳና ለመመለስ ፈቃደኛ ሁኚ።

3. ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንቺ ኃጢአት በመስቀል ላይ እንደሞተና ከመቃብር እንደተነሣ እመኚ።

4. በጸሎት ጌታ ኢየሱስ ወደ ሕይወትሽ እንዲገባ ጋብዢው።

ይህን አድርገሽ ታውቂያለሽ? እስከ ዛሬ ጌታን ካልተቀበልሽ አሁን በእምነትና በጸሎት ልታደርጊው ትችያለሽ። ጸሎትሽ የግድ የተወሳሰበ መሆን የለበትም። ግን እውነተኛ መሆን አለበት። ቀጥሎ ኢየሱስን ወደ ሕይወትሽ መጋበዝ የምትችዪበት ጸሎት ቀርቦልሻል።

እንዲህ ጸልዪ።

«እግዚአብሔር ሆይ፦ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ። ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ሞቶ የኃጢአቴን ዋጋ ከፍሎአል። ስለዚህም አመሰግንሃለሁ። ዛሬ በዚህች ቀን ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኜና እንደ መድኃኒቴ እቀበለዋለሁ። በምሕረትህ ተቀበለኝ። ከአሁን ጀምሮ እንደ ፈቃድህ እንድኖር እርዳኝ። አሜን።»

ጌታ ኢየሱስን ወደ ሕይወትሽ ጋብዘሽው የማታውቂ ከሆነ አሁን ልትፈጽሚው ትችያለሽ። ኢየሱስ ስለሚወድሽ ሕይወቱን ስለአንቺ አሳልፎ ሰጠ። የምታበሪ ዕንቁ ትሆኚ ዘንድ ከአንቺ ጋር ኅብረቱን ማጠናከር ይፈልጋል። ኢየሱስ የሕይወትሽ ጌታ ከሆነ የዘላለም ስጦታ አለሽ።

1ኛ ዮሐ. 5፡12–13ን አንብቢ። ጌታ ኢየሱስን ከተቀበልሽ አሁን ምን አለሽ?

---

## ዋጋሽን ግልጽ ማድረግ

*ዕንቁ ፍለጋ ጉድጓድ ይቆፍር ስለ ነበር አንድ ሰው የሚነገር ታሪክ አለ። ሲቆፍር ትንንሽ ባልጩቶችን አገኘ። ቆሻሻ ስለነበሩ ይወረውራቸው ነበር። ሌላ ሰው መጣና የሚወረወሩትን ባልጩቶች አየ። አንሥቶ በጥንቃቄ ይመለከታቸው ጀመር – በዚህም ተራ ባልጩቶች እንዳልሆኑ ተገነዘበ – ዕንቁዎች ነበሩ! በጥንቃቄ ያጥባቸውና በሥርዓት በመቆራረጥ ውበትን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ አንጥረኛ ወሰዳቸው። ዕንቁዎቹም ብዙ ዋጋ በማውጣታቸው ሰውየው የናጠጠ ሀብታም ሆነ።*

ከላይ ከተጠቀሰው ታሪክ እንደምታዪው ዕንቁዎች አንዳንዴ ዋጋ ያላቸው አይመስሉም። እውነት ነው አንዳንዴ ዕንቁ ተራ ባልጩት ይመስላል። ነገር ግን ከተጠራረገና ውበቱ ይገለጥ ዘንድ እንደሚገባው

ከተቆራረጠ በጣም ውብና ዋጋ ያለው ይሆናል። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር እንዲጠራርገን፥ እንደሚገባ እንዲቀርጸንና ከመጀመሪያ ጀምሮ በውስጣችን ያለውን ውበት እንዲፈነጥቅልን ለእግዚአብሔር መፍቀድ ይኖርብናል።

ፊልጵ. 1፡6ን አንብቢ። እግዚአብሔር በእኛ የጀመረው ምን ዓይነት ሥራ ነው?

---

የሚፈጽመው ምንድን ነው?

---

እግዚአብሔር በአንቺ የጀመረውን መልካም ሥራ እንደሚፈጽመው ቃል ገብቷል። እግዚአብሔር ለሕይወትሽ ቃል ገብቷል። ስለዚህም ምክንያት በየደቂቃውና በየቀኑ ሊመራሽ ይጠባበቅሻል። አንዳንዴ የራሳችንን ወይም የሌሎችን ዋጋ መገንዘብ ያቅተናል። የፈጠረን እግዚአብሔር ግን ከውጫዊ ማንነታችን በላይ እውነተኛ ውበታችንንና ዋጋችንን ያውቃል።

እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል። በዚህም እርሱን በተሻለ መጠን እንድናውቅና እንዴት መኖር እንዳለብን እንዲረዳን ይፈልጋል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍ ስለ ራሳችን ማንነት የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን ሳይሸፋፍን ያሳያል። እግዚአብሔር ሕይወታችንን በመቅረጽ ጠቃሚነታችንና ውስጣዊ ውበታችንን እንዲያጎላው ለእግዚአብሔር ፈቃድን ስለ መስጠት ያስተምረናል።

## የእኔ ምላሽ

ጊዜ በመውሰድ ዋጋ ይሰጣሉ ብለሽ የምታስቢያቸውን መመዘኛዎች ጻፊ – ምናልባት መልክ ይሆን? ሥራ የማቀላጠፍ ችሎታ? ልጆችሽ ወይም ባልሽ? ገንዘብና ንብረትሽ፥ ጓደኞችሽ፥ ነፃ አገልግሎትሽ ወይስ የሕይወት ምስክርነትሽ? ወይስ የማንነት መመዘኛሽ የፈጠረሽና የሚወድሽ አምላክ ስለ አንቺ መጥቶ በመሞቱ ላይ ነው?

---

---

ስለ ራስሽ የሚያበሳጩሽ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

---

ማንነትሽን በእግዚአብሔር ዓይን በማየትሽ ስለ እነዚህ ነገሮች የሚኖርሽ አስተያየት እንዴት ሊለወጥ ይችላል?

ጥልቅና ታላቅ የሆነው እግዚአብሔር ለአንቺ ያለውን ፍቅር በእውነት መረዳት እንድትችዪ እንዲረዳሽ ጠይቂው። ያ እግዚአብሔር ለአንቺ ስላለው ፍቅር ያጠናሻቸውን ጥቅሶች የራስሽን ስም በመጨመር ጻፊያቸው። (ለምሳሌ «ራሔልን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ራሔልን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል. . . »)። እነዚህን ጥቅሶች በማሰላሰል እግዚአብሔር ስለሚወድሽና በእርሱ ዘንድ ትልቅ ዋጋ ስላለሽ አመስግኚው።

ኢሳ. 40፡11

ዮሐ. 3፡16

## ምዕራፍ 2

# በእግዚአብሔር ጸጋ ትኖራለች

ኤፌሶን 2፡8–9ን በልብሽ አጥኚ

«ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።»

## በጸጋ ብቻ

*አንድ ትንሽ ልጅ አንድ ነገር ለማድረግ እየታገለ ነበር። ሣር በሞላበት ሜዳ ላይ አጎንብሶ የጫማውን ማሰሪያ በመያዝ ወደ ላይ መሳብ ጀመረ። ይታገል ይታገልና ሲደክመው ለትንሽ ጊዜ ያርፋል። ከትንሽ ዕረፍት በኋላ እንደገና ያንኑ ደግሞ ያደርጋል። ዝም ብላ ስታየው የነበረችው እናቱ ከቤት ወጥታ ልጁ ወደ ነበረበት ሜዳ አመራች።*

*«ምን እያደረግህ ነው ልጄ? የሆነ ነገር ለማድረግ ስትታገል አየሁህ። ምን ልትሠራ ፈልገህ ነው?» አለችው። ልጁም መለሰ «ጠንካራ እንደሆንኩ አውቃለሁ። ታላቅ እህቴን መሸከም እችላለሁ። ስለዚህ የጫማ ማሰሪያዎቼን በመሳብ ራሴን ወደ ላይ ከፍ አድርጌ ለማንሣት እየሞከርኩ ነው። ግን ለምንድን ነው ያቃተኝ? ከብደቴ እኮ ከእህቴ ያንሣል። ግን ራሴን ማንሣት አልቻልኩም!» አላት።*

የጫማውን ማሰሪያ በመሳብ ራሱን ለማንሣት ስለሞከረው ልጅ ስናስብ እንስቃለን። «ምን ነክቶት ነው?» ብለን እናስባለን። ትንሹ ልጅ ራሱን ማንሣት የሚችል መስሎት ነበር። በሞኝነቱም እንስቃለን።

ነገር ግን እንደዚህ ዓይነቱን የማይቻል ሥራ በሞኝነት ለመሥራት የሚጥሩ ሕፃናት ብቻ አይደሉም። አዋቂዎችም እንዲህ ዓይነቱን ሥራ ልንሠራ ሲዳዳን ይታያል። እንደ ልጁ በጫማችን ማሰሪያ ራሳችንን ለማንሣት እንሞክር ይሆናል። ነገር ግን ፈጽሞ የማይቻልን ነገር ልናከናውን እንጥራለን– ለምሳሌ በራሳችን ብርታት መንግሥተ ሰማይ ለመግባት እንሞክራለን። «ጥሩ ሕይወት ከኖርኩ፥ ቤተ ክርስቲያን ከሄድኩ፥ ያለኝን ለችግረኞች ካካፈልኩ፥ ካልሰረቅሁ፥ ካላማሁና ካልዋሸሁ መንግሥተ ሰማይ ስተት ብዬ እገባለሁ» ብለን እናስባለን።

እነዚህን ነገሮች አስበሻቸው ታውቂያለሽ? ልክ እንደዚህ የሚያስቡ ሰዎችን ታውቂያለሽ? መጽሐፍ ቅዱስ በራሳችን መልካም ሥራ መንግሥተ ሰማይ መግባት እንደማንችል ይነግረናል። ይሄ ማለት ልክ እንደ ሕፃኑ ልጅ ራሳችንን በጫማችን ማሰሪያ ለማንሣት እንደመታገል

ነው። ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። ገላትያ 3፡1–3 በራሳችን ሥራ ደኅንነታችንን እንደምናገኝ ማመን ሞኝነት እንደሆነ ይናገራል።

## በጸጋ ድናለች

ኤፌ.2፡8–9ን በጥንቃቄ አንብቢ። እነዚህ ጥቅሶች እንደሚሉት እንዴት ነው የዳንነው? ____________________ አድኖአችኋል።

በአዲስ ኪዳን ብቻ «ጸጋ» የሚለው ቃል 123 ጊዜ ተጠቅሷል። ስለ እግዚአብሔር ጸጋ በቤተ ክርስቲያን ሲሰበክ እንሰማለን። እግዚአብሔር ጸጋውን ስለ ሰጠንም እናመሰግናለን። ከዚያም አልፈን ልጆቻችንን «ጸጋ፥ ጸጋነሽ. . . » ብለን እንጠራቸዋለን። ግን ጸጋ ምንድን ነው? ምን ማለት እንደሆነ በእውነት ተረድተናል? ቀጥሎ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ጸጋ ምን ማለት እንደሚመስልሽ በዝርዝር ጻፊ፡—

______________________________________________

______________________________________________

የማይነገር ስጦታ ተቀብለሽ ታውቂያለሽ? ብዙዎቻችን መልካም ነገር ስላደረግን ስጦታ ተቀብለን እናውቃለን። ለምሳሌ ቤተሰቦቻችን በትምህርት ስላሳየነው ትጋት ከረሜላ ወይም ገንዘብ ቢጤ ሰጥተውን ይሆናል። ወይም ደግሞ አንድን ሥራ በሚገባ በማከናወናችን ሽልማት ተቀብለን ይሆናል። ነገር ግን ምንም ሳታደርጊ፤ ፍጹም የማይገባሽ ስጦታ ተሰጥቶሽ ያውቃል?

*ትዕግሥት በአንድ ድርጅት ውስጥ ትሠራለች። ጥሩ ሠራተኛ አልነበረችም። ሁልጊዜ ዘግይታ ትመጣለች፥ በዚያ ላይ ደግሞ ሰነፍ ስለሆነች ምንም አትሠራም። ጥንቁቅ ስላልሆነች ብዙ ጥፋቶችን ትፈጽማለች። የምሳ ሰዓቷ አንድ ሰዓት ብቻ ቢሆንም የሚያየኝ የለም ብላ ስለምታስብ የምሳ ጊዜዋን ታስረዝማለች። እንዲያውም አንዳንዴ ሰው ሳያይት ከገንዘብ ያዡዋ ገንዘብ ትሠርቃለች። አንድ ቀን አሠሪዋ ወደ እርሷ መጣች። በጣም የሚያምርና ውድ የሆነ ስጦታን ለትዕግስት አመጣችላት። ትዕግሥትም «ለምንድን ነው የህን የምታደርጊው እኔ ጥሩ ሠራተኛ አይደለሁም። ይህ ስጦታም አይገባኝም» አለች። አሠሪዋ ግን ፈገግ ብላ የትዕግሥትን ዓይኖች እየተመለከተች «ስለ አንቺ ሁሉንም አውቃለሁ። ጠንክረሽ እንደማትሠሪ አውቃለሁ። ዘግይተሽ እንደምትመጪና ለምሳ ወጥተሽ ሰዓት እንደምታሳልፊም አውቃለሁ። ግን ስለምወድሽ ይህን ስጦታ ልሰጥሽ ወደድኩ» አለቻት።*

«ጸጋ» ለሚለው ቃል ለምሳሌ የሚሆነን ይህ ነው። ጸጋ ማለት ለማይገባው ሰው ስጦታን መስጠት ማለት ነው። ያልለፉበትን ስጦታ መስጠት ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ሲናገር የማይገባንንና ያልለፋንበትን ስጦታ በነፃ ሰጠን ማለቱ ነው። ይህም ስጦታ ደኅንነታችን (የዘላለም ሕይወት) ነው።

## የእግዚአብሔርን ጸጋ መረዳት

ኤፌሶን 2፡8 እንደሚለው «የዳንነው በጸጋ ነው»። እስኪ ቀድሞ ጸጋ ምን ማለት እንደሆነ የጻፍሽውን ተመልከቺ። ትክክል ነበርሽ? ካልሆንሽ ቀጥሎ ባለው ባዶ ቦታ ጸጋ ምን ማለት እንደሆነ ጻፊ፡-

---

---

ክርስቲያን እንደ መሆናችን የእግዚአብሔርን ጸጋ በጥልቀት መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ጸጋ ምን እንደሆነ ሙሉ መረዳት የላቸውም። ደኅንነታችን ያልለፋንበትና በነፃ የሚገኝ እንደሆነ አይረዱም ወይም አያምኑም። እነዚህ ክርስቲያኖች ጥሩ ሥራ ካልሠሩ ደኅንነታቸውን የሚያጡ ስለሚመስላቸው ይፈራሉ።

ስለ ደኅንነታቸው ኃላፊዎቹ ራሳቸው እንደሆኑ ይገምታሉ። የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው እንዲጠሩ ሥልጣንን የሰጣቸውና መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ የሚያበቃቸው መልካም ሥራቸው እንደሆነ ያምናሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ልክ ራሱን በጫማው ማሠሪያ ለማንሣት እንደሞከረው ሕፃን ናቸው። ራሳቸውን በራሳቸው ማዳን እንደማይችሉ ያልተገነዘቡ «ሞኞች» ናቸው።

ኤፌሶን 2፡8-9ን እንደገና ተመልከቺ። ቁጥር 9 ስለ መልካም ሥራ ምን ይናገራል?

---

ይህ ጥቅስ ግልጽ እንዳደረገው መልካም ሥራችን ለደኅንነታችን መዋጮ አይደለም። ደኅንነትን ለማግኘት እምነታችንን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ ከማድረግና በእርሱ ጸጋ ከመታመን ውጭ የምናደርገው ምንም ነገር የለም።

ደኅንነትን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው። ገና ኃጢአተኞች ሳለን ሊወደን መረጠ። ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ነፃ ስጦታ የሆነውን ጸጋውን ሰጠን። ይህን ስጦታ ለማግኘት የምንሠራው ሥራ የለም።

ማድረግ የሚገባን ቢኖር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን በእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ሞተ በማመን ክርስቶስን በሕይወታችን ላይ ጌታ አድርገን መቀበል ብቻ ነው። ዮሐንስ 1፡12ን አንብቢና የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ምን ማድረግ እንደ አለብን? /ሁለት ነገሮች/ ጻፊ።

______________________________

______________________________

## መልካም ሥራ

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር በሰማይ የእኛን ሕይወት የሚመዝንበት ሚዛን እንዳለው ያስባሉ። የምንሠራቸውን መልካምና መጥፎ ምግባሮች እየተከታተለ የሚመዘግብ ይመስላቸዋል። ከዚያ ሚዛኑን ያወጣል። በአንደኛው የሚዛን ጫፍ ላይ መልካሙን ሥራችንን በማስቀመጥ ኃጢአታችንን ደግሞ በሌላኛው ጫፍ ላይ ያኖረዋል። ከዚያም ራቅ ብሎ የትኛው ጎን እንደከበደ ያያል። ኃጢአታችን ከበጎ ሥራችን ከመዘነ ወደ መንግሥተ ሰማይ አንገባም ማለት ነው። ነገር ግን መልካሙ ሥራችን ከኃጢአታችን ከመዘነ ደኅንነትን ስለምናገኝ መንግሥተ ሰማይ እንገባለን።

እውን እግዚአብሔር እንዲህ ነው? ሕይወታችንን በመመዘን በሥራችን መዳን አለመዳናችንን ይወስናል? መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንዳስቀመጠው የእግዚአብሔር መንገድ ይህ አይደለም። እንዳነበብሽው ደኅንነታችን በሥራችን ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

እሺ ከዳንን በኋላስ? ጥሩ ክርስቲያኖች ካልሆንን ደኅንነታችንን ልናጣ እንችላለንን? አንዳንድ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ደኅንነታችን የእግዚአብሔር ስጦታ ቢሆንም ከዳንን በኋላ ጥሩ ሥራ ካልሠራን እግዚአብሔር አሳቡን በመቀየር የሰጠንን ነፃ ስጦታ መልሶ ይወስደዋል ብለው ያምናሉ። ይህ አስተሳሰብ ትክክል አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ለደኅንነታችን መሠረት መልካሙ ሥራችን እንዳልሆነ ሁሉ መልካም ምግባሮቻችን ደኅንነታችንን እንዳናጣ ዋስትና አይሆኑም። የዳንነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ያለስጋት ተጠብቀን የምንኖረውም በእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

> «በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን? እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ?

በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን?» (ገላ. 3፡2–3)።

ክርስቲያን ከሆንሽ ደኅንነትሽን የጀመርሽው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ነው። የዳንሽው የእግዚአብሔርን ሕግ ስለጠበቅሽ አይደለም ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ እምነትሽን በጌታ ኢየሱስ ላይ ስታደርጊ መንፈስ ቅዱስን ሰጠሽ። ታዲያ ደኅንነታችንን በመንፈስ ቅዱስ ጀምረን በራሳችን ጥረት ልንጠብቀው ይገባናል? የእግዚአብሔር ቃል ይህንን «ሞኝነት» ይለዋል። ደኅንነታችንን በራሳችን ጥረት እንደማናገኝ ሁሉ በራሳችን ኃይል ደኅንነታችንን ልናቃናና ልንጠብቀው አንችልም።

## *መታዘዝ ፍቅራችንን ያሳያል*

ደኅንነታችንን የሚሰጠን ወይም ደኅንነታችንን ከማጣት የሚጠብቀን እግዚአብሔርን መታዘዛችን አይደለም። ነገር ግን መታዘዝ ለክርስትና ሕይወት እጅግ ጠቃሚ ነው። መታዘዛችን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዳለንና እንደምንወደው ያስረግጣል።

ኢየሱስን ትወጂዋለሽ? የአንቺን ኃጢአት ዋጋ ለመክፈል ሲል ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አሰቃቂ ሞትን ሞተ። በጣም ይወድሻል፥ ያጽናናሻል፥ ያበረታሻል፥ ጉዳትሽ ይገባዋል፥ ስትፈተኚ ይረዳሻል፥ የሚያስፈልግሽን ያዘጋጅልሻል። በዘመንሽ ሁሉ ሊኖሩሽ ከሚችሉ ወዳጆች ምርጡ ጌታ ነው። ኢየሱስን ትወጂዋለሽ?

ከኢየሱስ ጋር እውነተኛ ኅብረት ካለሽ፥ በእርሱ ካመንሽና በልብሽ ከተቀበልሽው ለእርሱ ጠሊቅ ፍቅር ይኖርሻል። ለእርሱ ያለሽን ፍቅር ደግሞ ቃሉን በመታዘዝ ታሳይዋለሽ። መታዘዛችን በኢየሱስ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ወይም እንዲወደን ለማድረግ አይደለም። ኢየሱስ ቀድሞውኑ ወድዶናልና ተቀብሎናል። መታዘዛችን ላሳየን ፍቅር ምላሽ ነው።

*ሰው አፍቅረሽ ታውቂያለሽ? ጥላሁን የተባለ ጎልማሳ ያገባች አስቴር የምትባል ሴት ነበረች። ጥላሁን አስቴርን በጣም ስለሚወዳት ጥሩ አድርጎ ይንከባከባት ነበር። የሚያስፈልጋትን በማሟላት በተቻለው መጠን ጥሩና አፍቃሪ ባል ለመሆን ሞከረ። ጥላሁን ስለወደዳት አስቴርም መልሳ በማፍቀር ምላሽን ሰጠችው። ደስ ያሰኙታል ብላ ያሰበቻቸውን ሁሉ አደረገች። የሚወደውን ምግብ አዘጋጀችለት። ንጹሕ ቤት ስለሚወድ ቤቱን አጸዳች። ጸጉሯን እርሱ በሚወደው መልኩ ተሠራች። አስቴር ስትዘምር መስማት ጥላሁንን ስለሚያስደስተው ሥራዋን ስትሠራ ትዘምር ነበር። እነዚህን ነገሮች*

ሁሉ ያደረገችው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ጥላሁን ላሳየት ፍቅር ምላሽ ለመስጠት ነው። እርሱ ስለወደዳትና እርሷም ስለወደደችው ላሳየት ፍቅር ደስ የሚያሰኘውን በማድረግ ምላሽ ሰጠች።

ልክ እንደዚሁ ኢየሱስ ስላሳየን ፍቅር መልሰን እርሱን በማፍቀር ምላሽ ልንሰጥ ይገባናል። ኢየሱስን ትወጂዋለሽ? ዮሐ. 14፡15ን እና 21ን አንብቢ። ኢየሱስን በእውነት የምትወጂው ከሆነ ምን ታደርጊያለሽ?

---

---

ኢየሱስን ከወደድነው የሚያስደስቱትን ነገሮች ለማድረግ እንፈልጋለን። እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ምንድን ነው? የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቢና እግዚአብሔርን የሚያስደስቱትን አራት ነገሮች ጻፊ፡-

ቆላ. 1፡10-12

---

---

እግዚአብሔርን ለማስደሰት ማድረግ ከሚገቡን ነገሮች መካከል ይህ ጥቅስ የሚለንን አንዱን እንመልከት። መልካም ሥራ በመሥራት ፍሬ ማፍራት አለብን። መልካም ሥራ የምንሠራው ግን ደኅንነታችንን ለማግኘት ሳይሆን ደኅንነትን ስላገኘንና የወደደንን አምላካችንን ለማስደሰት ነው። እግዚአብሔር እኛን መውደዱን መቼም አያቆምም።

## አዲሱ ተፈጥሮአችን

ለእግዚአብሔር የምንታዘዝበት ሌላ ምክንያት አለ። እግዚአብሔር በውስጣችን ከሠራው ሥራ የተነሣ ታዛዥነት የምላበት ሕይወት መኖር አለብን። ክርስቲያን ስትሆኚ አስደናቂ ነገር ተከናውኗል። 2ኛ ቆሮ. 5፡17ን አንብበሽ ይህን አስደናቂ ነገር ጻፊ፡-

---

አዲስ ፍጥረት ነሽ ማለት ነው! አሮጌው አልፎአል። እነሆ አዲሱ መጥቶአል። ኢየሱስን ወደ ሕይወትሽ ከጋበዝሽው እግዚአብሔር በጸጋው አስደናቂ ነገርን አድርጓል። አባጨጓሬ ቢራቢሮ ሲሆን አይተሽ ታውቂያለሽ? አስቀያሚው አባጨጓሬ ራሱን በቅርፊት ውስጥ ጠቅልሎ ያኖራል። ምናልባት ለረጅም ቀናት ወይም ሳምንታት በዚያ ውስጥ

ይቆያል። አንድ ቀን ቅርፊቱ መሠነጣጠቅ ይጀምራል። ያኔ አስቀያሚ አባጨጓሬ ሆኖ ሳይሆን የሚያምር ቢራቢሮ ይሆናል። አባጨጓሬው ፍጹም ልዩ ወደ ሆነ ፍጥረት ተቀይሯል። ልክ እንደ አዲስ ፍጥረት።

ይህ አባጨጓሬ ከዛሬ ጀምሮ ቢራቢሮ እንደሆነ ባይገነዘብ ምን የሚሆን ይመስልሻል? ክንፎቹን ዘርግቶ በመብረር ፈንታ መሬት ለመሬት ቢንፏቀቅ ምን ትያለሽ? የተለወጠው ቢራቢሮ በአየር ላይ ከቦታ ቦታ ባይበርና ከአበባ ወደ ሌላ አበባ ባይንሳፈፍ እንዲያውም ጭራሽ መለወጡን ባይረዳ እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው? አንዳንዶ ክርስቲያኖችም መለወጡን ያላወቀውን ቢራቢሮ ይመስላሉ። እግዚአብሔር በሕይወትሽ ያደረገውን ለውጥ ታውቂያለሽ? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በክርስቶስ ባመንን ጊዜ አዲስ ፍጥረት በመሆን አዲስ ባሕርይን ተላብሰናል።

1ኛ ጴጥ. 2፡9ን አንብቢና 1) ጥቅሱ ክርስቲያን በመሆናችን ስለ እኛ የሚናገረውን ጻፊ። 2) እግዚአብሔር ለእኛ ምን አደረገ?

1. ______________________________

______________________________

2. ______________________________

1ኛ ተሰ. 5፡5ና ኤፌ. 5፡8ን አንብበሽ በእነዚህ ጥቅሶች ክርስቲያኖች ምን ተብለው እንደተጠሩ ቀጥለሽ ጻፊ፤—

የሚያስደንቁ ጥቅሶች ናቸው! እግዚአብሔር «ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን አውጥቶናል።» እኛ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ርስቱ የተለየን ወገን ነን።

አሁን ስለአነበብሻቸው ጥቅሶች ምን ይሰማሻል? ያስደስቱሻል? እነዚህ ጥቅሶች ስለ አንቺ የተናገሩትን ታምኛለሽ? ቀጥሎ በተሰጠው ባዶ ቦታ የምታስቢውንና የሚሰማሽን ነገር ጻፊ፤—

______________________________

## አዲስ ፍጥረት እንደሆንን መኖር (መመላለስ)

አባጨጓሬ ወደ ቢራቢሮነት ሲቀየር በአዲሱ ባሕሪው መኖር እንዳለበት ሁሉ እግዚአብሔር ወደ አዲስ ፍጥረትነት ሲቀይረን የተለወጠ ኑሮን ልንኖር ይገባል። ኤፌ. 4:22-24ን አንብበሽ በአሮጌው ሰውና በአዲሱ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ጻፊ፦

አሮጌው ሰው፡ ________________________________

________________________________________

አዲሱ ሰው፡ ________________________________

________________________________________

ኤፌ. 5:8-11ን አንብቢ። የብርሃን ልጆች እንዴት ነው «መኖርና መመላለስ» ያለባቸው?

________________________________________

________________________________________

1ኛ ዮሐ. 2:6ን አንብቢ። እውነተኛ ክርስቲያኖች ከሆንን ምን ማድረግ አለብን?

________________________________________

ክርስቲያን እንደመሆናችን አዲሱን ባሕርያችንን በየዕለቱ ማስታወስ ይጠበቅብናል። ራሳችን «በእግዚአብሔር የተወደድን፤ የተመረጠ ትውልድ፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየን ወገኖችና የብርሃን ልጆች ነን።» እንደ አዲሱ ተፈጥሮአችን መመላለስ እንድንችል እግዚአብሔርን ልንጠይቅ ይገባል። ኢየሱስ እንደተመላለሰ ለመመላለስ። የምንታዘዘው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሳይሆን እግዚአብሔር ስላሳየን ፍቅር ምላሽ ለመስጠትና እንደ እውነተኛ የብርሃን ልጆች ለመመላለስ ነው።

ይህንን መጽሐፍ ስታጠኚ እግዚአብሔርን የምትፈራን ሴት ሕይወትና ባሕርይ የምትማሪው እግዚአብሔር እንዲወድሽና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት እንዳልሆነ አስታውሺ። ክርስቲያን ከሆንሽ እግዚአብሔር ወሰን በሌለው ፍቅሩ ወድዶሻል፤ ተቀብሎሻል፤ የዘላለም ሕይወትም ሰጥቶሻል። አሁን የምትማሪው እንደ እግዚአብሔር ልጅነትሽና እግዚአብሔርን ስለምትወጂው እርሱን ለማስደሰት እንዴት መኖር እንዳለብሽ ነው። የሚወዳት አባቷን

ለማስደሰት እንደምትናፍቅ ልጅ የሚወደው ልጁን ስለ እኛ ይሞት ዘንድ አሳልፎ የሰጠውን አምላካችንን ለማስደሰት ልንናፍቅ ይገባል።

የእኔ ምላሽ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ።

መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ያበቃኝ ምንድን ነው?

---

እግዚአብሔር እንዲወደኝና እንዲቀበለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

---

የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ የምጥረው ለምንድን ነው?

---

## ምዕራፍ 3

# እምነት ይጣልባታል

**መዝሙር 9፡10ን በቃል አጥኚ**

**«ስምህን የሚያውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ፥ አቤቱ፥ የሚሹህን አትተዋቸውምና።»**

## እምነት ይጣልባታል

*እናት ልጇ በአጠገቧ ሲያልፍ ጎንበስ ብላ አቅፋ አነሣችው። ከዚያም ብብትና ብብቱን ይዛ ወደ ላይ ወረወረችው። ተመልሶ መሬት ላይ ከመፈጥፈጡ በፊት በእጇ ተቀበለችው። ልጁ ሳቀ፤ ፈነደቀ። ወድቄ እጎዳለሁ ብሎ ጭራሽ አላሰበም። እናት ለልጇ «ወደ ላይ ወርውሬህ ወደ መሬት ስትወርድ ለምንድን ነው ያልፈራኸው?» ብላ ስትጠይቀው ልጁ መልሶ «እንደምትወጂኝና የሚጎዳኝን ነገር ፈጽሞ እንደማታደርጊ ስለማውቅ ነው» አላት። ይህ ልጅ ያልፈራውና ስጋት ያላደረበት ሙሉ በሙሉ እናቱን በማመኑ ነው። እናቱ ታማኝ እንደሆነች ያውቃል።*

«የባልዋ ልብ ይታመንባታል።» በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 31 ቁጥር 11 ላይ እጅግ መልካም ሴት በባልዋ እምነት እንደሚጣልባት ይነግረናል። ይህ ክፍል ባሏ አልፎ አልፎ ወይም አብዛኛውን ጊዜ ብቻ እንደሚታመንባት አይናገርም። እንዲያው በጥቅሉ ባሏ እንደሚታመንባት ይናገራል። እምነቱ ገደብ ያለውና በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አይደለም። ታማኝ ሴት ስለሆነች ከእርሷ ጋር በሚኖረው ኅብረት ያለፍርሃትና ያለስጋት ይኖራል።

እውነተኛና መልካም ሴት ታማኝነቷ ለባሏ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ጭምር ነው። ልጆቿ ወላጆቿ፥ ጓደኞቿ፥ ጎረቤቶቿ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኗ ሰዎች ሁሉም እምነት ሊጥሉባት ይገባል።

*ሐቀኛ መሆን ማለት ምን ማለት ይመስልሻል?*

________________________________________

________________________________________

እምነት የሚጣልባት ማለት የምትታመን፤ አመኔታ የሚጣልባት፤ አደራ የማትበላ፤ የማትጠረጠር እና ሊደገፉባት የምትችል ሴት ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ ያስተምረናል። በእግዚአብሔር መታመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚከተሉት ጥቅሶች የሚሉትን ጻፊ፡-

- መዝ. 9:10 ____________________
- መዝ. 21(22):5 ____________________
- መዝ. 31(32):16 ____________________
- ኢሳ. 28፥ 16ና 1ኛ ጴጥ. 2:6 (ልታምኚበት የምትችዪው «የማዕዘን ድንጋይ» ማን ነው?)

____________________

እግዚአብሔር ታማኝ ነው፥ በእርሱ ብንታመን አናፍርም። በእርሱ የሚታመኑትን ፈጽሞ አይተዋቸውም። በማያልቅ ፍቅር ይከበናል። የእግዚአብሔር ታማኝነት በምሳሌነት ስላለን እምነት የሚጣልብን ሴቶች ለመሆን መጣር ይኖርብናል።

## ሐቀኛ ናት

እምነት የሚጣልብን ሴቶች የመሆኛ ብዙ መንገዶች አሉ። ከእነዚህ አንደኛው ሐቀኝነትና እውነተኝነት ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ ስለ ሐቀኝነትና እውነተኝነት የሚናገሩትን ጻፊ፡-

መዝ. 14(15):1-3

መዝ. 50(51):6 ____________________

ኤፌ. 4:25 ____________________

ምሳ.12:22 ____________________

ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምናየው እግዚአብሔር እውነትን የምንናገር ሴቶች እንድንሆን ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ስላልተናገረች ሰጲራ ስለ ተባለች ሴት የሚናገረው ታሪክ አለ። የሐዋ. 5:1-10ን እንብቢና እውነትን ስለመናገር ያለውን አሳብ ቀጥለሽ ጻፊ።

____________________

የሐናንያና የሰጲራ ታሪክ እግዚአብሔር ለእውነት ትልቅ ግምት እንዳለው ያስረዳል። ነገር ግን ዛሬም በዋሸን ጊዜ እግዚአብሔር

ወዲያውኑ ይገድለናል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሐናንያና ሰጲራን በዚያ ዘመን ለነበሩ አማኞች ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ቀሰፋቸው። እንዲሁም ለእኛ ክርስቲያኖች እውነተኞችና ሐቀኞች እንድንሆን ስለሚፈልግ ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ታሪካቸው ተጻፈ።

እግዚአብሔር ሕይወታችን የእርሱን ፈለግ የተከተለ እንዲሆን ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ እውነተኛነቱ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቢና በሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት ውስጥ ስላለው እውነት የሚናገሩትን አሳብ ጻፊ፡-

እግዚአብሔር አብ- መዝ. 30(31)፡5፤ ቲቶ 1፡2 ________________

እግዚአብሔር ወልድ ዮሐ. 14፡6 ___

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዮሐ. 14፡16-17

አሁን ደግሞ ዮሐ. 8፡44ን አንብቢና ይህ ክፍል የሐሰት ምንጭ ማን እንደሆነ እንደሚናገር ጻፊ።

*አስቴር ክርስቲያን ስትሆን በሳምንት ሁለት ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ትሄዳለች። በቤተክርስቲያን በመዝሙር ታገለግላለች። ርኅሩኅና አፍቃሪ ከመሆኗም በላይ ቤቷን ትንከባከባለች። ነገር ግን አስቴር በአንዳንዱ የሕይወቷ ክፍል ድካም ይታይባታል። እውነትን፤ ያለመናገር ልማድ ተጠናውቷታል። ብዙ ጊዜ በትንሹ ትዋሻለች። ለምሳሌ አንድ ቀን ባሏ እንዳያውቅባት ስትል በ8 ብር የገዛችውን ነገር በ4 ብር እንደገዛች ነገረችው። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጓደኛዋ የአራት ግብዣ ስለነበረባት ሳሕንና ብርጭቆ እንድታበድራት ስትጠይቃት ይሰበርብኛል ብላ ስለፈራች ሌላ ሰው እንደተዋሳት ነግራ መለሰቻት። አንዳንዴም የልጆቿን ጥፋት ለመሸፈን ስትል ትዋሻለች። ምንም እንኳ ዕቃውን የሰበረው ልጇ እንደሆን ብታውቅም እርሱ አይደለም ብላ ሽንጧን ገትራ ትሟገታለች። በውሸታምነቷ ምክንያት የቤተ ክርስቲያኗ ሰዎችና ጎረቤቶቿ አስቴር ቃሏ እንደማይታመን ተረድተዋል።*

እምነት የሚጣልብን ሴቶች መሆን የምንሻ ከሆነ እውነትን መናገር ይኖርብናል። በሁሉም አጋጣሚዎች ዘወትር እውነትን ብንናገር ቃላችን በሰዎች የታመነ ይሆናል። አንቺስ በዚህ ጉዳይ እንዴት ነሽ? ሁሌም ሐቀኛ ነሽ? ወይስ አንዳንዴ ውሸት ትናገሪያለሽ?

በአገራችን የምንናገረው «ዋሽቶ ማስታረቅ ያለ ነው» የሚል አባባል አለ፥ ይህ አባባል እውነት ይመስልሻል?

ማስታወስ ያለብሽ ነገር ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን የምንወስነው በራሳችን አስተሳሰብና ስሜት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመሥርተንና ተመርኩዘን መሆን ይኖርበታል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ውሸት በእግዚአብሔር ዘንድ ‹አስጸያፊ› ነው (ምሳ. 12:22)። በጣም ኃይለኛ ቃል ነው! ይህ ቃል እግዚአብሔር ግብረሰዶምን፤ የጣዖት አምልኮንና ሕፃናትን መሥዋዕት ማድረግን ምን ያህል እንደሚጠላ ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ነው። እግዚአብሔር ምን ያህል ውሸትን እንደሚጠላ ስንረዳ ምንም እንኳ በመልካም ስሜት ብንናገራቸውም ውሸት ምን ጊዜም ቢሆን ኃጢአት መሆኑን ማወቅ ይገባናል።

ትንንሽ ኃጢአቶች ብለን የምናስባቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የላቸውም። እምነት የሚጣልብን ሴቶች መሆን ከፈለግን ሁልጊዜ እውነት መናገር አለብን። ትንሽ ጊዜ በመውሰድ እስከ ዛሬ ስለነበርሽባቸው ምግባሮች እግዚአብሔር ይቅር እንዲልሽ ጠይቂው። ዘወትር ሐቀኛና እውነተኛ መሆን እንድትችዪ ጌታ እንዲረዳሽ ጸልዪ።

አታማም

ሌላው እምነት የሚጣልብን ሴቶች መሆን የምንችልበት መንገድ ሐሜት አለመናገር ነው። ሐሜት ስለ ሰዎች እንድንናገር የማይፈልጉትን መጥፎ ነገር እነርሱ በሌሉበት ለሌሎች መናገር ማለት ነው። አንዳንዴ ሰዎች ሐሜትን እንደ መልካም ሥራ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

ሐሜት ምን ጉዳት ሲያደርስ አይተሻል?

ስለ ሌሎች ማውራት ትክክል የሚሆነው መቼ ነው?

ስለ ሌሎች ማውራት ትክክል የማይሆነውስ? ______

የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በማንበብ ስለ ሐሜት (ስም ማጥፋት) የሚናገሩትን ጻፊ።

ምሳ. 11፡13 ______

ምሳ. 16፡28 ______

ሮሜ 1፡28–32

ለማማት የተፈተንሽው መቼ ነበር? ______

______

*ራሔል በአንድ ቢሮ ውስጥ ትሠራለች። በየቀኑ ምሣዋን የምትበላው አብረዋት ከሚሠሩ ጓደኞቿ ጋር ነው። አንዳንዴም ምሣ ሰዓት ላይ ጓደኞቿ በቢሮ ውስጥ ስለሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ያወራሉ። አንዳንዴ እየሳቁ ስለ ሰዎቹ ተግባር እየተነጋገሩ ያሳግጣሉ። ምንም እንኳ ራሔል ማማት እንደሌለባት ብታውቅም እያሾፉ ስለሚያወሩት ነገር እየሠማች አንዳንዴ ትሥቃለች።*

አንቺም ለሐሜት የሚገፋፉ ሐሜተኛ ጓደኞች አሉሽን? ምሳ.20፡19 ከሐሜተኞች ጋር እንዳንተባበር ይነግረናል። ጥሩ ጓደኞች ኖረውሽ ሐሜተኞች ከሆኑ ኅብረታችሁን መመዘን ይኖርብሻል። እግዚአብሔር አንቺ ከእነርሱ ጋር ጥቂት ጊዜ ብቻ እንድታሳልፊ ወይም ደግሞ ሐሜትን ማስወገድ እንዳለባቸው እንድትነግሪያቸው ይፈልጋል።

እኛ እያለን ሌሎች ሰዎች ሐሜት ከጀመሩ ምላሻችን ምን መሆን አለበት? ማድረግ የምትችያቸውን ነገሮች ጻፊ።

## አመኔታ ይጣልባታል

ታማኝ ልንሆን የምንችልበት ሌላው መንገድ በሰዎች ዘንድ አመኔታን ስናገኝ ነው። አመኔታና ታማኝ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቀጥለሽ ጻፊ።

ይተማመንባታል ______

ታማኝነት (ሩት 1፡1–18ን በማንበብ ሩት ለኑኃሚን የነበራትን ታማኝነት ተመልከቺ።)

______

______

*አልማዝ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ከሆነው ከተስፋዬ ጋር ተጋባች። በአገልግሎት ምክንያት ብዙ ይጓዛል። አንዳንዴ ለብዙ ሳምንታት ይቆያል። በቤት ውስጥ ያሉትን ጉዳዮች እንደሚገባ ለማከናወን አልማዝ ተስፋዬ በማይኖርበት ጊዜ አመኔታ የሚጣልባት ልትሆን ይገባል። ማለትም ተስፋዬ በሌለ ጊዜ ምንም ዓይነት ችግር ቢመጣ ሁሉንም በጥንቃቄ እንደምታስተናግድ ሊተማመንባት ይገባል። ታማኝ መሆንም ይጠበቅባታል። ምንም እንኳ አንዳንዴ የሚያበሳጩ ጉዳዮች ቢገጥሟትም ታማኝ በመሆን ነገሮችን በቤትዋና በቤተ ክርስቲያን እንደየአመጣጣቸው በመመለስ ኃላፊነቷን መወጣት ይኖርባታል።*

እግዚአብሔር በትዳራችን ብቻ ሳይሆን በሕይወታችን ክፍሎች ሁሉ ታማኝና ሰዎች አመኔታ የሚጥሉብን ሴቶች እንድንሆን ይፈልጋል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቢና ብዙ ጊዜ፥ አልፎ አልፎ፥ አንዳንዴ በማለት መልሺ።

## በሰዎች ዘንድ አመኔታ ይጣልብሻል?

- አንድ ሰው ርዳታ ፈልጎ ወደ አንቺ ሲመጣ ልትረጂው እንደምትሞክሪ አመኔታ ይጥልብሻል? ____________

- አንድ ነገር አደርጋለሁ ካልሽ በእውነት ታደርጊዋለሽ? (እርሷ የተናገረችውን የምታደርግ ናት ብለው እንደ ምሳሌ ይቆጥሩሻል?)

- ሥራ ካለሽ አሠሪሽ ሥራሽን እንደሚገባ በጥንቃቄ እንደምታከናውኚ ይተማመንብሻል? ____________

- ባለትዳር ከሆንሽ ኃላፊነትሽን እንደሚገባው እንደምትወጪ ባልሽ ይተማመንብሻል? ____________

## ታማኝ ነሽ?

- ጓደኞችሽ፥ ዘመዶችሽና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚያናድድሽን ነገር ሲያደርጉ ቶሎ ብለሽ ትለያቸዋለሽ?

  ____________

- ጓደኞችሽ፥ ዘመዶችሽ ወይም የቤተ ክርስቲያን አባል ችግር ቢኖርባቸው ከጎናቸው በመቆም ትረጂያቸዋለሽ ወይስ ትሸሺያቸዋለሽ? ____________

- ባለትዳር ከሆንሽ ለባልሽ በአሳብ፥ በቃልሽና በምግባርሽ ታማኝ ነሽን?

ታማኞችና ሰዎች የሚተማመኑብን መሆን እምነት የሚጣልብን የመሆን አንደኛው መንገድ ነው። እነዚህ ነገሮች በሕይወታችን ካሉን ከዕንቁ የተመረጥን ሴቶች እንድንሆን ይረዱናል።

## የእኔ ምላሽ

እምነት የሚጣልብን ስለመሆን ላደረግሽው ጥናት ምላሽሽ ምንድን ነው? ምናልባት እግዚአብሔር ማሻሻል የሚገባሽን የሕይወትሽን ክፍል አሳይቶሽ ይሆናል።

- የበለጠ ሐቀኛ መሆን ይገባሻልን?
- ሐሜት ያስቸግርሻልን?
- የበለጠ ታማኝና የሚተማመኑብሽ ሴት መሆን ይገባሻልን?

እግዚአብሔር እምነት የሚጣልብሽ ሴት ለመሆን በሕይወትሽ መለወጥ እንዳለብሽ የተናገረሽ ከሆነ የምትፈልጊያቸውን የሕይወት ለውጦች ቀጥለሽ ጻፊያቸው። ከዚያም ስለ እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጸልዪ። እርሱ ታማኝ ስለሆነ ይረዳሻል።

## ምዕራፍ 4

# ትጉሕ ሠራተኛ ናት

ቆላ. 3፡23–24ን በልብሽ አጥኚ

«ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፥ ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን ነውና።»

## የልባም ሴት የሥራ ልምድ

*ፀሐይ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ናት። ቀኑን ሙሉ ባተሌ ናት። ልጆቿን ከመንከባከብ በተጨማሪ የባሏን ጎደሎ ለመሙላት ተፍ ተፍ ትላለች። በቤተ ክርስቲያንም ታገለግላለች። ብዙ ጊዜ ገና ሌሊት ሳለ ትነሣና እስኪመሽ ድረስ ትሠራለች። ሥራዋን ያለማጉረምረም በደስታና በእርግጠኝነት ታከናውናለች።*

ምሳሌ 31 እንደሚነግረን ልባም ሴት ትጉሕ ሠራተኛ ናት። በምሳሌ 31 የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ተመልከቺና ልባም ሴት ስላላት የሥራ ልምድ የሚለውን ጻፊ፦

ቁጥር 13 ______________________________

ቁጥር 14 ______________________________

ቁጥር 15 ______________________________

ቁጥር 16 ______________________________

ቁጥር 17 ______________________________

ቁጥር 18 ______________________________

ቁጥር 21 ______________________________

ቁጥር 22 ______________________________

ቁጥር 24 ______________________________

ቁጥር 27 ______________________________

እነዚህን ጥቅሶች ስንመለከት የተጠቀሰችው ሴት ትጉሕና ኃላፊነቷን በአግባቡ የምትወጣ እንደሆነች ግልጽ ብሎ ይታያል። በሥራ ልማድሽ አንቺ እንዴት ነሽ? ሥራሽን በአግባቡ ለማከናወን

ትቸገሪያለሽን? አንዳንዴ የማያስደስትሽን ሥራ በመተው የምትወጂውን ሌላ ነገር ትሠሪያለሽ? ለሥራ ያለሽ ስሜት እንዴት ነው? የተቻለሽን ስታደርጊ ታጉረመርሚያለሽ?

ሰዎች ሁሉ በሕይወታቸው በዚህ ዓይነት ችግር ሲፋጠጡ ይታያል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት መኖር ከፈለግን ለሥራ ልማዳችን ሥርዓት ያለው ጥሩ አመለካከት ማሳደጉ እጅግ ጠቃሚ ነው።

## እግዚአብሔር ስለ ስንፍና ምን ይላል?

ማድረግ የሚገባንን ከማየታችን በፊት ማድረግ የማይገባንን እንመልከት። በትጋት ጠንክሮ የመሥራት ተቃራኒ ስንፍና ነው። የእግዚአብሔር ቃል ስለ ስንፍና በብዙ ቦታ ይናገራል። እነዚህን ጥቅሶች በማንበብ ብቻ እግዚአብሔር ስንፍናን እንዴት እንደሚያየው መረዳት ይቻላል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች ከመጽሐፈ ምሳሌ በማንበብ እግዚአብሔር ስለ ስንፍና የሚናገረውን ጻፊ፡—

ምሳ. 10:26

ምሳ. 15:19 ____________________

ምሳ. 18:9

ምሳ. 21:25

እነዚህን ጥቅሶች ስታነቢ እግዚአብሔር ስንፍናን የሚያየው እንደ ቀላል ችግር ነው ወይስ እንደ ትልቅ ችግር? መልስሽን አብራሪ።

ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር ስንፍናን አይወድም። በምሳሌ 18:9 ላይ እግዚአብሔር ሲናገር በሥራው ታካች የሆነ ሰው የሀብት አጥፊ እንደሆነ አንብበናል። ስንፍና ለሕይወታችን አደገኛ ስለሆነና ጉዳት ስለሚያደርስ እግዚአብሔር እንደ ትልቅ ችግር ያየዋል። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከሥራ የሚባረሩት፥ ትምህርት የሚያቋርጡትና ከሌሎች ጋር ያላቸው ኅብረት የሚሻከረው በስንፍና ምክንያት ነው።

ሰንፍና ትልቅ ችግር ያደረሰበት የምታውቂው አጋጣሚ ካለ ቀጥለሽ ጻፊው (እባክሽ ሐሜትን ለማስወገድ የሰዎችን ስም እንዳትጠቅሺ።)

---

እግዚአብሔር ሰንፍናን እንደ ትልቅ ችግር የሚያይበት ሌላው ምክንያት በምድር ላይ ለእግዚአብሔር ሥራ አደገኛ ሊሆን ስለሚችል ነው። በእግዚአብሔር ሥራ ስንፍና ሊያመጣ ስለሚችለው ችግር ምሳሌ ስጪ።

---

## ትጋት

የስንፍና ተቃራኒ ትጋት ነው። እግዚአብሔር በሥራችን ትጉ እንድንሆን ይፈልጋል። ትጉ መሆን ማለት ምን ማለት ይመስልሻል? በትጉ ሠራተኝነቷ ስለምታውቂያት ሌላ ሴት እስኪ ቀጥለሽ ጻፊ። ትጉ ነች ያልሻት ለምንድን ነው?

---

ትጉ መሆን ማለት ሥራችንን ማጠናቀቅ ብቻ ማለት አይደለም። ነገር ግን ሥራችንን በጥንቃቄና በጥራት መሥራት ማለት ነው። ትጋት ማለት በሥራችን ከሚጠበቅብን በላይ ማከናወን ማለት ነው። ሴቶች እንደ መሆናችን ብዙ ሥራ አለን። በቤት ውስጥ እንሠራለን፥ ልጆች እንንከባከባለን፥ በቤተ ክርስቲያን እናገለግላለን ምናልባት ከቤት ውጭ ሥራ ይኖረን ይሆናል፤ የምንከባከባቸው አዛውንት ዘመዶቻችን ይኖራሉ። እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ በትጋት እንድንሠራ ይፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ርብቃ ስለ ተባለች ሴት እናነባለን። ርብቃ ትጉህና ደስተኛ ሠራተኛ በመሆን ከሚጠበቅባት በላይ ታከናውን ነበር። ዘፍጥረት 24፡15-20ን አንብበሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ።

የአብርሃም ሎሌ ውኃ እንድታጠጣው ሲጠይቃት የርብቃ ምላሽ ምን ነበር?

________________________________________

ርብቃ ለግመሎቹም ሁሉ ውኃ ቀዳች። ስንት ግመሎች ነበሩት? (ቁ.10)

________________________________________

ርብቃ ለግመሎቹ ስንት እንስራ ውኃ ነው እቀዳለሁ ያለችው? (ቁ. 19)

________________________________________

ርብቃ ግመሎቹን ውኃ እንድታጠጣ አልተጠየቀችም ነበር። ሎሌው ውኃ እንድታጠጣው ብቻ ነበር የጠየቃት። ርብቃ ግን ከተጠየቀችው በላይ አደረገች። ሌላን ሰው ለማገልገል በነበራት መሻት እንኳ ትጉሕ ነበረች።

አንድ ግመል 27 ሊትር ውኃ ይጠጣል። ሎሌው ደግሞ አሥር ግመሎች ነበሩት። ይህ ማለት ደግሞ ርብቃ 270 ሊትር ውኃ መቅዳት ነበረባት። ዝንባሌዋ ግን ማጉረምረምና ማልመጥ አልነበረም። በምንባቡ ውስጥ ሁለት ጊዜ ርብቃ ሥራዋን በፍጥነት እንዳቀላጠፈችና ሌላ ልትቀዳ ወደ ጉድጓድ መሮጧም ተገልፆልናል (ቁ. 18 ና 20)። እዚህ ጋ በግልጽ እንደተጻፈው ርብቃ የተጠየቀችውን በደስታ፥ በጥንቃቄና በትጋት ለማከናወን የተቻላትን እንዳደረገች እናያለን።

ይህ መመሪያ «የርብቃ መመሪያ» ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ምንም እንኳ ሥራው አስቸጋሪ እና ከተጠየቅነው በላይ ቢሆንም ሳንነጫነጭና ሳናጉረመርም በጥንቃቄና በደስታ ስናከናውን «የርብቃን መመሪያ» ተከትለናል ማለት ነው። የርብቃን መመሪያ ትከተያለሽን? ሥራሽን በደስታና በፍጥነት ታከናውኛለሽ ወይስ በዝግታ፥ በመነጫነጭና በማጉረምረም ነው የምትሠሪው? የሚጠበቅብሽን ያህል ብቻ ነው የምትሠሪው ወይስ ከተጠየቅሽው በላይ ለመሥራት ትጥሪያለሽ?

## የምትሠሪው ለማን እንደሆነ አስታውሺ

ምናልባት ጥረታችንንና ልፋታችንን ሰዎች የማይረዱልን ከሆነ የርብቃን ምሳሌ በመከተል በትጋት ለመሥራት አስቸጋሪ ይሆን ይሆናል። በተለይ ለብዙ ሴቶች የርብቃን መመሪያ ለመከተል የሚቸገሩት በቤታቸው ውስጥ ሲሠሩ ነው። የቤት ውስጥ ሥራ ብዙ ጊዜ ደስ የሚያሰኝ አይደለም፤ ብዙ ልፋትን ይጠይቃል። ብዙ ጊዜ ደግሞ አድናቆትንና ምስጋናን የምናገኝበት አካባቢ ስላልሆነ ያስቸግራል።

ማስታወስ የሚገባን ነገር ቢኖር የቤት ውስጥን ሥራ ጨምሮ የምናደርጋቸውን ነገሮች በሙሉ የምንሠራው ከሰዎች ዘንድ ምስጋናን ለማግኘት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነው።

ቆላ. 3፡22-24ን አንብበሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ:-

ቁጥር 22 ማድረግ የማይገባን ነገር ምንድን ነው ይላል?

_______________________________________________

ቁጥር 23 ና 24 የምናደርገው ለማን ነው ይላል?

_______________________________________________

የምንሠራው ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰዎች እንዳልሆነ በኤፌ.6፡5-8 ላይ በድጋሚ ሲንጸባረቅ ይታያል። (ይህንን ክፍል አንብቢው።) ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰው ክፍል ባሪያዎች ጌቶቻቸውን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው ለማሳወቅ የተጻፈ ቢሆንም መርሁ ግን በቤት ለምንሠራ፥ ለአሠሪዎቻችን ግልጋሎት ለምንሰጥና በቤት፥ በቤተ ክርስቲያንና በሌላም ቦታ ለምንሠራ ተግባራዊ ይሆናል። ያለማቋረጥ ማስታወስ ያለብን የምንሠራው እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንጂ ሰዎችን ለማስደሰት አይደለም። ሌላው ማስታወስ ያለብን ነገር በሥራችን ክብርን የምንሰጠው ለእግዚአብሔር እንጂ ለራሳችን እንዳልሆነ ነው።

*በአንድ ወቅት ትልቅ አዳራሽ እንድታጸዳ ሥራ ስለ ተሰጣት ወጣት የሚነገር ታሪክ አለ። ቆሻሻና አቧራው በትክክል መጠረጉን እያረጋገጠች ጠንክራ ሠራች። በአዳራሹ መጨረሻ በደረሰች ጊዜ ወደ አንድ ትልቅ የጠረጴዛ መሳቢያዎች ተጠጋች። የመሳቢያዎቹን ሥር ሥር መጠረግ አለመጠረጉን ማንም አያየውም ብላ ስለገመተች አልፋው ሄደች። ነገር ግን ተመለሰችና የመሳቢያዎቹን ሥር ጠረገች። እየጠረገች ሳለች እንዲህ አለች «እኔ ይህንን የምሠራው ለኢየሱስ ነው»። ሥር ሥሩን ያጸዳችው ሰዎች እንዲያመሰግኗት ብላ አይደለም፥ ነገር ግን በክርስቶስ ፊት ትጉሕ ሠራተኛ መሆንን ስለመረጠች እንጂ።*

እንደ እግዚአብሔር ሴትነታችን ለጌታ ስንል ሥራዎችን መሥራት መማር አለብን።

## ሳይነጫነጩ መሥራት

በአዲስ አበባ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል የሆነች አንዲት ድሃ ሴት ነበረች። ሥራም ሆነ ሌላ የገቢ ምንጭ ስላልነበራት የቤት ኪራይ ለመክፈልና ለልጆቿ ምግብ ለመግዛት ተቸገረች። የቤት

ክርስቲያን መሪዎች ድህነቷንና ምስኪንነቷን ተረድተው ሥራ አዘጋጁላት። ሥራዋ ቤተ ክርስቲያንን ማጽዳት ነበር። መጥረግ፥ የቆሻሻ ቅርጫቶችን መገልበጥ፥ ወንበሮችን ማስተካከልና የመሳሰሉትን ነበር የምትሠራው።

ስለ ሥራዋ በማመስገን ፈንታ ስለ ተሰጣት ሥራ ትነጫነጭ ነበር። ለሁለት ሳምንታት ከሠራች በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሄደች «የዚህ ዓይነት ሥራ አልፈልግም! እኔ የነገሥታት ንጉሥ ልጅ ነኝ! የንጉሥ ልጅ እንዲህ ዓይነት ርካሽ ሥራ መሥራት ይገባታልን?» በማለት ሥራዋን አቆመች። ከጥቂት ቀናት በኋላ ገንዘብ ስለሌላት ሰዎች እንዲረዱት የእርጥባን ወረቀት መበተኗን መሪዎች ሰሙ።

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ሥራችንን ሳናጉረመርምና ሳንነጫነጭ ስንሠራ ለእግዚአብሔር ክብርን እንሰጣለን። ምንም ዓይነት ሥራ ቢኖረን በደስታ ልንሠራ ያስፈልጋል። ጌታ ኢየሱስ ራሱ የተሰጠውን ሥራ በደስታና በፍቅር ፈጽሟል። በቅንነትና በፍቅር የደቀ መዛሙርቱን እግር እስከማጠብ ድረስ ፈቃደኛ ነበር! ጌታ ኢየሱስ የንጉሥ ልጅ ብቻ ሳይሆን የነገሥታት ንጉሥም ነበር። ምሳሌ 31፡13ን አንብቢ። ይህቺ ሴት ሥራዋን ስትሠራ አስተሳሰብዋ እንዴት ነበር?

---

ፊልጵ.2፡14–16ን አንብቢና ለሚከተሉት ለጥያቄዎች መልስ ስጪ።

ሁሉን ነገር ስንሠራ አስተሳሰባችን ምን መሆን አለበት? (ቁ. 14)

---

የአስተሳሰባችን ውጤት ምን ይሆናል? (ቁ. 15–16)

---

ለሥራችን የሚኖረን አስተሳሰብ ክርስቲያናዊ ምስክርነታችንን እንዴት ያበላሸዋል?

---

የተሳሳተ አስተሳሰብ ስሜትሽን እንዴት ነው የሚያዛባው?

## መጀመሪያ መሠራት ለሚገባቸው ቅድሚያ መስጠት

ሥራችንን ስንሠራ ጠቃሚው ነገር ሥራችንን በትጋትና በደስታ ማከናወናችን ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ የሆኑትን ነገሮች መሥራትም ጭምር ነው። በትጋትና በደስታ የተሳሳቱ ነገሮችን ማከናወን ይቻላል። የምንሠራው ሥራ እግዚአብሔር እንድንሠራው የሚፈልገው ሥራ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለብን።

ሰይጣን አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖችን ምርጥ በሆነው ፈንታ ጥሩ ነገር እንዲያደርጉ ይፈታተናቸዋል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የሁለቱ ሴቶች ማለትም የማርያምና የማርታ ታሪክ ነው።

ይህንን ታሪክ በሉቃ. 10:39-42 ላይ አንብበሽ ቀጥለው ያሉትን ጥያቄዎች መልሺ፡-

ኢየሱስ በቤታቸው ሳለ ማርያም ምን ትሠራ ነበር? ____________

____________

ማርታስ ምን ትሠራ ነበር? ____________

ኢየሱስ ማርያም ልትሠራ ስለመረጠችው ነገር ምን አለ? ____________

____________

ጌታ ኢየሱስ ማርያም «መልካም ዕድልን መርጣለች» ሲል ማርታ የምታደርገው መጥፎ ነው ማለቱ ነውን? በፍጹም አይደለም። ኢየሱስ ምግብ እንዲበላና እንደሚገባው እንዲስተናገድ መትጋቷ መጥፎ ምግባር አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ጥሩ ነገር ነው። ጌታ ኢየሱስ ግን ማርታ ከዚህ የተሻለ ነገር እንድታደርግ ወደደ። ምርጥ የሆነውን ነገር እንድታደርግ ፈለገ። እግሩ ሥር ተቀምጣ የሚናገረውን እንድትሰማ ነበር የፈለገው።

ማርታ ኢየሱስን «ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?» ብላ ብትጠይቀው ኖሮ ይነግራት ነበር። ነገር ግን አልጠየቀችም። ለራሷ እንደመሰላት የራሷን ውሳኔ ወሰደች።

አንዳንዴ ልክ ናቸው ብለን የምናስባቸው ነገሮች እግዚአብሔር እንድንሠራ የማይፈልገው ሆነው ይገኛሉ። ለምንሠራው ሥራ ቅድሚያ በመስጠት አንጻር ብዙ ጊዜ እንስታለን። ቅደም ተከተል ስናወጣ ለእኛ የሚቀሉንንና የምንወዳቸውን በማስቀደም አስቸጋሪዎቹን ደግሞ እናስቀራቸዋለን። ይህ ውሳኔ ለማድረግ ትክክለኛው መንገድ አይደለም። ልንሠራው ስላለን ሥራ በውሳኔያችን እግዚአብሔር እንዲረዳን እርሱን መጠየቅ ይኖርብናል። በየዕለቱ በማለዳ ቀኑን ሙሉ ምን ማድረግ እንዳለብን የእርሱን ትእዛዝ ልንቀበል እንችላለን። ከዚያ ቀኑን ሙሉ ሥራችንን ስንሠራ የእግዚአብሔርን ምሪት መከተል እንችላለን።

ከዚህ በፊት ምርጥ ነገር በመሥራት ፈንታ ጥሩ ነገር ያደረግሽበትን አጋጣሚ ቀጥለሽ ጻፊ፡—

______________________________________________

______________________________________________

የማትወጂውን ሥራ ወደ ጎን ያገለልሽበትን አጋጣሚ ቀጥለሽ ጻፊ፡—

______________________________________________

## የእኔ ምላሽ

ምሳሌ 31 ግልጽ እንደሚያደርገው ጥሩ ሴት ስንፍና አይነካካትም። እንዲያውም ስላለባት ኃላፊነት ትጉሕና ታታሪ ናት። የምሳሌ 31 ሴት «የሀኬትንም እንጀራ አትበላም. . . ገና ሌሊት ሳለ ትነሣለች። ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች. . . ንግድዋ መልካም እንደሆነ ትመለከታለች. . . በእጆችዋም ደስ ብሏት ትሠራለች፥ መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም።»

በሥራ ልማድሽ እንዴት ነሽ? ቀጥለው የተዘረዘሩትን በመመልከት ትጋትሽን መዝኚው፡—

- ሥራዬን በታታሪነት እሠራለሁ፥ ጊዜ አላባክንም?
- መሥራት ያለብኝን ወደ ጎን አላገልልም?
- በሥራዬ ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት እንዳለብኝ ለማወቅ እጸልያለሁ?

- የርብቃን መመሪያ በመከተል ከተጠየቅሁት በላይ እሠራለሁ?
- ሥራዬን በደስታ ሳላጉረመርምና ሳልነጫነጭ እሠራለሁ?
- ሥራዬን ለሰዎች ሳይሆን ለእግዚአብሔር እሠራለሁ?

በሥራ ልማድሽ አንዳንድ ለውጦችን ማድረግ ትፈልጊያለሽን? ባሕርያችንን በራሳችን ለመቀየር ያስቸግረናል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ረዳትነት የሥራ ልማዳችንን በመቀየር ልባም ሴቶች ልንሆን እንችላለን።

አሁኑኑ ጊዜ ወስደሽ በመጸለይ እግዚአብሔር ቅድሚያ በመስጠት ላይ ምሪትን እንዲሰጥሽና ሥራሽን በትክክለኛ ስሜትና አሳብ ማከናወን እንድትችይ እንዲረዳሽ ጠይቂው።

## ምዕራፍ 5

# በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች

ፊልጵ. 4፡6–7ን በልብሽ አጥኚ

«በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።»

## በኋላ ዘመን ላይ መሳቅ

*አልጋዋ ላይ ጋደም እንዳለች መብራቱን ስታጠፋ ልቧ ተጨንቆ ነበር። በሕይወቷ ብዙ ችግሮች ነበሩ! ባሏ ሥራ የለውም፣ ልጇ ደግሞ ታሟል፥ በቤቱ የነበረው የጤፍ ዱቄትም ቢሆን ከጥቂት ቀናት በኋላ ያከትምለታል። መጪው ሕይወቷን ስታስብ ተጨነቀች። ነገ የሚጨመሩትን ችግሮች ደግሞ እግዚአብሔር ይቁጠራቸው! ነገን እንዴት ነው ይኽን ሁሉ ችግር ተሸክማ የምትጋፈጠው?*

አንቺስ በሕይወት ዘመንሽ እንዲህ ተሰምቶሽ ያውቃል? ሁላችንም ችግርና መከራ ገጥሞናል። በምሳሌ 31 የተገለጸችው ሴት እንኳ ሳትቀር ችግርን ተጋፍጣለች። ነገር ግን የመጽሐፈ ምሳሌን የመጨረሻ ምዕራፍ ስናነብ ስለዚህች ልባም ሴት አንድ ነገር እናስተውላለን– ስለ መጪው ዘመን አትጨነቅም፥ ደግሞም አትሰጋም። ቁጥር 21 ና 25 እንዲህ ይላሉ፡– *«ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ የተነሣ አትፈራም፥ የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና. . . በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች»።*

እስኪ የመጀመሪያውን ጥቅስ በማስተዋል እንየው፥ «ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ የተነሣ አትፈራም»። ሰዎች ዝናብ ዘንቦ በረዶም አከባቢውን ሁሉ ሲያቀዘቅዝ ለምንድን ነው የሚፈሩት? ምንም እንኳን በኢትዮጵያ የበረዶ መጠን አነስተኛ ቢሆንም በአንዳንድ አገሮች አመዳይ እንደ ዝናብ ስለሚወርድ ተጠራቅሞ የሙቀቱን መጠን በጣም ይቀንሰዋል። በዚያ ቀን ወደ ውጭ የወጣ ሰው በብርድ ተቆራምዶ ሊሞት ይችላል። እንዲያውም አንዳንዴ የአመዳዩ ክምር የቤታቸውን ዙሪያ ስለሚሸፍነው ብዙ ሰዎች በዚሁ ምክንያት ሞተዋል። አንዳንዶቹማ ከብርዱ ኃይለኛነት የተነሣ ሕይወታቸው የሚያልፈው ቤታቸው ውስጥ ነው። አየሽ ለዚህ ነው ሰዎች የአመዳይ ዝናብንና የበረዶ ክምርን የሚፈሩትና ሲያካፋ የሚጨነቁት።

ነገር ግን ምሳሌ 31 ይህች ሴት በረዶ እንደማትፈራ ይነግረናል። ለምን ይሆን? መልሱ ቀጥሎ ያለው ጥቅስ ላይ ይገኛል። «የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸው»። ይህች ሴት የማትፈራበት ምክንያት ቀደም ብላ እጥፍ ድርብ (ወፍራም) ልብስ ስላዘጋጀች ነው። መጪው ዘመን ሊያመጣ ለሚችለው ችግር ማድረግ የሚገባትን ዝግጅት አድርጋለች። በኋላ ዘመን የምትስቅበት ሌላም ምክንያት አለ። ምክንያቱም እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ አድርጋለችና ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለተረዳችና እግዚአብሔር እምነት የሚጣልበት አምላክ መሆኑን ስላወቀች ስለወደፊት በመጨነቅ ፈንታ በዘመኑ ላይ ትስቃለች።

## መሳቅ ትችያለሽን?

በኋላ (በመጪው) ዘመን መሳቅ ትችያለሽን? ወይስ ራስሽን ስለ መጪው ዘመን እያሰብሽ ስትጨነቂ ታገኚዋለሽ? እስኪ ስለ «ጭንቀት» ትንሽ ጊዜ ወስደን ትርጉሙን እንመልከት። አዲስ ኪዳን መጀመሪያ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነበር። የቃሉን ትርጉም በሚገባ ለመረዳት የግሪኩን ጥሬ ትርጉም ማየቱ ጠቀሜታ አለው። ይህ ቃል የመጣው «አእምሮ»ና «መከፋፈል» ከሚሉ ሁለት ቃላት ነው። ስንጨነቅ አእምሮአችን ለሁለት ይከፈላል። በሌሎች ነገሮች ላይ ማተኮር ይሳነናል። ምክንያቱም አእምሮአችን በጭንቀት ተከፍሎአልና። ስለ አንድ ነገር መጨነቅ መላ ሕይወታችንን ሊያናጋና ሊጎዳን ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ጭንቀት ኃጢአት እንደሆነ ይናገረናል። ማቴዎስ 6፡25–34 ያለውን አንብበሽ እንዳንጨነቅባቸው የተነገሩንን ሦስት ነገሮች ቀጥለሽ ጻፊ፦

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ስንጨነቅ በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ምን ያህል ነው ይላል? (ቁ. 30)

________________________________________

በጭንቀት ፈንታ ኃይላችንን ለምን ማዋል አለብን? (ቁ. 33)

________________________________________

በጣም የምትጨነቂበት ወይም የምትፈሪው ነገር ምንድን ነው? ቀጥሎ ባለው ባዶ ቦታ የምትጨነቂባቸውን ነገሮች ሁሉ ዘርዝረሽ ጻፊ፡-

---

ጥቂት ጊዜ በመውሰድ ስለሚያስጨንቁሽ ነገሮች አስቢ። አንዳንዶቹ ልትሠሪያቸው የምትችያቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከአቅምሽ በላይ ናቸው። ብዙዎቹ የሚያስጨንቁን ነገሮች ደግሞ የሁለቱም ቅልቅል ናቸው። እስኪ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንይ።

- በትምህርት ቤት ፈተና ጥሩ ውጤት ስለማምጣት የምትጨነቂ ከሆነ ቢያንስ ቢያንስ በራስሽ ልታደርጊያቸው የምትችያቸው ነገሮች ይኖራሉ–ጠንክረሽ በማጥናት ራስሽን ለፈተና ማዘጋጀት ትችያለሽ።
- በሠርግሽ ቀን የዝናብ መዝነብ አለመዝነብ ጉዳይ ግን ከቁጥጥርሽ ውጭ ነው። በአየሩ ጠባይ ላይ ምንም ጉልበት አይኖርሽም።
- ስለ ልጅሽ የወደፊት ሕይወት የምትሰጊ ከሆነ ከላይ የጠቀስናቸው የሁለቱም ቅልቅል ነው። ልጅሽ በትምህርቱ እንዲያጠና ልትረጂው፥ ጠንካራ አንባቢ እንዲሆን ሥርዓት ልታስተምሪው፥ የልጅሽ ጓደኞች ጥሩ ልጆች መሆን አለመሆናቸውንም ልታረጋግጪ፥ ስለ ኢየሱስ ልታስተምሪውና በቤት ውስጥ ጥሩ ምሳሌነትን ልታሳዪው፥ በየቀኑ ልትጸልዪለትና የመሳሰሉ ነገሮችን ልታከናውኚ መብቱና ችሎታው አለሽ። ነገር ግን የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት ወይም ፖለቲካ ወይም የሥራ ችግር መቆጣጠር ስለማትችዪ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እርሱ ያከናውናቸው ዘንድ በጸሎት ለእግዚአብሔር አሳልፈሽ መስጠት አለብሽ።

እስኪ ከላይ የጠቀስኻቸውን ጭንቀቶችሽን ተመልከች። ስለተጨነቅሽባቸው ነገሮች ማድረግ የምትችዪው ነገር አለን? አንዳንዶቹ ጭንቀቶችሽ በእግዚአብሔር ብቻ የሚከናወኑ ናቸውን? ስለ እያንዳንዱ ጭንቀትሽ ጊዜ ወስደሽ አስቢና ቀጥሎ ያለውን ሠንጠረዥ ሙዪ። የመጀመሪያው ምሳሌ ይሆንሽ ዘንድ ተሠርቶልኻል።

| ጭንቀቴ | ማድረግ የምችለው | በእግዚአብሔር ብቻ የሚሠሩ |
|---|---|---|
| 1. የልጄ ጉዳይ | እንዲያጠና መርዳት፤ ጓደኞቹ ጥሩ እንደሆኑ ማረጋገጥ፤ ስለ ኢየሱስ ማስተማር፤ ጥሩ ምሳሌ መሆን፤ በየቀኑ ስለ እርሱ መጸለይ . . . ወዘተ። | የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ፤ የሥራ ማጣት፤ የልጄ የወደፊት ሥራ. . . ወዘተ። |
| 2. | | |
| 3. | | |
| 4. | | |
| 5. | | |

## ጭንቀትሽን ለእግዚአብሔር ስጪ

ከላይ ለዘረዘርሻቸው ጉዳዮች መልስ መጨነቅ የለብሽም። በጭንቀት ፈንታ እርምጃ መውሰድ አለብሽ። በመጀመሪያ፥ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለብሽ። ምንም ማድረግ የማንችላቸውን ጉዳዮች አንድ በአንድ በጸሎት ለእግዚአብሔር ማስረከብ የግድ ነው። የሆነ ነገር ማድረግ ስለምንችልባቸው ጉዳዮችም ጭምር መጸለይ ይኖርብናል። ምክንያቱም ያለ እግዚአብሔር እርዳታ አንዳች ማድረግ አይቻለንምና።

ችግሮችሽንና ጭንቀቶችሽን ለእግዚአብሔር አሳልፈሽ ከሰጠሽ በኋላ መልሰሽ አታስታውሺያቸው። ስለ ነገሮቹ በጣም የምትጨነቂ ከሆነ ለእግዚአብሔር አልሰጠሻቸውም ማለት ነው። ዝም ብለሽ ጭንቀትሽን በመሸከም አእምሮሽን ለሁለት ትከፍይዋለሽ።

አንዳንድ ጊዜ ችግሮችሽንና ጭንቀቶችሽን ለእግዚአብሔር መስጠትሽን በአዕምሮሽ መሣል ጥሩ ነው። ስለተጨነቅሽባቸው ነገሮች ስትጸልዪ በአዕምሮሽ አንድ ትልቅ ሳጥን እንዳለ አድርገሽ አስቢ። ከዚያ በኋላ ስትጸልዪ ችግሮችሽን አንድ በአንድ ወደ ቅርጫት ውስጥ እንደምትጥዪ አስቢ። ችግርሽን ሁሉ ሳጥን ውስጥ ካስገባሽ በኋላ ሳጥንሽን ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠሽው አስቢ። ከዚያም በጸሎት እግዚአብሔርን እንዲህ በዪው፡-

«ጌታ ሆይ፥ እባክህ ይህንን ውሰድ። ጌታ ሆይ ችግሮቼና ጭንቀቶቼ ከአቅሜ በላይ ስለሆኑ ልሰጥህ ወደድኩ። እነዚህን ነገሮች ለመቆጣጠር ጉልበት ስለሌለኝ አልቻልኳቸውም። አንተ ግን ትችላለህ። ጭንቀቶቼን ሁሉ አንተ እንደ ፈቃድህ ልታስወግዳቸው ቃል ገብተሃል። ስለዚህም ነው ሁሉንም ላንተ የምሰጠው። ለአንተ አሳልፌ ልሰጥህና ደግሜ ስለ እነዚህ ላለመጨነቅ ወስኛለሁ።»

ችግርን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ስለ መስጠት ያለውን ሂደት በአእምሮ መሣሉ ጭንቀቶችሽ እንዲወገዱና ለእግዚአብሔር አሳልፈሽ እንድትሰጪ ይረዳሻል።

በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ የመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ታሪኳን የምናነበው ሐና ብዙ ጭንቀቶች ነበሯት። ልጅ እንዲኖራት በጣም ትፈልግ ነበር፥ ግን አላገኘችም። የባሏ ሌላኛዋ ሚስቱ ሐና ልጅ ስላልነበራት ትሳለቅና ታላግጥባት ነበር። ሐና ችግሯን በሙሉ መቆጣጠር ባትችልም ምን ማድረግ እንዳለባት ግን ታውቅ ነበር። ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ በጸሎት «በእግዚአብሔር ፊት ነፍሷን አፈሰሰች።» (1፡15)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሐና ጭንቀቷን ለእግዚአብሔር አሳልፋ ከሰጠች በኋላ «መንገዷን ሄደች፤ በላችም ፊቷም ከእንግዲህ ወዲያ ኀዘንተኛ መስሎ አልታየም» (1፡18)። ችግሯን ለእግዚአብሔር በመስጠት እንደገና ሕይወቷ በደስታ ተሞላ።

ቀጥለው የተሰጡትን ጥቅሶች በማንበብ ችግራችንና ጭንቀታችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ስለመስጠት የሚናገሩትንና እግዚአብሔር ደግሞ ሊያደርግልን የገባልንን ተስፋ ጻፊ፡-

1ኛ ጴጥ.5፡7 ________________________

መዝ. 54(55)፡22 ________________________

መዝ. 93(94)፡19

ፊልጵ. 4፡6–7 ________________________________

## የምትችዪውን ማድረግ

ስለ ጭንቀታችን መጸለይ እንዳለብን አይተናል። ነገር ግን እግዚአብሔር እንድንጸልይ ብቻ አይፈልግም። ስለምንጨነቅባቸው ነገሮች ማድረግ የምንችለውን መፈጸም ይኖርብናል። ጊዜያችንንና አጋጣሚዎችን በመጠቀም እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን መንገዶችና ዕድሎች ልንጠቀምባቸው ይገባል።

መጽሐፈ አስቴር የፋርስ ንግሥት እንደሆነች አይሁዳውያን ይናገራሉ። በአንድ ወቅት ችግር ገጥሟት ነበር። በዚህ ምድር ይኖሩ የነበሩትን አይሁዳውያን በሙሉ አይሁድ ያልነበረው ንጉሥ ሊገድላቸው እንደፈለገ ሰማች። አስቴር ስለዚህ ጉዳይ ሦስት ቀን ጸለየች። ነገር ግን በጸሎት ብቻ አልቆመችም፥ እርምጃም ወሰደች። ምንም እንኳ በንጉሥ ሳትጠራ ወደ እርሱ ለመቅረብ በመሞከሯ ልትገደል ብትችልም (አስ.4፡11) በንጉሥ ፊት መቆምን ቆረጠች። በዚህ እርምጃዋም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት አተረፈች።

ጸሎት ትልቅ ጥቅም አለው። ነገር ግን መጽሐፈ አስቴር እንደሚነግረን መጸለይ ብቻ ሳይሆን ማድረግ የሚገባንን ነገሮች መፈጸም ይገባናል።

በምሳሌ 6፡6–8 ላይ ወደፊት በማቀድ ስለመጪው ዘመን እንዴት መዘጋጀት እንዳለብን ሲገልጽ እግዚአብሔር የጉንዳንን ምሳሌ ተጠቅሟል። እነዚህን ጥቅሶች በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሽ።

ጉንዳን ስለ ወደፊት ዘመን ሲዘጋጅ ምን ያደርጋል? __________

ጉንዳን ራስን በሥርዓት ስለማኖር የሚያሳየው ምሳሌ ምንድን ነው? (ቁ. 7)

ቁጥር 6 ላይ እንደሚናገረው የጉንዳንን ምሳሌ ብንከተል ጠቢብ እንሆናለን። እግዚአብሔር የሚያደርገውን እናያለን በማለት እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ የለብንም። ይልቁንስ በተቻለን አቅም ስለ ወደፊቱ መዘጋጀት አለብን። ወደፊት ስላለው ዘመን ለመዘጋጀት ምን

እያደረግሽ ነው? ለገንዘብሽ ጥሩ ባለ አደራ ነሽን? ማጠራቀም የምትችዪውን ያህል በማስቀመጥ ከዕዳ ነፃ ነሽን? ምንም እንኳን ገቢሽ አነስተኛ ቢሆንም በየሳምንቱ ትንሽ ሳንቲምም ቢሆን በማሰሮ ነገር ልታስቀምጪ ትችያለሽ። ቀደም ብለሽ ያሰብሽውን ዕቅድሽንና ዓላማሽን ከግብ ለማድረስ በየቀኑ የተቻለሽን ትፈጽሚያለሽን? እግዚአብሔር እንደ ጉንዳን ጠቢብ እንድንሆንና ስለመጪው ዘመን እንድንዘጋጅ ይፈልጋል።

ባለፈው ገጽ ላይ ያለውን ሠንጠረዥ ተመልከች። በሁለተኛው ረድፍ የጻፍሻቸውን ከልሺ። ስለ ጭንቀትሽ መሥራት የምትችዪው ነገር ካለ ማድረግ ብትጀምሪ ጥሩ ነው። መሥራት የምትችዪውን ዝም ብለሽ አታቆዪ። ዕቅዶችን አውጪና ዛሬውኑ መሥራት ጀምሪ። የምትችዪውን ስትሠሪ መጸለይን አትርሺ።

## ለጭንቀት ፍቱን መድኃኒት (መፍትሔ)

ፊልጵ. 4:6–7ን ደግመሽ ተመልከቺ። ቁ. 8 ላይ ስለምን ማሰብ አለብን ይላል?

____________________________________________

____________________________________________

ጭንቀትን ለማቆምና የእግዚአብሔርን ሰላም ለመለማመድ የሚያስጨንቁንን ነገሮች ማሰብ እንደሌለብን ነገር ግን በዚያ ፈንታ መልካም ወሬ ያለበትን፤ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን እንድናስብ ያሳስበናል።

በዓለም ላይ ካሉ ነገሮች ሁሉ እነዚህን ማግኘት የሚቻለው በእግዚአብሔርና በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ብቻ ነው። ልናስብና ልናሰላስል የምንችለው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው። ለጭንቀት ፍቱን መፍትሔ ይሄ ነው።

መዝ. 1:1–3ን አንብቢ። ቁጥር 3 ላይ የአንድ ጠንካራ፥ ውብ፥ ፍሬያማና ቅጠሉ የማይረግፍ ዛፍ ምሳሌ ተሰጥቶናል። የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በማሰላሰል ከፍርሃትና ከስጋት የምንድነው እንዴት ነው?

____________________________________________

እንደ ምሳሌ 31 ሴት በኋላ ዘመን ላይ መሳቅ ትፈልጊያለሽ? ከሚያስጨንቅ ስጋት ልትድኚ ትወጂያለሽን? እንግዲያውስ ጭንቀትሽን በማቆም መጸለይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ፥ ማጥናትና

ማሰላሰል ጀምሪ። ስለ ችግሮችሽ ማሰብን አቁሚ። በዚያ ፈንታ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ኃይል አስቢ። ይህም ስለ ራስሽና ቤተሰብሽ ሕይወት በእግዚአብሔር ላይ እንድትታመኚ ይረዳሻል። ኃላፊነትሽን ለመወጣት ጉልበት በመስጠት ለወደፊት እንድትዘጋጂ ያስችልሻል።

ከጸለይሽ በኋላ የሚከተሉትን ርምጃዎች ውሰጂ። መሥራት የምትችዪውን አስበሽ ማድረግ ጀምሪ፤ «አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል» ፊልጵ. 4፡7።

*«ጭንቀት ዛሬን ያበላሸዋል እንጂ የነገን ችግር አያቃልልም»።*

ኮሬ ቴን ቡም

## የእኔ ምላሽ

ከዚህ በፊት የጻፍሺያቸውን የሚያስጨንቁሽን ነገሮች ዝርዝር ለእግዚአብሔር በጸሎት አሳልፈሽ ስጪ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራቸው የሚችላቸውን ጉዳዮች ወደ ጎን አድርጊና አንቺ ማድረግ የምትችያቸውን ነገሮች እንዴት መሥራት እንዳለብሽ እግዚአብሔር እንዲያሳይሽ ጠይቂው። ለተጨነቅሽባቸው ነገሮች በዚህ ሳምንት መሥራት የምትጀምሪያቸውን ሦስት ነገሮች ቀጥለሽ ጻፊ፡–

1.

2. __

3.

ቀጥለሽ መልካም፥ ንጹሕና ምስጋና የሚገባቸውን የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ጊዜ ወስደሽ አሰላስዪ፡– ዘዳ. 31፡6፤ መዝ. 18፡28–36፤ መዝ. 39(40)፡1–3፤ ኢሳ. 41፡10፤ ኤር. 29፡11፤ ኤር. 31፡17፤ ማር. 10፡27፤ ሮሜ 8፡31–39፤ ኤፌ. 3፡20፤ ፊልጵ. 4፡13።

ምዕራፍ 6

# አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች

የያዕቆብ መልእክት ምዕ.3፡17

«ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ፥ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት»።

## የጥበብ ምንጭ

*ሶፊያ በጥበብ የተሞላች ሴት ናት። የተለያዩ ሰዎች ከቤትዋ ምክርዋን ለማድመጥና ለመቀበል አዘውትረው ሲገቡና ሲወጡ ይታያሉ። ሶፊያ የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ትምህርት አልወሰደችም። በዚህ አገልግሎት ምንም የተሰጣት ሥልጠና የለም። እንዲህ በጥበብ የተሞላችው እንዴት እንደሆነ ማንም ማወቅ አልቻለም። ነገር ግን ሁልጊዜ የማይለያትና ስታነብ የምትታየው መጽሐፍ ቅዱስዋን ነው። ጧት በማለዳ እንዲሁም በምሽት ሶፊያ የምትታየው በመስኮቷ አጠገብ ተቀምጣ መጽሐፍ ቅዱስዋን ስታነብና ስታጠናው ነው።*

ምሳሌ 31 ልባም ሴት አፍዋን በጥበብ እንደምትከፍት ይናገራል። ይህንን ጥበብ ከየት ማግኘት ይቻል ይሆን? ይህ ጥያቄ በዘመናት ሰዎችን ያነጋገረ ጥያቄ ነው። ሰዎች የጥበብ ምንጭ ከወዴት ነው ብለው ይገምታሉ?

ኢዮብ 28 ላይ ኢዮብ ይህንን ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርቧል። «ጥበብ የምትገኘው ወዴት ነው?» መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጥያቄ ይመልሰዋል። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበሽ ስለ ጥበብ ምንጭ የሚገልጸውን ጻፊ።

ኢዮብ 12፡13

ቆላስይስ 2፡2-3 ________________________________

እውነተኛ የጥበብ ምንጭ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና። የእርሱ ጥበብ ፍጹም፥ ሙሉና ከሰው ጥበብ እጅግ የላቀ ነው። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ «ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና» ይላል።

በሕይወታችን ውስጥ ይህንን ጥበብ ማግኘት እንዴት ይቻላል? ጥበብ ከየት እንደምትገኝ የሚያውቅ አንድ እግዚአብሔር ነው። እርሱም ይህንን የጥበብ ምሥጢር ገልጾልናል። ኢዮብ 28:28ን አንብበሽ እግዚአብሔር ስለ ጥበብ የተናገረውን አሳብ ጻፊ።

________________________________________

ከጥበብ ዋነኛውና የመጀመሪያው ባሕርይ «እግዚአብሔርን መፍራት ነው»። እኛ ለእግዚአብሔር የሚገባው ፍርሀት ቢኖረንና እግዚአብሔርን እንደሚገባ ብናከብረው፥ ብንወደውና ብንታዘዘው ጥበብ የተሞላን እንሆናለን። እግዚአብሔርን መፍራት ምን ማለት እንደሆነ በይበልጥ በምዕራፍ አሥር ላይ በተብራራ መልኩ እናየዋለን።

ጥበብ ሌላ የተለያዩ ገጽታዎች አሏት። የሚከተሉትን ጥቅሶች በማየት ስለ ጥበብ የሚገልጹትን ጻፍ።

ዘዳግም 4:5-6 ______________________________

________________________________________

ምሳሌ 11:2 ______________________________

ምሳሌ 19:11 ______________________________

ምሳሌ 13:10 ______________________________

ያዕቆብ 3:17 ______________________________

________________________________________

መዝ. (51):6 ______________________________

የላይኛዎቹን ጥቅሶች ስናነብ ጥበብ የተለያዩ ገጽታዎች እንዳሏት ግልጽ ነው። ጥበበኛ መሆን የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ፥ ትሑት መሆንና የሌሎችን ምክር መቀበል መቻል ነው። በተጨማሪም ከእነዚህ ጥቅሶች ለመረዳት የምንችለው እግዚአብሔርን ብንጠይቀው ጥበብን በልባችን ውስጥ ሊያስተምረን እንደሚችል ነው።

## እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጥ መጠየቅ

ልባም ሴቶች ለመሆን በጥበብ ማደግ ይኖርብናል። ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች የጥበብን የተለያዩ ገጽታዎች ያሳዩናል። ነገር ግን ይህንን ጥበብ እንዴት ማግኘት ይቻላል? ብዙ ሰዎች ጥበብን የሚፈልጓት በማይሆን በታ ነው። አንዳንዶቹ ጌታን ከማያውቁ ሰዎች

ምክርን በመጠየቅ ይፈልጓታል። ሌሎች ደግሞ ከቃልቻና ከመሳሰሉ ዘንድ በመሄድ ምክርን ይሻሉ። እነዚህ ግን ጥበብን ማግኛ ዘዴዎች አይደሉም። የጥበብ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው እንዴት በጥበብ የተሞላ ምክርን መስጠት ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብን ማግኘት የምንችልበትን መንገድ ይነግረናል።

ያዕቆብ 1፡5ን አንብበሽ መልሺ።

---

እግዚአብሔር ጥበብን ብንሻና ብንጠይቀው እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል። ያዕቆብ በመጽሐፍ ቅዱስ « ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱም ይሰጠዋል» ይላል። ስለዚህም እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጠን መጠየቅ ጥበብን ለማግኘት የመጀመሪያው ደረጃ ይሆናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ጥበበኛ እንዲያደርገው የጠየቀ ሰሎሞን የሚባል ሰው ነበር። 2ኛ ዜና 1፡7–12ን አንብቢ። በዚህ ታሪክ ሰሎሞን ቁጥራቸው እንደ ምድር ትቢያ ብዙ ለሆነው የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ ተደርጎ ተሹሞ ነበር። እግዚአብሔር ሰሎሞንን «ምን እንድሰጥህ ለምነኝ» ሲል ጠየቀው። ሰሎሞን ይህንን ታላቅ ሕዝብ ለመምራት የሚያስችል ጥበብ እንደሚያስፈልገው ተረድቶ ስለነበርና በራሱም ኃይል አንዳች ማድረግ እንደማይችል ስላወቀ ለእግዚአብሔር የጸለየው ጸሎት «ጥበብንና እውቀትን ስጠኝ» የሚል ነበር። እግዚአብሔር በሰሎሞን ጥያቄ እጅግ ተደስቶ «ጥበብንና እውቀትን ሰጥቼሀለሁ» አለው።

እግዚአብሔር ለሰሎሞን የሰጠው ጥበብ ምን ያህል ነበር? 1ኛ ነገሥት 4፡22ን አንብበሽ መልሱን ጻፊ።

እግዚአብሔር ለሰሎሞን የእስራኤልን ሕዝብ ለመምራት የሚያስችለውን ጥበብ ሰጠው። እግዚአብሔር ለእኛም እርሱን በመታዘዝ የምናገለግልበትን ጥበብ ይሰጠናል። እግዚአብሔር አባታችን ጥበብን ለጠየቁት ሁሉ ለመስጠት ያዘጋጀው ትልቅ የጥበብ ጎተራ አለው። የእግዚአብሔርን ጥበብ በየትኛው የኑሮ ሁኔታሽ ላይ እንደምትሺ ጻፊ። (ለምሳሌ አንዳንድ ውሳኔዎችን እንዴት እንደምትወስኚ ወይንም አንዳንድ ችግሮችን እንዴት እንደምትወጪ) አስበሽ ጻፊ።

አሁን ትንሽ ጊዜ በመውሰድ እግዚአብሔር በእነዚህ በገለጽሻቸው ስፍራዎች ላይ ጥበቡን እንዲሰጥሽ ጸልዩ።

## ጥበብን መፈለግ

እግዚአብሔር ጥበብን ለማግኘት ስንጠይቀው እንደሚሰጠን አንብበናል። ይህንንም ጥበብ ለማግኘት የሰጠን ዋናው መንገድ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የሚከተለው ጥቅስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል ጻፊ።

መዝ. (19):7

መዝ. (119):98–100

መዝ. (119):130

ዘዳ. 4:5–6

መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ጥበበኛ ያደርገናል? መጽሐፍ ቅዱስ ስላለን ብቻ ጥበበኛ መሆን እንችላለንን? የትምህርት ቤት ደብተሩን ማታ ሊተኛ ሲል ትራሱ ሥር አድርጎ የሚተኛ አንድ ትንሽ ልጅ ነበር። ደብተሩን ተደግፎ በማደሩ ትምህርቱን ማጥናት የሚችል ይመስለው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ጠቢባን እንዲያደርገን ከፈለግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብና ማጥናት ያስፈልገናል። ምሳሌ 2:1–6ን አንብበሽ ጥበብን ማግኘት የምንችልበትን መንገድ ጻፊ።

መጽሐፍ ቅዱስ የጥበብ መዝገብን ይዟል። ይህንን የጥበብ መዝገብ እኛ ቆፍረን ማግኘት ይኖርብናል። ለዚህም ቃሉን በጥሞና ማንበብና ማጥናት ይኖርብናል። የቃሉም ደጆች እንዲከፈቱልን እግዚአብሔርን አዘውትረን መለመን አለብን። የተማርነውን የጥበብ መዝገብ እንዲገልጥልን ዘወትር መትጋት ይኖርብናል። ጥበብን ስንፈልግ የንጉሥ ሰሎሞንን ምሳሌ መከተል አለብን። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሰሎሞንን የተለየ ጥበብ ቢሞላውም መጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ መክብብ 1:13 ላይ ሰሎሞን «ከሰማይም በታች

የተደረገውን ሁሉ በጥበብ እፈልግና እመረምር ዘንድ ልቤን አተጋሁ» ይላል። እንግዲህ ይህ በዓለም ላይ ካሉት ጠበብት ሁሉ የመጀመሪያ ጠቢብ የተባለ ሰው ጊዜውን የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናትና የጥበብን መዝገብ በመፈለግ ኖሯል።

እኛስ ጥበብን እንዴት መፈለግ ይኖርብናል? ምሳሌ 2:4 «ጥበብን እንደ ብር ብትፈልጋት እርሷንም እንደተቀበረ ገንዘብ ብትሻት» ይላል። ይህንን ለማድረግ ጥበብ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነች መገንዘብ ያስፈልገናል። ምሳሌ 8:11 ስለ ጥበብ ምን ይላል?

---

*እመቤት ሣራ የምትባል የአምስት ዓመት ልጅ ነበረቻት። ሣራ እጅግ ተወዳጅና የእናቷን ልብ በደስታ የምትሞላ ልጅ ነበረች። አንድ ቀን እመቤት ልብስ ለማጠብ ወደ ወንዝ ወረደች። ሣራም አንዲት ዶሮ ተከትላ እየሮጠች ስትጫወት እናቷ ከነበረችበት ሥፍራ ራቅ ብላ ትሄዳለች። እመቤት ከልብስ አጠባዋ መካከል ቀና ብላ ልጇን ስትመለከት ልጇ ሣራ አለመኖሯን ታያለች። እመቤትም በድንጋጤ ልብሷና ሣሙናዋን ወንዝ እንደተወች ልጇን ለማግኘት ፍለጋ በየቦታው ትሮጥ ጀመረች። ልጇን ከየቋጥኙ ሥርና ከየዛፉ ኋላ መፈለግ ጀመረች። ልጅዋ መጫወት ደስ የሚያሰኛትን ሥፍራ ሁሉ እየመረጠች ፍለጋዋን ቀጠለች። እመቤት ልጇን ሣራን እስክታገኝ ፍለጋዋን አላቋረጠችም።*

እናትየው በእንዲህ ያለ ትጋት ልጇን የፈለገችው ለምን ይመስልሻል? ምክንያቱም ልጇ የእርሷ እጅግ የከበረች ስለሆነች ነው። ጥበብ ለእኛ ይህን ያህል የከበረች ዋጋ ያላት ብትሆን ፍለጋችን እንዲህ መሆን ይኖርበታል። ጥበብን የምትፈልጊያት እንዴት ነው? ፍለጋሽን በትጋት እያካሄድሽ ነው? ጥበብን ለማግኘት ዘወትር መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብ ቃሉን ማብላላትና ስላነበብነው መጸለይ ያስፈልገናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት በቀን ውስጥ የምትወስጂው ጊዜ ምን ያህል ነው? ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የጸሎትና የቃል ጥናት ጊዜ በቀላሉ ሊታወክ ይችላል። የእግዚአብሔር ቃል ከማንበብ የሚያግዱሽን አራት ነገሮች አስበሽ ጻፊ። ከዚያም ስለ እነዚህ እክሎች ጸልዩና ከጎን ባለው መሥመር ላይ እክሎቹን ለማስወገድ ወይንም ያለ እክል ለማጥናት የሚቻልበትን ዘዴ ቀይሰሽ ጻፊ።

| አክል | ማድረግ የሚገባኝ ነገር |
|---|---|

1. ______________________________

2. ______________________________

3. ______________________________

4. ______________________________

ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ጥበብን ስንፈልግ እግዚአብሔር ምን የገባልን ቃል አለ?

ምሳሌ 2፡5፣ 9 እና 10ን አንብበሽ እግዚአብሔር የገባልንን ቃል ጻፊ።

______________________________

______________________________

እጅግ መልካም የሆነው ቃል የሚገኘው በምሳ. 2፡9 ላይ ነው። «የዚያን ጊዜ ጽድቅንና ፍርድን፥ ቅንነትንና መልካም መንገድን ሁሉ ታስተውላለህ።» ትልቅ ይሁን ትንሽ ውሳኔን ለመወሰን ጥበብ ያስፈልገናል። ጥበብን ስንፈልግ ጊዜያችንን የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በማሰላሰል ብናሳልፍ እግዚአብሔር ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችል ጥበብን ይሰጠናል።

## የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን መሰወር

ምሳሌ 2፡1 «የእግዚአብሔርን ቃል በአንተ ዘንድ ሸሽገህ ብትይዛት» ይላል። አንቺስ ቃሉን እያነበብሽና እያሰላሰልሽ በልብሽ ትሸሽጊዋለሽ? ይህ እጅግ ጠቃሚ ነው። መዝ. 119፡11ን አንብቢ። ጌታን እንዳንበድል ከኃጢአት ለመራቅ ምን ማድረግ አለብን የሚል ይመስልሻል?

______________________________

______________________________

የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ከበደልና ከመፈተን ሊያድነን ይችላል። የሰይጣንን ውሸትና ፈተና ለማለፍ ትልቁ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትና ማወቅ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድረ በዳ ሊፈትነው የመጣውን ሰይጣን ተቋቁሞ ሊያሸንፈው የቻለው በዚህ መንገድ ነው። ሰይጣን ጌታን በፈተነበት

በእያንዳንዱ ፈተና ጌታ «ተብሎ ተጽፎአልና» በማለት ያጠናውን ቃል መልሶለታል። የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትና በልባችን መሰወር ኃጢአትን ለማሸነፍ ይረዳናል። እግዚአብሔርንም የሚያስደስት ኑሮ መኖር እንችላለን።

የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት በድንገት ሊከሰቱ በሚችሉ ችግሮቻችን ወይንም አደጋዎች ጊዜ ሊረዳን ይችላል። የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ከሰወርን በሄድንበት ቦታና ባለንበት ሁኔታ ውስጥ ጥበብና መጽናናት ይሆንልናል።

*በ1971 እ.ኤ.አ. አንዲት የአሜሪካ አገር ተወላጅ የሆነች በኢትዮጵያ ውስጥ የምታገለግል ሚስዮናዊ በሽፍቶች ትጠለፋለች። ለ26 ቀናት ያህል በሽፍቶቹ ቁጥጥር ውስጥ ነበረች። የምትቀይረው ልብስ እንኳን አልያዘችም ነበር። የምትበላውም ምግብ እጅግ አነስተኛ ነበር። የሽፍቶቹን ቋንቋ ባለመቻሏ አሳብዋን መግለጽ አቅቷት ነበር። ይህች ሴት በዚያን ወቅት በፍርሃት ተሞልታ ነበር። ፍርሃቷ ስለ ራሷ ብቻ ሳይሆን በሆዷ ስለተረገዘው የመጀመሪያ ልጇ ነበር። ትልቁ ምኞቷ መጽሐፍ ቅዱስ አግኝታ በቃሉ መጽናናት ነበር። ነገር ግን አስቀድማ መጽሐፍ ቅዱስዋን አጥንታ በልቧ የሰወረችውን የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል መጽናናት ቻለች። ይህች ሴት መጽሐፍ ቅዱስዋን ማጥናትና ማሰላሰል የዘወትር ልምምዱ ነበር።*

*ይህም የእግዚአብሔር ቃል የጠለፋዋትን ሰዎች በፍቅርና በርኅራኄ እንድታነጋግራቸው ጥበብን ሰጣት። እንዲሁም ቃሉ እግዚአብሔርን ታምና ተስፋዋን በእርሱ እንድታደርግ ረዳት። በመጨረሻም ያለ አንዳች ጉዳት ተለቀቀች።*

አንቺስ የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናት ልምምድ አለሽ ወይ? አንዱን መልስ ክበቢ

አለኝ የለኝም

በዚህ መጽሐፍ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አጥንተሻልን?

አዎ አይ አላጠናሁም

ይህ ካልሆነ ከዛሬ ጀምሮ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ማጥናት ጀምሪ። ማጥናት የምትፈልጊውን ጥቅስ በወረቀት ላይ በመጻፍ በልብሽ እስክትይዢው ድረስ በተደጋጋሚ አጥኚው።

## የጥበብ ንግግር ተናገሪ

በምሳሌ 31 ላይ ያለችው ልባም ሴት «አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች» ይላል። እኛስ እንዴት በጥበብ ልንነጋገር እንችላለን? በውስጣችን በጥበብ ከተሞላን ወደ ውጭ የሚወጣውም ይኸው ጥበብ ነው። የበቆሎ ዘር ብትዘሩ ምን የሚበቅል ይመስላችኋል? እርግጥ ነው የሚበቅለው የዘራነው የበቆሎ ተክል ነው እንጂ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም። እንዲሁም ደግሞ ጥበብን በልባችን ብንዘራ ንግግራችንና ምግባራችንም በጥበብ የተሞላ ይሆናል።

ማቴዎስ 12:34-35 አንብበሽ አንደበታችንን ለመናገር የሚያነሣሣው ምን እንደሆነ ጻፊ።

---

አፍዋን በጥበብ እንደምትከፍተው ልባም ሴት መሆን ትፈልጋላችሁን? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በማጥናት ጊዜያችሁን ብታሳልፉ ልባችሁ በጥበብ ተሞልቶ አፋችሁ በጥበብ ይከፈታል።

### የእኔ ምላሽ

- ይህንን ክፍል ስታጠኚ በሕይወትሽ ልታስተካክዪው በሚገባሽ ነገር መንፈስ ቅዱስ አስተምሮሻልን?
- የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በማጥናት ተግተሽ ጥበብን ፈልገሻልን?
- ንግግርሽ በጥበብ እንዲሞላ ራስሽን በመልካም ነገር ሞልተሻልን?
- ጥበብን በይበልጥ አጠናክረሽ እንድትፈልጊያትና እንደ ልባሟ ሴት በጥበብ የተሞላሽ እንድትሆኚ ጸልዪ።

## ምዕራፍ 7

# ሌሎችን በጥበብ ታስተምራለች

**መዝሙር 77(78)፡4፥ 6–7ን በልብሽ አጥኚ**

*«የእግዚአብሔርን ምስጋናና ኃይሉን፥ ያደረገውንም ተአምራት ተናገሩ . . . የሚመጣ ትውልድ የሚወለዱም ልጆች ያውቁ ዘንድ፤ ተነሥተው ለልጆቻቸው ይነግራሉ፥ ተስፋቸውን በእግዚአብሔር እንዲያደርጉ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ እንዳይረሱ፥ ትእዛዙንም እንዲጠብቁ»።*

## የልባም ሴት ትምህርት

*እቴነሽ ስትሞት 76 ዓመቷ ነበር። በልቅሶው ቀን ሰዎች ድንኳኑን ሞልተውት ነበር። ብዙዎቹ ሴቶች ከአርሷ ቤተ ክርስቲያን የመጡ ነበሩ። ሁሉም ለእቴነሽ ያላቸውን ፍቅር ሲናገሩ ለእያንዳንዳቸው ጥሩ ምሳሌ እንደነበረች ለመረዳት አያዳግትም። አንዳንዶቹ እቴነሽ እንዴት ትጸልይላቸው እንደነበር፤ እንዳጽናናቻቸው፤ አብራ እንዳለቀሰች፤ የተሻሉ ሚስቶችና እናቶች እንዲሆኑ እንዳበረታታቻቸው፤ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ኅብረት እንዲኖራቸው እንደነገረቻቸው፤ እንደመከረቻቸው፤ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሚስቶች ይሆኑ ዘንድ እንዳበረታታቻቸው፤ እንዲያውም አንዳንዴ ሲሳሳቱ እንደምታርማቸው እያነሡ ይተርኩ ነበር። እቴነሽ እነርሱን እንደምትወዳቸውና የተሻሉ ሴቶች ይሆኑ ዘንድ እንደረዳቻቸው በደንብ አውቀዋል። ምንም እንኳ እቴነሽ ባትወልዳቸውም መንፈሳዊ እናታቸው ነበረች።*

ምሳሌ 31፡26 እንደሚነግረን ልባም ሴት ሌሎች እንዴት መኖርና ራሳቸውን መምራት እንዳለባቸው ታስተምራለች። ጥቅሱ እንዲህ ይላል። «አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፥ የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ»።

ይህች ልባም ሴት ሌሎችን እንዴት መኖር እንዳለባቸው በርኅራኄ የምታስተምር ከሆነ ብዙ ነገር ታስተምራለች ማለት ነው። ምክንያቱም ርኅራኄ ሁሉንም የሕይወት ዘርፍ ይነካልና። ስለ ርኅራኄ ስታስቢ ምን ዓይነት ባሕርይ ይታወስሻል? (ለምሳሌ፡- ለጋስ መሆን፥ ትዕግሥተኛ መሆን፥ ወዘተ...)

____________________________________________________

____________________________________________________

ስለ እውነተኛ ርኅራኄ እንድናውቅና ርኅራኄ እንድናሳይ የሚረዳን አንድ መጽሐፍ አለ። እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜም ርኅራኄን የምናሳይ ሴቶች እንሆን ዘንድ በእያንዳንዱ አጋጣሚ ምሪትን ይሰጠናል።

በምሳሌ 31 ላይ የተጠቀሰችው ልባም ሴት እግዚአብሔርን የምታመልክ ሴት ስለነበረችና ስታስተምር የእግዚአብሔርን የጥበብ ቃል ስለምትጠቀም ሌሎች ሰዎችን ስለ ርኅራኄ የምታስተምረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ነው።

## ልጆቻችንን ማስተማር

ይህች ሴት የምታስተምረው ማንን ነበር? እናት ስለነበረች (ቁ.28) ልጆቿን በርኅራኄ እንዴት መኖር እንደሚችሉ ታስተምራቸው ነበር። የእናት ትልቁ ኃላፊነት ልጆቿ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲኖሩ ማስተማር ነው።

ዘዳ. 6:6–7ን አንብቢ። ልጆቻችንን ምን ማስተማር አለብን? (ዘዳ. 5:1–22ን እና 6:1–5 አንብበሽ መልስ ስጪ።)

---

መቼ እናስተምራቸው? (ቁ.7)

---

ኤፌ. 6:4ን አንብቢ፤ ልጆቻችን እንዲከተሉ የምናስተምራቸው የማንን መንገድ ነው?

ብዙ ወላጆች ልጆቻቸውን ስለ እግዚአብሔር የማስተማር ኃላፊነት እንዳለባቸው ዘንግተዋል። አንዳንዱ ልጆቻቸውን ስለ እግዚአብሔር ማስተማር ያለባት ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንደሆነች ያስባሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ክርስቲያናዊ ትምህርት በመጀመሪያ ደረጃ ማስተማር ያለባቸው ወላጆች ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን ዘወትር ስለ እግዚአብሔርና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር አለባቸው።

*ከብዙ ዓመታት በፊት በእንግሊዝ አገር ትኖር የነበረች ሱዛና ዌስሊ የተባለችው ሴት ትዳር የያዘችው በ19 ዓመቷ ነበር። ከዚያም በቀጣዮቹ 21 ዓመታት ውስጥ 19 ልጆችን ወልዳ ነበር። ትጉ ሠራተኛ በመሆኗ ወንጌላዊ ለነበረው ባሏ የሚያስፈልገውን በማሟላት፥ በቤት ውስጥ*

ሁሉንም በማስተካከልና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም ትሳተፍ ነበር። ከሁሉም ልጆቿ የሚያስታውሱት በየቀኑ ስለ እግዚአብሔር የምታስተምራቸውን ትምህርት ነበር። ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በቃልና በሥራ ትነግራቸው ነበር። በሥራ በምትወጠርበት የቀን ክፍለ ጊዜ ሳይቀር በየመሃሉ ስለ ጌታ ትናገር ነበር። ከእነርሱ ጋር አብራ በመጸለይ የጸሎትን ጥቅም አሳየቻቸው። ከጌታ ጋር በጸሎት እንዴት እንደምታሳልፍ እንዲያዩ ትፈቅድላቸው ነበር። ከልጅነታቸው ጀምሮ ጥቅስ በልባቸው እንዲያጠኑ ትረዳቸው ነበር። በጎረቤትና በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኙ ችግረኞችን ስትረዳ ይዛቸው ትሄድ ነበር። በየቀኑ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እያስታወሰቻቸው ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረት ታበረታታቸው ነበር። ልጆቿ ሲያድጉ ድንቅ የወንጌል አገልጋዮች ሆኑ። ሰባኪ የነበረው አንደኛው ልጇ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎችን በወንጌል ማረከ። ሌላኛው ደግሞ እስከ አሁን ድረስ በዓለም ዙሪያ የሚዘመሩ መዝሙሮችን ደርሷል።

ሱዛና ዌስሊ ልጆቿን ለማስተማር የነበረባትን ኃላፊነት ተገንዝባ ነበር። እያንዳንዱን አጋጣሚ በመጠቀም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለልጆቿ በመናገር እግዚአብሔር በዓለም ዙሪያ እንዴት እየሠራ እንዳለ አሳየቻቸው። በየቀኑ እየጸለየች እግዚአብሔርን በመፍራት ላይ የተመሠረተ ሕይወት እንዲኖሩ አስተማረቻቸው። በመጨረሻም ልጆቿ ሲያድጉ የእግዚአብሔር ሰዎች ሆኑ።

መጽሐፍ ቅዱስ ከእናቶቻቸው ስለ እግዚአብሔር የተማሩ ልጆች እንዳሉ ይነግረናል። ለምሳሌ ብንወስድ ጢሞቴዎስ በክርስትና የመጀመሪያ ዘመናት የነበረ ታማኝ የወንጌል ሰባኪ ነበር። ግሪክ፥ እስያ፥ መቄዶንያ ተጉዟል፤ በቆሮንቶስ የነበሩትን አማኞች፥ የተሰሎንቄን ቤተ ክርስቲያን፥ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን፥ በፊልጵስዩስና በሌሎች ብዙ አገሮች የነበሩ አማኞችን በማስተማር አበረታቷል። ጢሞቴዎስ መጀመሪያ ወንጌል የሰማው ከማን ነው? 2ኛ ጢሞ. 1፡5ን አንብቢ። ለጢሞቴዎስ በመጀመሪያ ስለ ጌታ የነገሩት እነማን ነበሩ።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን ሴቶች የማያምን ባል ያገባሉ። ነገር ግን ያለ ባላቸው ርዳታ ልጆቻቸው ወንጌልን በመረዳት የክርስቶስ ተከታይ ይሆኑ ዘንድ ሊያስተምሯቸው ይችላሉ። የሐዋ. 16፡1ን አንብቢ። ይህ ጥቅስ ስለ ጢሞቴዎስ አባት ምን ይላል?

ምንም እንኳ የጢሞቴዎስ አባት ግሪካዊ ቢሆንና ክርስቶስን ባይከተልም እናቱ ግን እምነቷን ለልጇ ማስተላለፍ ችላለች። ባልሽ ዓለማዊ ነውን?

ለልጇ ለጢሞቴዎስ እንዳደረገችው ልጆችሽን ስለ ጌታ ኢየሱስ ማስተማር እንዳለብሽ በማስታወስ እግዚአብሔር እንዲያስችልሽ ጸልዪ። ዓለማዊ ባል ያላት ጓደኛ አለችሽ? ልጆቿን ስለ እግዚአብሔር እንድታስተምር በምን መልኩ ልትረጂያት ትችያለሽ? ቀጥለሽ አንዳንድ አሳቦችን ጻፊ።

---

## በልጆቻችን ውስጥ ዘር መዝራት

ልጆቻችንን ስለ እግዚአብሔር ማስተማር ዘርን ከመዝራት ጋር ሊነጻጸር ይችላል። ዘሮች ትንሽ ከመሆናቸው የተነሣ መሬት ላይ ሲበተኑ መዘራታቸው እስከማይታወቅ ድረስ አይታዩም። ነገር ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ዘሩ ማደግ ይጀምራል። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ተክሉ ሲያቆጠቁጥ ይታያል። በዚህም የማይታይ የነበረው ዘር አድጎ ፍሬን የሚያፈራ ትልቅና ጠንካራ ተክል ይሆናል።

ልጆችን ዘወትር ስለ እግዚአብሔር ስታስተምሪ ትንሽ የእምነት ዘርን እንደ መዝራት ነው። ምንም እንኳ ዘሮቹ ትንንሽ ቢሆኑም አንድ ቀን በልጅሽ ሕይወት ዘላቂ እምነትን ያፈራሉ። (በልጅነትሽ እናትሽ ወይም ሌላ ክርስቲያን ሴት በአንቺ ላይ የዘራችው ዘሮች ምን ምን ነበሩ?)

---

በቤትሽ ልጆች ካሉ በየቀኑ ስለ እግዚአብሔር ለማስተማር ቢያንስ ቢያንስ አንድ አጋጣሚ መጠቀም አለብሽ። ልጆች ከሌሉሽ የጓደኛሽን ወይም የጎረቤትሽን ልጆች ስለ እግዚአብሔር ማስተማር ትችያለሽ። አንዳንድ አሳቦች ቀጥለው ቀርበውልሻል፡—

- ለልጆችሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ንገሪያቸው።
- ስለሚያስቸግራቸው ነገር አብረሽ ቁጭ ብለሽ ጸልዩላቸው።

- እግዚአብሔር በፍጥረት የገለጠውን ውበት ለምሳሌ አበቦችንና ጀንበር ስትጠልቅ ያለውን ውበት እንዲያስተውሉ እርጂያቸው።
- ጥቅስ በልባቸው እንዲያጠኑ እርጂያቸው።
- ከቤተ ክርስቲያን አባላት መሃል የታመመ ሰው ቢኖር ለመጠየቅ ስትሄጂ ውሰጂያቸው።
- ከጓደኞቻቸው ጋር ሳይስማሙ ሲቀሩ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ንገሪያቸው (ለምሳሌ:- አፍቃሪ፥ ይቅር ባይና ትዕግሥተኛ፥ ወዘተ... መሆን አለባቸው)።
- የምስጋና መዝሙር አብረሽ በመዘመር እግዚአብሔርን አመስግኚ።
- አንድ ጥሩ ነገር ሲሆን መልካም ነገር ሁሉ የሚከናወነው ከእግዚአብሔር እንደሆነ አስታውሺያቸው። አብረሻቸው ለማመስገን ጊዜ ይኑርሽ።

እናት ከሆንሽ ልጆችሽን ስለ እግዚአብሔር እንዴት ማስተማር እንደምትችዪ አንዳንድ መንገዶችን ጻፊ። ልጆች ከሌሉሽ ደግሞ በጎረቤት የሚገኙ ልጆችን ወይም የዘመድ ልጆችን እንዴት ስለ እግዚአብሔር ማስተማር እንደምትችዪ መንገዶችን በዝርዝር ጻፊ።

________________________________________

________________________________________

## ሌሎች ሴቶችን ማስተማር

ከልጆቻችን በተጨማሪ ልናስተምራቸው የሚገባን ብዙ ሰዎች አሉ። ቲቶ. 2:3–5ን አንብቢ። በዚህ ጥቅስ መሠረት ሴቶች ማንን ነው ማስተማር ያለባቸው?

________________________________________

ምንድን ነው ማስተማር ያለባቸው?

ስለ እግዚአብሔር እና ክርስቲያናዊ ሕይወትን እንዴት መኖር እንደሚቻል ለማስተማር ጊዜ መውሰድ ጠቃሚ ነው። ጢሞቴዎስን እናቱና አያቱ ከልጅነቱ ጀምሮ ስለ ጌታ እንዳስተማሩት እንብበናል። ጢሞቴዎስ ባደገ ጊዜ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ተገናኘ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከእርሱ ይማር ዘንድ በአገልግሎቱ እንዲረዳው ጠየቀው

(የሐዋ. 16:3)። አብረው ባሳለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ብዙ ነገር አስተማረው። ጳውሎስ ከመሞቱ በፊት ለጢሞቴዎስ ደብዳቤ ጽፎለት ነበር። 2ኛ ጢሞ. 2፡2ን አንብቢ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ምን ማድረግ አለብህ ነው ያለው?

---

ይህንን ጥቅስ በጥልቀት ስናየው የእግዚአብሔር ቃል ወደ ብዙ ሰዎች ሲተላለፍ እናስተውላለን። በመጀመሪያ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን አስተማረ፤ ጢሞቴዎስ ደግሞ ሌሎችን፤ እንደገና ሌሎች ደግሞ ሌሎችን ያስተምራሉ።

ይህ ለምን የሚጠቅም ይመስልሻል?

---

## መንፈሳዊ እናትነት

ዛሬ ብዙ ሴቶች በሌላ ሴት የመወደድና ርዳታ የማግኘት መሻት አላቸው። መንፈሳዊ እናት የምትሆናቸውን የአንድን ሴት ፍቅርና ተቀባይነትን ይፈልጋሉ። ከእነርሱ ጠና ያለችና ስጋታቸውን ለማስወገድ በሚያደርጉት ነገር የምታስተካክላቸውን ሴት ይፈልጋሉ። የምታበረታታቸው፥ የምታጽናናቸውና በክርስትና ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምትረዳቸውን ሴት ይሻሉ።

ሌላ ሴትን በዚህ መልኩ መርዳት «መንፈሳዊ እናትነት» ይባላል። መንፈሳዊ እናትነት አንድ ክርስቲያን እኅት ሌላ ወጣት ሴትን በጥንቃቄ ልታበረታታትና በሕይወቷ ለእግዚአብሔር ክብር እንድትኖር ልታግዝ የምትችልበት ኅብረት ነው።

መንፈሳዊ እናትነት ለሌሎች የእግዚአብሔርን ርኅራኄ በማሳየትና እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩ መርዳት ነው።

ከላይ በተመለከትነው ታሪክ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በክርስትና እምነት ደቀ መዝሙር ሊያደርገው እንደወደደ አይተናል። ጳውሎስና ጢሞቴዎስ አብረው ጊዜ ሲያሳልፉ ኅብረታቸው ጠንክሮ ነበር። 1ኛ ጢሞ. 1፡2ን እና 2ኛ ጢሞ. 1፡2ን አንብቢ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ማን ብሎ ነው የሚጠራው?

በጳውሎስና በጢሞቴዎስ መካከል የነበረው ኅብረት እጅግ የጠለቀና ፍቅርን የተላበሰ ስለ ነበር ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መንፈሳዊ አባት ሆነ። እግዚአብሔር ከሌሎች ሴቶች ጋር እንዲኖረን የሚፈልገው ኅብረት የዚህ ዓይነቱን ነው። በምዕራፉ መጀመሪያ ያነበብነው የኢቴነሽ ታሪክ የመንፈሳዊ እናትነት ጥሩ ምሳሌ ነው። ኢቴነሽ አንድ ተራ ሴት ነበረች። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አልገባችም። ሥልጠናም አልወሰደችም። እጅግ ደልቃቃና ባለ ትልቅ ቤትም አልነበረችም። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስን ስለ ወደደችው ለእርሱ ኖረች። በአካባቢዋ ላሉት የእግዚአብሔርን ርኅራኄ በማሳየት ክርስቶስን መሰለች። ለሌሎች ሴቶች ከነበራት ፍቅርና አገልግሎት የተነሣ በሕይወታቸው ለውጥን አመጣች።

አንድ ሴት በሕይወቷ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ኑሮ እንድትኖር ለማስቻል፤ እምነት እንዲኖራትና ደስተኛ እንድትሆን፥ በማበረታታትና በመርዳት፥ በመምከርና በመምራት አንዳንዴም ስትሳሳት በማረም ሌላዋ እኅት ትልቅ ሥራ ልትሠራ ትችላለች። የመንፈሳዊ እናትነት ግቡ ይኸው ነው።

በቤተ ክርስቲያን ዙሪያችንን በማየት፥ በማበረታታት፤ በመርዳትና በማጽናናት ሌሎችን ማገዝ የምንችልበት መንገድ ማሰብ ይኖርብናል። ከዚህ በፊት ከሌላ ሴት ማበረታታትና እርዳታ ተቀብለሽ ታውቂያለሽ? በሌሎች እህቶች ርኅራኄ ብርታት ያገኙ ሴቶች በምሳሌነት ቀጥለው ቀርበዋል፦

- ባሌ ሌላ ሴት ወድዶ ትቶኝ ሄደ። አንድ ሴት ከቤተ ክርስቲያን መጥታ አቀፈችኝና ከእኔ ጋ እያለቀሰች ጸለየች። እግዚአብሔር እንደማይተወኝና እንደማይጥለኝ አረጋገጠችልኝ።

- ታምሜ ሳለ የቤተ ክርስቲያን ሴቶች በየቀኑ ወደ ቤቴ ምግብ ይዘው በመምጣት ቤቴን ያጸዱ ነበር። ልጆቼንም በትምህርታቸው ይረዱአቸው ነበር።

- በቤተ ክርስቲያናችን የነበረች አንድ ጠና ያለች ሴት ዓለማዊ ስለ ነበረው ባሌ እንደምትጸልይለት ነገረችኝ። በዚህም ባሌን ይቅር ብዬ መውደድ እንደሚገባኝና እንዳፈቅረው እንድችል ረዳችኝ።

- ስለ ራሴ መጥፎ ነገሮችን ሳስብ የቤተ ክርስቲያኔ ሴት ወደ ቤቴ በመምጣት በእኔ ውስጥ ስላየቻቸው መልካም ባሕርያት ነገረችኝ። በእምነቴ እንድበረታ ረዳችኝ።

እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑና ለእርሱ ክብር እንዲኖሩ ልናግዛቸው እንችላለን። ሌሎች ሴቶችን በማበረታታት ፍቅርን በጎረቤታችንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልንገልጽ የምንችልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። ሌሎችን ለመርዳት ዕድሉን ለማግኘት በየሳምንቱ መትጋት ያሻናል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሴቶችን ለማበረታታት ምን ማድረግ ትችያለሽ?

በቤተ ክርስቲያናችን ለሚገኙ ሴቶች ፍቅር ከማሳየት በተጨማሪ ለወጣት ሴቶች መንፈሳዊ እናት እንሆናቸው ዘንድ ወደ እኛ እንዲያመጣቸው እግዚአብሔርን ልንጠይቅ ይገባናል። ጊዜያችንን ከወጣት ሴቶች ጋር በማሳለፍ እግዚአብሔር በቲቶ 2:3-5 ና 2ኛ ጢ.ሞ. 2:2 የተናገረውን እንታዘዛለን። በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን የእነ ኤልሳቤጥን ምሳሌ እንከተላለን ማለት ነው። ሌላ ሴትን ልናስተምር፥ ምክር ልንሰጣትና በእምነቷ እንድታድግ ልንረዳት እንችላለን።

*ሐና ራሷን ለእግዚአብሔር የሰጠች የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል ናት። ሰሞኑን በተካፈለችው የሴቶች ስብሰባ ስለ መንፈሳዊ እናትነት ተምራለች። ሰባኪው ሴቶች ወጣት እኅቶችን በመንፈሳዊ እናትነት እንዲያሳድጉ ያበረታታ ነበር። ፍቅርና ርዳታ የነገሠበት ኅብረት ከሌላ ሴት ጋር እንዲኖራቸው ወደ ትክክለኛው እኅት እንዲመራቸው እግዚአብሔርን እንዲጠይቁ ያብራራ ነበር። ሐና ስለ እነዚህ ስትሰማ ደስ ብሏት ነበር። ነገር ግን ፈርታም ነበር። «እኔ ሌላ ሰው ልረዳ እችላለሁ? እኔ ጠንካራ ክርስቲያን አይደለሁም። በሕይወቴ ከኃጢአት ጋር እታገላለሁ። ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የማላውቃቸው ነገሮች አሉ። ለሌላ ሴት እንዴት መንፈሳዊ እናት እሆናለሁ?» ብላ አሰበች።*

ብዙ ሴቶች እንደ ሐና ያስባሉ። ምናልባት አንቺም ይህንን ምዕራፍ ስታነቢ እንዲሁ ተሰምቶሽ ይሆናል። ሌላ ሴትን ለመውደድና ለመርዳት ፍጹም ክርስቲያን መሆን እንደማያስፈልግሽ ማስታወስ ጠቃሚ ነው። መንፈሳዊ እናት ለመሆንም ሁሉን ነገር ማወቅና የሠለጠንሽ መምህር መሆን አያሻሽም። በቀላሉ ፍቅርንና ማበረታታትን ለሌላ ሰው ማበርከት ትችያለሽ። አዳምጪያት፥ ተንከባከቢያት፥ እርዷያት፥ ጸልዩላት። ስታዝን አጽናኚያት፥ ደስ ሲላት አብረሻት ተደሰቺ። እግዚአብሔርን የሚያስደስት ኑሮን መኖር እንድትችል አብረሻት መጽሐፍ ቅዱስ አንብቢ። ይህን ሁሉ ስታደርጊ

ብቻሽን አይደለሽም። እግዚአብሔር በአንቺ ውስጥ አልፎ ይሠራል፤ በመንገድሽም ሁሉ ይመራሻል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ እናት ልትሆኛቸው የምትችያቸው ሴቶች አሉን? እግዚአብሔር አሳብሽን እንዲመራው ጸልዩና ቀጥለሽ አንዳንድ ስሞችን ጻፊ፡-

________________________________________________

________________________________________________

## የእኔ ምላሽ

ልጆቻችንንና ሌሎች ሴቶችን ማስተማርና ማበረታታት የክርስትና ሕይወት አንደኛው ክፍል ነው። ልባም ሴት ዘወትር የርኅራኄ ሕግ ትምህርት በምላስዋ ላይ ነው– ማለትም ሌሎችን በቅን መንፈስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመሥርታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታስተምራለች። ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ሌሎችን ማበረታታትም ሆነ ማስተማር አንችልም። ለልጆችሽና ለሌሎች ሴቶች መንፈሳዊ እናት መሆን እንድትችዪ እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጊዜ ወስደሽ ጸልዪ።

## ምዕራፍ 8

# ባሏን እንደሚገባ ትንከባከባለች

ፊልጵ. 2፡3-4ን በልብሽ አጥኚ

«. . . ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ»።

## የምትስማሚ ረዳት መሆን

የሒሩት ባል በሚቀጥለው ቀን ስብሰባ ነበረው። ሒሩት ስለ ስብሰባው እንደተጨነቀ ስለተረዳች የምትችለውን ያህል ሊታረጋጋው ፈለገች። ግሩም እራት ይበላ ዘንድ የዶሮ ወጥ አዘጋጀች። ምንም እንኳን ልብሶቹ በጣም ባይቆሽሹም አውጥታ አጠበቻቸው። ሲደርቁ በካውያ ተኩሳ በሥርዓት ሰቀለቻቸው። በሚቀጥለው ጧት ባሏ ወደ ሥራ ከመሄዱ በፊት ጥሩ ቁርስ እንዲበላ ምግብ ለማዘጋጀት በሌሊት ተነሣች። ቁርሱን በልቶ ከተሰናበታቸው በኋላ ለ20 ደቂቃ እግዚአብሔር በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እንዲረዳው ጸለየችለት።

በምሳሌ 31 የተጠቀሰችው ልባም ሴት ለባሏ ጥሩ ሚስት ናት። ግሩም አበረታችና ታማኝ ጓደኛ ስለሆነች ባሏ እንዲከበር የምትችለውን ሁሉ ታደርጋለች።

ሴቶች በጋብቻው ዓለም ትልቅ ሚና አላቸው። ባለትዳር ከሆንሽ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚናገረውን በማወቅ እግዚአብሔር እንድትሆኚ የሚፈልገውን ዓይነት ሚስት እንድትሆኚ ቃሉን ማጥናት ጥሩ ነው። ገና ካላገባሽ ወይም መበለት ከሆንሽ አንቺም ስለ ጋብቻ ማወቅ ይጠቅምሻል። አንድ ቀን ታገቢ ይሆናል። ወይም ደግሞ ባለትዳር ሴትን ታማክሪ ይሆናል። በተጨማሪ ይህን ምዕራፍ ስታጠኑ የምታቀርቢያቸው አሳቦች ባለትዳር የሆኑ ሌሎች ሴቶችን ይረዳ ይሆናል።

ዘፍ. 2፡18ን አንብቢ። እግዚአብሔር ስለሚፈጥራት ሴት ምን አለ?

ሴቶች በተለይ የተፈጠርነው ለባሎቻችን ረዳት እንድንሆን ነው። ሌላ ሰው ሊረዳቸው ከሚችለው በላይ የቅርብ ጓደኛ በመሆን ጎዶሎአቸውን ለመሙላትና ሙላትን እንሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር

አዘጋጀን። ማቲው ሔንሪ የተባለው ሰው በባልና ሚስት መካከል ያለውን ኅብረት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡—

«ሴቷ የተሠራችው በእርሱ ላይ ራስ ትሆን ዘንድ ከራሱ አልነበረም፥ በእርሱ ትረገጥ ዘንድ ከእግሩም አይደለም። ነገር ግን ከአዳም ጋር እኩል ትሆን ዘንድ ከጎኑ ነበር የተሠራችው። ምክንያቱም በክንዱ ሥር እንድትጠለልና ትወደድ ዘንድ ደግሞ ከልቡ አጠገብ ነበር የተፈጠረችው»።

እግዚአብሔር ከባሎቻችን ጋር እንዲኖረን የሚፈልገው ኅብረት ይህ ዓይነቱን ነው። ይኸውም በፍቅርና በእንክብካቤ የተቆራኘ ኅብረት፤ ሁለታችንም አባላት የሆንንበት ኅብረት ነው። እግዚአብሔር ወንድንም ሴትንም በአምሳሉ ፈጠራቸው (ዘፍ. 1፡27)። በዋጋችንም ሆነ ከምንሰጠው ጥቅም አኳያ ሁለታችንንም እኩል አድርጎ ሠራን (ገላ. 3፡28ን ተመልከቺ)። ነገር ግን ለእኛ ለሴቶች በጋብቻ ውስጥ ለባሎቻችን «ረዳት» የመሆንን ልዩ ሚና ሰጠን።

ለባሎቻችን የምንስማማ ረዳቶች መሆን እንችል ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን ልናውቅ ያስፈልጋል። ባልሽ አስቸጋሪ ሥራ ካለው ባለበት አንዳንድ የሥራ ኃላፊነት ልታግዢው ትችያለሽ። ባልሽ ስለ አንድ ጉዳይ የሚጨነቅ ከሆነ በመርዳት፥ በማስተዳደርና ምግብ በማዘጋጀትም ጭምር ባልሽን ልትረጂው ትችያለሽ።

ባለትዳር ከሆንሽ ባልሽ የሚያስፈልገውን ነገር በማሰብ ጥቂት ደቂቃዎችን አሳልፊ። ምን ምን ያስፈልገዋል? መርዳት እንደሚገባሽ እየረዳሽው ነውን?

## ለባሎቻችን መልካምን እንጂ ክፉን አለማድረግ

ምሳሌ 31፡12 ባላችንን መርዳት የምንችልበትን አንድ ጠቃሚ መንገድ ይነግረናል።

ጥቅሱን አንብቢና ምን እንደሚል ቀጥለሽ ጻፊ።

-

---

ምሳሌ 31 ላይ ያለችውን ልባም ሴት ያገባ ባል ሚስቱ ታማኝና አፍቃሪ ረዳት መሆኗን ያውቃል። የሚጎዳኝን ወይም ደግሞ ችግር የሚያደርስብኝን ነገር ታደርጋለች ብሎ አይጨነቅም። ምሳሌ 31፡11 እንደሚለው «የባልዋ ልብ ይታመንባታል»።

- በምክርሽ የሚገባውን እንዲያደርግ ተጽዕኖ እያሳደርሽበት ነውን?

- በጥሩ ምሳሌነትሽ መልካምን ያደርግ ዘንድ ተጽዕኖ እያሳደርሽበት ነውን?

- በዝንባሌሽና በፍቅርሽ ለመልካም ነገር ተጽዕኖ እያሳደርሽበት ነውን?

ባልሽን ለመልካም ወይም ለመጥፎ ሥራ ተጽዕኖ ያሳደርሽበትን አጋጣሚ ቀጥለሽ ጻፊ (ያላገባሽ ከሆንሽ በዘመድሽ ወይም ደግሞ በአንዱ ጓደኛሽ ያሳደርሽውን ተጽዕኖ መግለጽ ትችያለሽ)።

ዓለማዊ ባሎችን ያገቡ ብዙ ክርስቲያን ሴቶች አሉ። ለእነዚህ ዓይነቶቹ ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ በባሎቻቸው ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይናገራል። 1ኛ ጴጥ. 3፡1–2ን አንብቢና በዚህ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሴቶች እግዚአብሔር የሚለውን ጻፊ።

ዓለማዊ ባል ካለሽ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ተጽዕኖ ልታሳድሪ የምትችይው በቃልሽ (ማለትም በስብከት) ሳይሆን በመልካም ባሕርይሽ ነው። እርሱን በማክበር በንጽሕና ከኖርሽ ዝንባሌሽና ባሕርይሽ በባልሽ ላይ መልካም ተጽዕኖን ስለሚያሳድሩ በእግዚአብሔር ጸጋ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል።

## ለባሎቻችን ክብርን መስጠት

ሌላው ባሎቻችንን ልንረዳ የምንችልበት መንገድ ሚስቶች ባሎቻቸውን «ማክበር» አለባቸው የሚለውን ኤፌ. 5፡33 ተግባራዊ በማድረግ ነው። ሌላን ሰው ማክበር ማለት ምን ማለት ነው? ሌሎችን ማክበር ማለት የተለየ ክበሬታን ማሳየት፥ ጎደሎአቸውን፥ አሳባቸውን፥ ፍላጎታቸውንና እግዚአብሔር ልዩ አድርጎ እንደፈጠራቸው መረዳት ማለት ነው። ሌሎችን ማክበር ማለት በእነርሱ ማሾፍ፥ መኮነንና ሁልጊዜ ከሥራቸው ስሕተታቸውን እየነቀሱ ማውጣት ማለት አይደለም።

እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልግብንን ዓይነት ሚስቶች እንሆን ዘንድ ለባሎቻችን በሚኖረን ዝንባሌና በባሕርያችን ከበሬታን ማሳየት ይኖርብናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለባሎቻቸው ከበሬታን ያልሰጡ የአንዳንድ ሴቶች ምሳሌዎችን ይሰጠናል። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበሽ እነዚህ ሴቶች የሠሩትን ከበሬታ ያልታየበትን ነገር ጻፊ።

ዘፍ. 27፡1–19

2ኛ ሳሙ. 6፡12–23 ______________________________

*ዓለምፀሐይ ባሏን እንደማታከብር ጎረቤት ሁሉ ያውቃል። ማታ ማታ ስትጮኽበትና ስትተቸው ይሰማሉ። ከሌሎች ሴቶች ጋር ጎረቤት ቡና ስትጠጣ እያሾፈችበት የእርሱን ደካማ ጎን ትናገራለች። ከቃሏም የተነሣ ጎረቤቱ ሁሉ ባሏን ይንቁት ጀመር።*

ባልሽን ታከብሪያለሽን? የሚከተሉትን ዝርዝር በማንበብ ማሻሻል የሚገባሽ ላይ ምልክት አድርጊ

| | ይህን አደርጋለሁ | ማሻሻል ያስፈልገኛል |
|---|---|---|
| – በሌሎች ፊት ስለ ባሌ መልካም ነገርን እናገራለሁ | | |
| – ሁልጊዜ ባሌን አልተችም | | |
| – አሳቡን እሰማዋለሁ | | |
| – አላሾፍበትም | | |
| – በሌሎች ፊት አልገሥጸውም | | |
| – በቁጣና በማይገባ ቃል አልገሥጸውም | | |
| – አበረታታዋለሁ እንጂ አላሳፍረውም | | |

ባልሽ ኃጢአት የሆነ ነገርን ቢፈጽምስ? አሁንም ማክበር አለብሽ ማለት ነው? አዎ ይገባናል። ምንም እንኳ ባሎቻችን ስሕተት ቢሠሩና ክብርን አይሰጥም ብለን የምናስበውን ምግባር ቢፈጽሙም ከበሬታን የተሞላ ምላሽን ልንሰጥ ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህን እንድናደርግ አዝዟልና። ባልሽ ኃጢአትን ቢያደርግ እንኳ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ «ልትገሥጪው» ይገባል። (ልክ ሌሎች ኃጢአት የሚሠሩ ክርስቲያኖችን በምንገሥጽበት መንገድ) መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ሰዎችን እንዴት መገሠጽ እንዳለብን መመሪያዎችን ሰጥቶናል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበሽ መልሱን ጻፊ፥ ሌሎችን ለመገሠጽ የሚያነሣሣን ምን መሆን አለበት? (1ኛ ቆሮ. 4:14)

---

ሌሎችን ከመገሠጻችን በፊት ራሳችንን እንዴት ነው መመርመር ያለብን? (ማቴ. 7:2–5)

እንዴት ነው ሌሎችን መገሠጽ ያለብን? (ገላ. 6:1 እና የሐዋ. 20:31)

---

ባልሽን ስትገሥጪውም ይሁን ስታርሚው እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ትከተያለሽ ወይስ የምትገሥጪው በቁጣና ራስ ወዳድነትን በተላበሰ ጎጂ ምክንያቶች ተነሣሥተሽ ነው? ስሕተት ወይም ኃጢአት መስሎ በባልሽ ላይ የታየሽን ነገር ለማንም ከማማከርሽ በፊት ፍቅር፥ ጨዋነትና ከበሬታ ባለው መንገድ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተሰጡትን መመሪያዎች በመከተል መገሠጽ እንድትችዪ እግዚአብሔር ይረዳሽ ዘንድ የጸሎት ጊዜ ይኑርሽ።

ብዙ ጊዜ ባልሽን ለማረም ወይም ለመቀየር የምትሞክሪው እንዴት ነው? ምናልባት ለየት ባለ መልኩ ልታደርጊያቸው የሚገቡሽ ነገሮች ይኖሩ ይሆን? (ያላገባሽ ከሆንሽ) ጓደኞችሽን ወይም ዘመዶችሽን ለመቀየር የምትሞክሪው እንዴት ነው? ምናልባት ለየት ባለ መልኩ ልታደርጊያቸው የሚገቡሽ ነገሮች ይኖሩ ይሆን?

---

ባሎቻችን እኛ እንድናከብራቸው ይፈልጋሉ። ትልቅ ስፍራ እንደምንሰጣቸውና የእርሱን በጎ ነገር ማየት እንደምንሻ ማየት ይኖርባቸዋል። ለባሎቻችን ከበሬታን ስናሳይ ስንገሥጻቸው እንኳን እንከብካቤ በተሞላው ምክራችን ምላሽ በመስጠት በየጊዜው እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ዓይነት ሰዎች ወደ መሆን ያድጋሉ። የእግዚአብሔር ዓላማ ይህ ነው። የእግዚአብሔርን ዓላማ መቀበል ደግሞ ሁሌም እጅጉን ምርጥ ነው።

## እንከን ያለባቸውን ጋብቻዎች ማስተናገድ

*የብርሃኑና የገነት ትዳር አስቸጋሪ ነው። ምንም እንኳ ሁለቱም ክርስቲያኖች ቢሆኑም ግንኙነታቸው ግን ሁሌም እንደሻከረ ነው። ገነት አንዳንዴ ቀኑን ሙሉ የምታገለግል የብርሃኑ ባርያ የሆነች ይመስላታል። የምትለውን አይሰማትም። እንዲያውም አንዳንዴ ሲናደድ ይመታታል። ገነትም ብርሃኑን በጣም ጠላችው። ትተቸውም ጀመር። እንዲያውም አንዳንዴ ስለ እርሱ ነውር ትናገራለች። በልቧም ከዚህ ትዳር እንዴት እንደምትወጣ ዘወትር ትመኛለች።*

ትዳር አንዳንድ ጊዜ በክርስቲያኖችም ቤት ቢሆን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ብዙ ጊዜ ሰይጣን ባልና ሚስትን ያጠቃል። ምክንያቱም ትዳራቸውን ካፈረሰ ልጆች ይጎዳሉ። ቀስ በቀስም ኅብረተሰቡ ይተራመሳል። እግዚአብሔር ለባሎች እንዲህ ብሏል። «...ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ...»። ባሎች ከራሳቸው አስበልጠው ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ታዝዘዋል። የራሳቸውን ፍላጎት ከማሰባቸው በፊት የሚስቶቻቸውን ማስቀደም አለባቸው። ሚስቶች ደግሞ ምሪትን በተመለከተ ለባሎቻቸው እንዲገዙ እግዚአብሔር ተናግሯል። ግን ባል እንደሚገባው ባይወድስ? ልናከብረው ይገባናልን? አሁንም ልንገዛለት ይገባናል? *መጀመሪያ መረዳት ያለብን «መገዛት» ማለት አንዱ ከአንዱ ያንሳል ወይም ደግሞ* ሚስቶች ከባሎቻቸው ያነሰ ጥቅም ይሰጣሉ ማለት አይደለም። ባል ሚስቱን እንደፈለገው የማንገላታት መብት አለው ማለትም አይደለም።

መገዛት ማለት ምን ማለት ነው? መገዛት ማለት ባሎቻችን በቤተሰብ ውስጥ የመምራት ሚና እንዲኖራቸው መፍቀድ ማለት ነው። በፈቃዳችን ባሎቻችን በቤተሰባችን ውስጥ ኃላፊነትንና መሪነትን እንዲወስዱ ልንሰጥ ይገባናል። ክብርን በመስጠት መልካም ልናደርግላቸው ይገባል እንጂ ክፉ ልናደርግ አይገባንም። ምንም

እንኳን ባሎቻችን እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ የሰጣቸውን ኃላፊነት ባይወጡም ይህንን ሁሉ ልናደርግ ይገባናል።

## በአስቸጋሪ ትዳር ውስጥ በእግዚአብሔር ጸጋ መኖር

እግዚአብሔር አስቸጋሪ ትዳሮችን ያያል። ብዙ ሴቶችን የሚገጥሟቸውን ችግሮች ያውቃል። በዚህ ዓይነት ትዳር ውስጥ ያሉትን ኃጢአትና ችግሮች ጠራርጎ መጣል ይሻል። ነገር ግን ሴቶች እንዳይበቀሉ ይናገራል። ኃጢአትን የሚሠሩትን የሚቀጣና የሚያስተካክል እግዚአብሔር ነው። ይህንንም እንደ ፈቃዱ በራሱ ጊዜ ያደርጋል። የእኛ ሚና ቃሉን መታዘዝ ነው። ባሎቻችን ይለወጡ ዘንድ ማስገደድ አንችልም ወይም ደግሞ በቁጣችን የምንፈልጋቸውን ዓይነት ባሎች አይሆኑልንም። ያዕ. 1፡19–20ን አንብቢ። ጥቅሱ ቁጣ ምን አይሠራም ነው የሚሉት?

የባሎቻችንን ባሕርይ መቆጣጠር አንችልም። ነገር ግን ለእነርሱ ባሕርይ የእኛን ምላሽ መቆጣጠር እንችላለን። በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል በአስቸጋሪ ትዳር ውስጥ ልባም ሴቶች መሆን እንችላለን።

የእግዚአብሔር ቃል ባሎቻችንንና ሌሎችን ጭምር እንዴት ማስተናገድ እንዳለብን ይናገራል። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበሽ ሌሎችን ስለማስተናገድ የሚናገሩትን ጻፊ።

ፊልጵ. 2፡3–4

________________________________________

ሮሜ 12፡10 __________________________________

ቆላ. 3፡13

1ኛ ተሰ. 5፡11 ________________________________

ገላ. 6፡2 ___

እንዳስተዋልሽው የእግዚአብሔር ቃል እነዚህን የምናደርገው ሰዎች ለእኛ መልካም ሲሆኑ ብቻ ነው ብሎ አይናገርም። ጥቅሱ «አንድ ሰው በመጀመሪያ ይቅር ካለሽ ይቅር በዪው» ብሎ አይናገርም። የፈለገ ነገር ቢበድሉን እኛ ግን እንደሚገባ ልናስተናግዳቸው ይገባናል። ዮሐ. 13፡34ን አንብበሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ።

በዚህ ጥቅስ መሠረት እርስ በርሳችን እንዴት ልንዋደድ ይገባናል?

ጥቅሱ ክርስቶስ እንደወደደን ይላል። ክርስቶስ ፍቅሩን ያሳየን እንዴት ነው?

ክርስቶስ ፍቅርን ከማሳየቱ በፊት መልካም እስክንሆን ድረስ ይጠብቅ ነበር? (ሮሜ 5:8ን ተመልከቺ)

በዚህ ሳምንት በልብሽ የምታጠኚው ጥቅስ ፊልጵ. 2:3-4ን ነው። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ክፍል አንብቢና ቀጥለሽ ጻፊው። (ቁ. 5)

አሁን ደግሞ ቀጥለው ያሉትን ሁለት ጥቅሶች አንብቢ (ቁ. 6-8)። እነዚህ ጥቅሶች ክርስቶስ ስለ እኛ ስለነበረው አመለካከት ምን ይላሉ?

ከባልሽ ጋር በሚኖርሽ ኅብረት የዚህ ዓይነት አመለካከት እንዴት ሊኖርሽ ይችላል? (ያላገባሽ ከሆንሽ አብረሻቸው ለምትኖሪያቸው ሰዎች ይህ አመለካከት እንዴት ሊኖርሽ ይችላል?)

በአስቸጋሪ ትዳር ውስጥ መኖር ቀላል አይደለም። ሕመም፥ ጥላቻ፥ ምሬትና ኀዘን ሊኖርበት ይችላል። ምናልባት አንዳንድ ሌሊቶችን የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በእንባ ታሳልፊ ይሆናል። ትዳርሽ ችግር ካለበት ዘወትር ችግሮችሽን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ልታቀርቢ ይገባል። ልትጸልዪባቸው የሚገቡሽ ነገሮች ቀጥለው ቀርበዋል።

- በራስሽ ብርታት ባልሽን እንደሚገባ ለመውደድ አለመቻልሽን እመኚ።

- እግዚአብሔር ለአንቺ ያለውን ጥልቅ ፍቅር እንድታውቂ እንዲረዳሽ ጌታን ጠይቂው።

- እግዚአብሔር አንቺን በወደደበት ፍቅር ባልሽን መውደድ እንድትችዪ እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጠይቂው።

- ክርስቶስ ይቅር እንዳለሽ አንቺም ባልሽን ይቅር ማለት እንድትችዪ እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጠይቂው።

- እግዚአብሔር እንደሚረዳሽ በመታመን ባልሽ ላደረሰብሽ በደል ይቅርታን ልታደርጊ መምረጥሽን ንገሪው። ይቅርታ ለማድረግ እስኪሰማሽ አትጠብቂ። ነገር ግን በፈቃደኝነት አሁኑኑ ይቅር በዪው።

- በአሳብሽ፥ በቃልሽና በሥራሽ በትጋት የተሞላሽ እንድትሆኚ እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጠይቂው።

- በሌሎች ፊት ስለ ባልሽ መጥፎ ነገርን መናገር እንድትተዪ እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጠይቂው።

- ሁኔታዎችን ማለፍ የምትችይበትን ጥበብ እንዲሰጥሽ እግዚአብሔርን ጠይቂው።

- ለባልሽ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ምላሽ መስጠት ትችዪ ዘንድ ብርታትና ፍቅርን እንዲሰጥሽ እግዚአብሔርን ጠይቂው።

- እግዚአብሔር በባልሽ ልብ ውስጥ እንዲሠራ ጠይቂው።

- እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ስለሆነ አመስግኚው። ስለሚወድሽ አመስግኚው። በመከራ ጊዜ መጠጊያሽና ኃይልሽ ይሆን ዘንድ ተስፋን ስለሰጠሽ አመስግኚው [መዝ. 45(46):1፥ መዝ. 58(59):16-17]።

የሚከተለውን ምንባብ በእርጋታና በጥንቃቄ አንብቢ።

«መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ። እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ። እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ» (ኤፌ. 4:31-5:2)።

አሁን ምንባቡን ስታነቢ የተጠቀሱትን ነገሮች ለማድረግ እግዚአብሔር እንዲረዳሽና በዚህም እርሱ የሚፈልጋትን ዓይነት ሴት

መሆን እንድትችዪ ጸልዪ። እነዚህን ነገሮች እንድታደርጊ የጠየቀሽ እግዚአብሔር ስለሆነ በየቀኑ መፈጸም ትችዪ ዘንድ ኃይሉንና ፍቅሩን ይሰጥሻል።

## ከሌሎች እርዳታን መፈለግ

እግዚአብሔር ባልሽን እንድታከብሪ ስለተናገረሽ ብቻ በትዳርሽ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለማንም መናገር የለብሽም። ለአንድ ሁለት ታማኝ ጓደኞችሽ ግን ስለ ሁኔታው ልታሜውቂያቸው ትችያለሽ። እነርሱም ሊጸልዩልሽ የሚችሉ፥ ጥበብና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክርን የሚሰጡሽ እንጂ ሐሜተኞች መሆን የለባቸውም።

ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም እርዳታ ልታገኚ ትችያለሽ። ከሽማግሌዎች ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ ያዢ። በትዳር ጉዳይ ምክር እንደምትፈልጊ ግለጪላቸው። ስለምታልፊበት አስቸጋሪ ጉዳይ በመንገር እርዳታ እንዲደረግልሽ ጠይቂያቸው።

እግዚአብሔር የክርስቲያን ትዳር የጋራ ፍቅርና ከበሬታ የሞላበት እንዲሆን ይሻል። እግዚአብሔር ደግሞ የተስፋ አምላክ ነው። ስለሆነም ተስፋሽን በእርሱ ላይ አድርጊ። እርሱን የሚያስከብር ትዳር እንዲሰጥሽም እግዚአብሔርን ጠይቂው።

## የእኔ ምላሽ

ምሳሌ 12፡4 እንዲህ ይላል «መልካም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት...»። አንቺ ለባልሽ ዘውድ ነሽን? ምሳሌ 14፡14 «ብልሃተኛ ሴት ቤትዋን ትሠራለች፤ ሰነፍ ሴት ግን በእጅዋ ታፈርሰዋለች» ይላል። እግዚአብሔርን የምትፈራ ሚስት በመሆን ቤትሽን ትሠሪያለሽን ወይስ በትዳርሽ ውስጥ ባለሽ ባሕርይ ቤትሽን እያፈረስሽ ነው? ይህንን ምዕራፍ ስታጠኚ ምናልባት መንፈስ ቅዱስ በሕይወትሽ አንዳንድ ለውጥን እንድታደርጊ አነሣሥቶሽ ይሆናል። ይህ ከሆነ መለወጥ የምትፈልጊያቸውን ነገሮች ቀጥለሽ ጻፊያቸው። ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት በመውደቅ በሕይወትሽ የሚፈልገውን ለውጥ ማድረግ ይችል ዘንድ ጠይቂው።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ምዕራፍ 9

# እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች

ማቴዎስ 25፡40ን በልብሽ አጥኚ

«እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት»።

## እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች

*አልማዝ ብዙ ገንዘብ የላትም። የባሏ ደመወዝ ትንሽ ከመሆኑም በላይ በትምህርት ላይ ያሉ የአራት ልጆች እናት ናት። አልማዝ ግን ባላት ነገር ለጋስ ናት። በየቀኑ ወደ ቤቷ ለምትመጣው ለማኝ ሁል ጊዜ እንጀራ ትሰጣለች። የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሲታመሙና ምግብ ለማዘጋጀት ሲሳናቸው ምግብ ይዛላቸው ትሄዳለች። ልጆቿ ለጓደኞቻቸው የሚያካፍሉትን ዳቦ ቆሎ ታዘጋጅላቸዋለች። ወደ ገበያ ስትሄድ እጆቻቸውን ዘርግተው ለእርዳታ ወደ እርሷ ለሚመጡት ሕፃናት ሳንቲም ትሰጣቸዋለች። አልማዝን የሚያውቁ ሁሉ ስለ ለጋስነትዋ ይናገራሉ።*

ምሳሌ 31፡20 ልባም ሴት «እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች»። ይላል። ድሀና ችግረኛ የሆነ ሰው የሌሉትን ነገሮች በዝርዝር ጻፊ፡-

ዝርዝርሽ ስለ ድሀው ቁሳዊና አካላዊ ጉድለት ብቻ ነውን? ሊኖሩ የሚችሉ ሌሎች ጉድለቶች ምን ምን ናቸው?

# እግዚአብሔር ለችግረኞች ያስባል

ችግረኞችን ስለ መንከባከብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበሽ እግዚአብሔር ለድሆችና ችግረኞች ያለውን አሳብ ጻፊ፡—

መዝ. 11(12)፥5 ______________________________

መዝ. 139(140)፥12 ______________________________

ኢሳ. 25፥4

አሁን ያነበብሻቸው ጥቅሶች እግዚአብሔር ለድሆችና ለችግረኞች እንደሚገደው ግልጽ ያደርጋሉ። ለእነርሱ ያለውንም ርኅራኄና ፍቅር ያሳያሉ። ድሆችና ችግረኞችን እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባን እግዚአብሔር መመሪያን ሰጥቶናል። የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ ምን ማድረግ እንደሚገባን የሚናገሩትን ቃል ጻፊ፡—

ዘሌዋ. 23፥22 ______________________________

ዘሌዋ. 25፥35

ዘዳ. 15፥7—11 __

ምሳ.14፥31 ______________________________

እግዚአብሔር ለተቸገሩ ግድ እንደሚለው የሚያስተምሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ ሳይሆኑ ምስኪኖችን መንከባከብ የጌታ ኢየሱስ አንዱ አገልግሎት ነበር። በማቴ. 25፥34—40 ጌታ ኢየሱስ ለችግረኞች ርኅራኄ ማሳየት እንደሚገባን ተናግሯል። ጥቅሶቹን አንብቢና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ።

ጻድቁ ሰው ለችግረኛው ያደረጋቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?

______________________________

______________________________

ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረው ለእርሱ ያለንን ፍቅር ለማሳየት ምን ማድረግ አለብን?

በሉቃ. 10:30-37 እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ባልንጀሮቻችን ፍቅር ማሳየት እንደሚገባን ተናግሯል። ያንን ክፍል አንብቢና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጪ።

ሳምራዊው ሰው ለመንገደኛው ካደረጋቸው ነገሮች አምስቱን ጻፊ፡-

---

---

---

ደጉ ሳምራዊ ስላደረገው ርዳታ ሊያጋጥሙት የሚችሉት ችግሮች ምን ምን ነበሩ?

ችግረኛን ለመርዳት ብታስቢ ሊገጥምሽ የሚችለው ችግር ምንድን ነው?

ሊገጥሙሽ የሚችሉት ችግሮች ለችግረኛዋ ልታደርጊላት ያሰብሽውን ከማድረግ ሊያግዱሽ ይገባቸዋልን?

---

መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን አይሁዳውያን ሳምራውያንን ይጠሏቸው ነበር። ከሳምራውያን እንሻላለን ብለው ስለሚያስቡ አይተባበሩዋቸውም ነበር። ዛሬም በኢትዮጵያ ተመሳሳይ ችግሮች ይታያሉን? ካሉ ምን ምን ናቸው?

---

---

ይህ ምሳሌ ስለ ዘረኝነት (ጎሰኝነት) ምን ያስተምረናል?

---

---

ከላይ ባጠናናቸው ጥቅሶች መሠረት ለችግረኛ ሰዎች እግዚአብሔር እጅጉን ግድ ይለዋል። ምንም እንኳን እነዚህ ችግረኞች በዘር

የማይዛመዱንና ከሌላ ጎሣ የመጡ፥ በእምነት የማይመሳሰሉንም እንኳ ቢሆኑ እንድንረዳቸው እግዚአብሔር ይፈልጋል። እንዳየነው ሁሉ ለእነርሱ የምናደርገውን የምንሠራው ለጌታ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስን ትወጂዋለሽ? እንግዲያውስ ለእርሱ ያለሽን ፍቅር በአካባቢሽ ያሉትን ችግረኞች በመርዳት ልታሳዪው ትችያለሽ።

## እጆችሽን ለችግረኞች መዘርጋት

መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ ችግረኞችን ስለምትረዳ ዶርቃ ስለ ተባለች ሴት ይነግረናል። የሐዋ. 9:36-42ን አንብበሽ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጪ። ዶርቃ ሁልጊዜ ምን ነበር የምትሠራው? (ቁ. 36)

መበለቶች ብዙ ጊዜ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያልፋሉ። አንዳንዶ ሴቶች መሥራት አይችሉም። ለዚህም ነው ባላቸው ሲሞት የገንዘብ ችግር የሚገጥማቸው። በተለይ ደግሞ ልጆች ካላቸው ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለልጆቻቸውም የሚያስፈልጋቸውን ማሟላት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ መበለቶች ከብቸኝነትና ኀዘን ጋር ይታገላሉ። ምክንያቱም ይወዳቸውና ይንከባከባቸው የነበረውን ሰው አጥተዋልና ነው።

አካላዊና ስሜታዊ ጉደሎዋቸውን በማሟላት በአካባቢዋ የነበሩትን መበለቶች በመንከባከብ ዶርቃ ፍቅሯን አሳየች። እንዴት ነበር አካላዊ ጉድለታቸውን ያሟላችው?

---

ዶርቃ ያሟላቻቸው ስሜታዊ ጎዶሎዎች ምን ምን ነበሩ?

---

ለመበለቶቹ የሚያስብላቸው፥ የሚወዳቸው፥ የሚንከባከባቸውና ጓዳቸውን የሚሞላ ሰው መኖሩን ማወቁ እንዴት የሚያበረታታና የሚያጽናና ነበር! ዶርቃ በምሳሌ 31:20 የተጠቀሰችው ሴት ምሳሌ ናት። ምክንያቱም «እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች»።

## ችግረኞችን ለምን እንረዳለን?

ችግር ላለባቸው ሰዎች የእርሱ ልጆች ቸርነትን ሲያሳዩ እግዚአብሔር ደስ እንደሚለኝ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበሽ እግዚአብሔር ድሆችን ስለሚረዱ ሰዎች የሚናገረውን ጻፊ፦

ምሳ. 14:21 ______________________________

ምሳ. 19:17 ______________________________

ምሳ. 21:13 ______________________________

ምሳ. 22:9 ______________________________

አንዳንድ ሰዎች ለድሆች ቸርነትን ካደረጉ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት እንደሚያስችላቸው አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እውነት እንዳልሆነ ያስተምራል (ኤፌ. 2:8-9ን አንብቢ)። የምንሠራው ሥራ በምንም ዓይነት መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማይ አያስገባንም። ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት የምንችለው ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ስለ ኃጢአት በከፈለው ዋጋ ብቻ ነው።

ድሆችን የምንረዳው ደግነትን ለማግኘት አይደለም። ድሆችንና ችግረኞችን የምንረዳው ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተነሣ ነው። ማስታወስ የሚገባሽ ቢኖር ሌሎችን ስንረዳ ስጦታውን የምንሰጠው በቀጥታ ለጌታ ኢየሱስ ነው። በዚህም ምን ያህል እንደምንወደውና ስላደረገልን ምስጋናን ለመግለጽ ነው።

እግዚአብሔር ሌሎችን እንድንወድና እንድንንከባከባቸው ይፈልጋል። ሌሎችን በመርዳት የእርሱ እጆች እንድንሆን ይሻል። እግዚአብሔርም ድሆችንና ችግረኞችን ስንረዳ እንደሚባርከን ቃል ገብቷል።

ሉቃ. 6:38ን ጻፊ፡- ______________________________

______________________________

______________________________

## በደስታ መስጠት

ለድሆችና ለችግረኞች እጅሽን ስትዘረጊ አመለካከትሽ ምንድን ነው? በደስታና በፈቃደኝነት ትሰጪያለሽ ወይስ በልብሽ እያጉረመረምሽ ትነጫነጫለሽ? በ2ኛ ቆሮ. 9:7 ላይ እንደተናገረን «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም»። እግዚአብሔር በፈቃደኝነትና በደስታ ያለ ጥላቻ እንድንሰጥ ይፈልጋል። ሌሎችን ስለመርዳት ደስታን የተሞላ ዝንባሌ እንዲኖረን ገንዘባችንና ንብረታችን ከየት እንደመጣ ማስታወስ ይገባናል።

ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 29፡14ን አንብቢ። ከእግዚአብሔር ለእኛ የተሰጡን ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ዘዳ. 8፡18ን አንብቢ። ለመሥራትና ገንዘብ ለማግኘት የቻልነው እንዴት ነው?

---

በአነበብናቸው ጥቅሶች መሠረት ካሉን ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠን ምንም የለም። ሠርተን ገንዘብ ማግኘት የቻልንበት ችሎታ ምንጭ እግዚአብሔር በመሆኑ ያለን ሁሉ የእርሱ ስጦታ ነው። በዓለም ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር በመሆኑ ያሉን ነገሮች በሙሉ የእኛ አለመሆናቸውን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። እግዚአብሔር እንድንንከባከባቸው አሳልፎ የሰጠንን ነገሮች እየተቆጣጠርን ነው ያለነው።

*ገነትና ጽዮን ክርስቲያኖች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ብዙ ችግረኞች በመኖራቸው ሽማግሌዎችና አባላት ገንዘብ በመስጠት ድሆችን እንዲረዱ እየጠየቁ ነበር። አንድ ቀን ገነት በመንገድ ላይ ስትሄድ አንድ እንግዳ ሰው ወደ እርሷ መጥቶ 200 ብር ሰጣት። ገነት ገንዘቡ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ብላ ስላሰበች ደስ ተሰኘች። ከፊሉን ገንዘብ በቤተ ክርስቲያን ያሉት ችግረኞች እንዲረዱበት ሰጠች። የገነት ጓደኛ ጽዮን አዲስ ሰሃን ለመግዛት በጥንቃቄ ገንዘብ እያጠራቀመች ነበር። 200 ብር አጠራቅማለች፤ ነገር ግን ድሆችን ለመርዳት ለመስጠት አልወደደችም። 200 ብሩ የእግዚአብሔር ገንዘብ አልመሰላትም፤ የራሴ ገንዘብ ነው አለች። ምክንያቱም ይህን ለማግኘት ለፍታ ነበርና።*

*ጽዮን ያሰበችው ልክ አልነበረም። ከላይ ያነበብናቸው ጥቅሶች እንደተናገሩት በምንም ዓይነት መልኩ የምናገኘው ንብረትና ገንዘብ የእግዚአብሔር ሲሆን ለእኛም በስጦታነት የሰጠን እግዚአብሔር ነው። በገንዘባችንና በንብረታችን ዙሪያ ስለሚኖረን ዝንባሌ ዘወትር ማስታወስ የሚገባን ነገር ቢኖር እኛ ያለን ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ያለንን ነገር በደስታ በዙሪያችን ካሉ ድሆችና ችግረኞች ጋር እንድንካፈለው ይፈልጋል።*

ሴትየዋ ራሷ ድሀ ከሆነችና ለሌሎች የምትሰጠው ብርም ሆነ ምግብ ከሌላትስ? ችግረኞችን እንዴት ልትረዳ ትችላለች? ምንም እንኳ ትርፍ ገንዘብ ባይኖርሽም ጊዜሽን መሥዋዕት በማድረግና ስሜታዊ ጎደሎዎቻቸውን በመሙላት ልትረጂያቸው ትችያለሽ። ልቅሶ ያለበትን

ሄደሽ መጠየቅ ትችያለሽ። ማበረታቻ ወይም ምክር ከሚያስፈልገው ሰው ጋር ሄደሽ መነጋገር ትችያለሽ። ለሌሎች ያለሽን ፍቅርና እንክብካቤ በብዙ መንገዶች ማሳየት ይቻላል።

እጅሽን ወደ ድሆችና ችግረኞች መዘርጋት ማለት ቁሳዊ ነገራቸውን ለማሟላት ርዳታን ማበርከት ብቻ ሳይሆን ስሜታዊና መንፈሳዊ ጉድለታቸውን ማሟላትም ሊሆን ይችላል።

## የእኔ ምላሽ

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ምሳ. 30:21ን አንብበናል። ይህም ልባም ሴት «እጇን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች» ይላል። እናት የምትወደውን ልጅ ለማጽናናትና ለመርዳት እጅዋን እንደምትዘረጋ አይተናል። ልባም ሴት እጅዋን የምትዘረጋው ለቤተሰቦቿ ብቻ ሳይሆን ለድሆችና ለችግረኞች ነው። በዚህም ማድረግ የምትችለውን በተግባር ታሳያለች።

በአካባቢሽ ለድሆችና ለችግረኞች ምን ማድረግ ትችያለሽ? ምንም እንኳን ያለሽ ገንዘብ ትንሽ ቢሆንም ሌሎችን መርዳት የምትችዪባቸው ብዙ መንገዶች መኖራቸውን አስታውሺ። ስለምታውቂያቸው ቁሳዊና ስሜታዊ ችግር ስላለባቸው ሰዎች አስቢ። እነርሱን መርዳት የምትችዪባቸውን መንገዶች ቀጥለሽ በዝርዝር አስቀምጪ።

---

አንዳንዴ ሌሎችን መርዳት አስቸጋሪ ነው። ሊሰለቸን ይችላል። ብዙ ርዳታ በሚፈልጉ ሰዎች ልንጨነቅም እንችላለን። ያለን ከማነሱ የተነሣ ለሌሎች ለጋስ ለመሆን እንቸገር ይሆናል። ነገር ግን እርሱን ብንጠይቀው በአካባቢያችን ያሉ ሰዎችን መርዳት የምንችልበትን ብርታት ይሰጠናል።

ፊልጵ. 4:13ን ጻፊ፦

ዘወትር «እጇን ወደ ድሀ የምትዘረጋና ወደ ችግረኛም እጅዋን የምትሰድ ሴት» እንድትሆኚና በዚህም እግዚአብሔር ጥበብ፥ ፍቅርና ብርታት እንዲሰጥሽ ጊዜ ወስደሽ በመጸለይ ጠይቀው።

ምዕራፍ 10

# እግዚአብሔርን ትፈራለች

(ፈሪሀ እግዚአብሔር አላት)

ምሳሌ 31፥30ን በቃልሽ አጥኚ።

«ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች»።

## እግዚአብሔርን መፍራት

*ከረጅም ጊዜ በፊት በቻይና የነበሩ ክርስቲያኖች በሚሰደዱበት ዘመን የምትኖር አንዲት የ12 ዓመት ወጣት ነበረች። አንድ ቀን ድብቅ ቤተ ክርስቲያን ከነበረችበት ቤት ስትወጣ በኮምዩኒስት ወታደሮች ተያዘች። በጥያቄ ሦስት ቀን ሙሉ ከቆየች በኋላ ወደ ፍርድ ቤት ቀረበች። ጠባቂዎቹ ጠየቋት። የጠየቋት ጥያቄ መልስ የሞትና የሕይወት ጉዳይ መሆኑን ታውቃለች። «ኢየሱስን ትወጂዋለሽን?» ብለው ጠባቂዎቹ ወተወቷት። በጣም ከመፍራቷ የተነሣ አልወደውም ለማለት ቃጥቷት ነበር። ነገር ግን በዚያው ቅጽበት በተሰበሰቡት መካከል በእርሷ የዕድሜ ክልል የምትገኝ ሌላ ወጣት ድምፅ ሳታሰማ በእጆቿ የመስቀል ምልክት ስትሠራ ተመለከተች። ይህችኛዋም ወጣት ቀጥ ብላ ቆመችና በድፍረት «አዎ ኢየሱስን እወደዋለሁ» ስትል መለሰች። ወታደሮቹም ወዲያውኑ ገደሏት። ይህች ወጣት ከሰዎች ይበልጥ እግዚአብሔርን በእውነት እንደምትመርጥ አረጋገጠች።*

መጽሐፈ ምሳሌ «እግዚአብሔርን መፍራት» በሚለው ሐረግ ይጀምራል፤ ይጨርሳልም። በምሳሌ ምዕራፍ 1 «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ይላል። የመጨረሻው የምሳሌ ምዕራፍም «እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርሷ ትመሰገናለች» በማለት ይዘጋል።

እግዚአብሔርን መፍራት ምን ማለት ይመስልሻል?

---

ለአንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ስሙ ሲጠራ መርበድበድና መንቀጥቀጥ ማለት ይመስላቸዋል። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ግን እንዲህ ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠት ማለት ነው።

ቅድስናውን፥ ኃይሉንና ምስጋናውን በመረዳት መታዘዝ በሚያስችለን መልኩ መገንዘብ ማለት ነው። በቀላሉ እሱ አምላክ መሆኑንና እኛ ደግሞ ፍጥረቱ መሆናችንን ማስተዋል ነው። እግዚአብሔርን እንፈራለን ስንል እንርበደበዳለን ማለት ሳይሆን በአለመታዘዛችን እንዳናሳዝነው እርሱን የምንፈራው ጨዋነት የተሞላበትን ጠንካራ ሥርዓቱን በመተላለፍ እንዳንበድለው ነው።

የሚከተሉትን ጥቅሶች ከምሳሌ መጽሐፍ አንብቢና እግዚአብሔርን ስለመፍራት የሚናገሩትን ጻፊ።

ምሳ. 14:26–27 ______________________________

______________________________

ምሳ. 15:16 ______________________________

______________________________

ምሳ. 15:33 ______________________________

ምሳ. 16:6 ______________________________

______________________________

ምሳ. 19:23 ______________________________

______________________________

የምሳሌ መጽሐፍ ሞኞች እግዚአብሔርን እንደማይፈሩ ይነግረናል። እግዚአብሔርን አለመፍራት ሞኝነት የሆነበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

______________________________

______________________________

በእስልምና እምነት እስላሞች «አምላካቸውን» ይፈራሉ። አላህን ያከብራሉ። ነገር ግን ልዩነት አለን። ከአምላካቸው ጋር የቀረበና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የላቸውም። አምላካቸውን የሚፈሩት እንደሚገባ ካልታዘዙት መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ ይከለክለናል ብለው ስለሚያምኑ ነው።

ክርስቲያን እንደመሆናችን እግዚአብሔር እንድንፈራው ይነግረናል። ይህ ፍርሀት ግን ወደ እርሱ ያስጠጋናል። እኛ ልጆቹ ነን። አባታችን

ብለን እንጠራዋለን። ከአምላካችን ጋር በፍቅር ላይ የተመሠረተ ግሩም ኅብረት አለን። የምንፈራው ጥሩ ካልሆንን መንግሥተ ሰማይ አያስገባንም ብለን ስለምናስብ አይደለም። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ኃጢአታችን ይቅር እንደተባለልንና በመንግስተ ሰማይ መያዣ ርስት እንዳለን እናውቃለን። እግዚአብሔርን የመፍራታችን መሠረቱ ለእርሱ ያለን ፍቅርና አክብሮት ነው። እግዚአብሔር እንደሚወደን እናውቃለን። እርሱ ስለወደደን እኛ በምላሹ እንወደዋለን። በጣም ስለምንወደው ነው እርሱን በመታዘዝ ልናከብረው የወደድነው። በምሳሌ 31 የተጠቀሰችው ልባም ሴት ይህንን እውነታ ታውቀዋለች። ሕይወቷም የተለወጠውና የተመራው እግዚአብሔርን በመፍራትና በመውደድ ላይ ነው።

## ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን መፍራት እንዳለብን ብቻ አይናገርም። ነገር ግን የሰውን ልጆች ከምንፈራው በላይ እግዚአብሔርን መፍራት እንዳለብን ይነግረናል። ይሄ ቀላል ይመስላል። «ከሰው ልጆች ይልቅ እግዚአብሔርን እፈራለሁ! እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። የነገሥታት ንጉሥ ነው!» ብለሽ ታስቢ ይሆናል። ግን በእውነት ሰውን ከምንፈራው ይበልጥ እግዚአብሔርን እንፈራለን?

*ቆንጂት ክርስቲያን እናት ናት። እግዚአብሔርን የመፍራትን ጥቅም በደንብ ተረድታለች። እግዚአብሔርን እንደምትፈራም ጽኑ እምነት አላት። የቆንጂት ጎረቤት ፋጡማ ትባላለች። ቆንጂትና ፋጡማ ለረጅም ጊዜ ጓደኛሞች ነበሩ። ቆንጂት ለፋጡማ ስለ ጌታ ኢየሱስ መናገር እንዳለባት ታውቃለች። ነገር ግን ምናልባት ፋጡማ ተቆጥታ ትጣላኝ ይሆናል ብላ ፈራች። ዓመታት ቢያልፉም ቆንጂት ስለ እግዚአብሔር የምታውቀውን እውነታ ስለ ፋጡማ ሲል በመስቀል ስለሞተው ጌታ ነገራት አታውቅም።*

ቆንጂት እግዚአብሔርን እንደሚገባ የምትፈራ መስሏት ነበር። እውነቱን ስናየው ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ነው የምትፈራው። የፈራችው እግዚአብሔርን ማሳዘኗንና አለመታዘዟን ሳይሆን ፍርሃቷ ምናልባት ሰዎች ተቆጥተው እንዳይተዉአት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቀን ሌሊት ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ስለፈራው ስለ ጴጥሮስ ታሪክ ይነግረናል (ማቴ. 26:31–35 እና 26:69–73ን አንብቢ)። ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን መፍራቱን ያሳየው እንዴት ነበር?

ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን ይፈሩ ስለነበሩ የአንዳንድ ሴቶች ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት። ዘጸአት 1:15–20ን አንብቢና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ።

ንጉሥ ለዕብራውያን አዋላጆች ምን ብሎ ትእዛዝ ሰጠ?

---

ለአዋላጆቹ የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር? (ቁ. 20)

ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ስለ መፍራት ይሄ ጥሩ ምሳሌያችን ነው። አዋላጆቹ ንጉሡን መፍራት ይችሉ ነበር። ንጉሡ ከኃይሉ የተነሣ ትእዛዙን በመተላለፋቸው ሊያስገድላቸው ይችል ነበር። አዋላጆቹ ግን ለሞት እንኳን ቁብ አልነበራቸውም። በምትኩ እግዚአብሔርን ፈሩ። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደሆነ በመረዳት ወንዶች ልጆችን በእግዚአብሔር ፊት መግደል ትክክል እንዳልሆነ አወቁ። ስለዚህም እግዚአብሔርን ታዘዙ። አዋላጆቹ እግዚአብሔርን ስለፈሩ እግዚአብሔር አከበራቸው፤ ባረካቸውም።

## እግዚአብሔር ሊፈትነን ይችላል

እግዚአብሔር አንዳንዴ እርሱን በእውነት መፍራት አለመፍራታችንን ለማረጋገጥ ይፈትነናል። በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ስለተፈተነው አብርሃም ታሪኩን እናስታውሳለን። እግዚአብሔር አብርሃም የሚወደው ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያ ላይ ይሠዋው ዘንድ አዘዘው። ምንም እንኳ አብርሃም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ቢያዝንም አላመነታም። ታዘዘ። ልክ አብርሃም ልጁን ሊሠዋው ሲል እግዚአብሔር አስቆመው። ዘፍ. 22:12ን አንብቢና እግዚአብሔር አብርሃምን ለፈተና ያቀረበለትን ምክንያት ጻፊ።

እግዚአብሔር አብርሃምን በፈተነበት መልኩ እኛን አይፈትነንም፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅርና ፍርሃት ይመዘን ዘንድ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ እንድናልፍ ያደርገናል።

*አበነሽ ዛሬ ከሰዓት ሥራ መግባት አትፈልግም። ምክንያቱም ሌላ አዲስ ካምፓኒ ልትቀጠር የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ አላት። ሥራ ካልገባች*

ያው የከሰዓቱ ደመወዝ ይቆረጣል። ነገር ግን ገንዘብን ማጣት አትፈልግም። ስለሆነም ለኃላፊዋ እንደታመመች ተናገረች። ታምሜአለሁ ካለች የት እንደምትሄድ፥ ምን ልትሠራ እንደምትሄድ አትጠየቅም። በዚህ ላይ ደግሞ ደመወዝዋ አይቆርጥም። ማንም ስለማያውቅ ይህንን ማድርጉ ከፋት እንደሌለበት አድርጋ አሰበች።

በዚህ አቅጣጫ ምናልባት እግዚአብሔር አበነሽን እየፈተናት ይሆናል። አበነሽ ማንም ሥራዋን ሊያውቅ የማይችልበት ደረጃ ላይ እንኳ ብትደርስ በእውነት እግዚአብሔርን መፍራትዋንና ለመታዘዝ መሻቷን ማየት ይፈልጋል። የሚያሳዝነው ግን አበነሽ ፈተናውን መውደቋ ነው። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ባለመቻሏ እግዚአብሔርን እንደማትፈራና እንደማታከብረው በሥራዋ አሳየች።

እግዚአብሔር አንቺ በእውነት እንደምትፈሪው ለማወቅ አንቺን የፈተነበት ወቅት ነበርን? ካለ ቀጥለሽ ጻፊው።

የእግዚአብሔርን ፈተና መፍራት የለብንም። ዘፍ. 20፡20 ላይ «እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ኃጢአትም እንዳትሠሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ ይሆን ዘንድ መጥቶአልና አትፍሩ አለ» ይላል። የእግዚአብሔርን ፈተና መፍራት የለብንም። ምክንያቱም ፈተናውን ብንወድቅ ጌታ አይተወንምና። እግዚአብሔር የሚፈሩትን የሚፈትነው ስለሚወደን ብርታትና ድፍረት እንዲሁም እግዚአብሔርን መፍራት በሕይወታችን እንድናገኝና ኃጢአት እንዳንሠራ ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ በፈተና ውስጥ ስናልፍ እርሱን መፍራትና እርሱ የሚለንን ዓይነት ሰዎች መሆን እንድንችል መጸለይ አለብን።

ውበትና ደም ግባት

የምሳሌ 31 የመጨረሻ ክፍል እግዚአብሔርን ስለመፍራት ብቻ ሳይሆን ስለ ውበትና ደም ግባት የሚናገረውም ነገር አለ።

ምሳሌ 31፡20ን ቀጥለሽ ጻፊ።

ብዙ ሴቶች ውበት እንዲኖራቸው ይሻሉ። ስንቶቻችን ነን አንዲት ቆንጆ ሴት አይተን እንደ እርሷ ለመሆን የተመኘን? ማለትም ወፈር ያላለች፥ ቀጫጫም ያልሆነች ውብ ፀጉርና የሚያምር ቁመና ያላት። አንዳንዶቻችን ውብ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግር ይለናል። ምናልባት ውበት ደስታ፥ ሀብትና ዝና ያስገኝልናል ብለን እናስባለን።

ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለምን በጣም ቆንጆና የምንስብ አድርጎ አልፈጠረንም ብለን ጠይቀን ይሆናል። ውበት ለሴት ልጅ ጠቃሚ ነገር ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ውበት ልናሳድደው የሚገባ ነገር እንዳልሆነ ይናገራል።

ቆንጆ መሆን መጥፎ አይደለም። ነገር ግን ውበት በራሱ ደስታን እንደማይሰጠን ማስታወሱ ጠቃሚ ነው። ምሳሌ 31:30 ውበት ሐሰት እንደሆነ ይናገራል። በምዕራፍ 2 በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አስቴር ስለተባለች ቆንጆ ሴት አንብበናል። በመጽሐፈ አስቴር 2:7 ላይ «የተዋበችና መልከ መልካም ነበረች» ይላል። ከቁንጅናዋ የተነሣ የንጉሡን ልብ አሸንፋ ንግሥት ለመሆን በቃች። አስቴር ግን ውብ ብቻ አልነበረችም። እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴትም ነበረች።

ንግሥት ከሆነች ከጥቂት ጊዜ በኋላ አይሁዳውያንን ለማጥፋት ሤራ እንደተሸረበ ሰማች። ንግሥት እንደመሆኗ ንጉሡን በማነጋገር ሕዝቡን ልታድናቸው እንደምትችል ታውቃለች። ነገር ግን ንጉሡ ካልጠራት በስተቀር ወደ እርሱ መቅረብ አትችልም ነበር። ሳይጋበዝ ወደ ንጉሡ መቅረብ የሚሻ ማንም ቢኖር የሞት ቅጣት ይደርስበት ነበር። አስቴር ወደ ንጉሡ ስትገባ በሞት ሊቀጣት እንደምትችል ብታውቅም ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ስለፈራች እንዲህ ስትል ተናገረች «ምንም እንኳ ያለ ሕግ ብሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ፥ ብጠፋም እጠፋለሁ» (አስቴ. 4:16)።

ለአስቴር ውበቷ ንግሥት ለመሆን አበቃት! የአስቴር ውበት ብቻውን የአይሁድን ሕዝብ ለማዳን ብቃት አልነበረውም። ለአስቴር ወደ ንጉሡ ቀርባ ስለ አይሁዳውያን እንድትጠይቅ ያበረታታት እግዚአብሔርን መፍራቷ ነበር። እግዚአብሔር የአስቴርን ድፍረት አከበረ፥ አይሁዳውያንንም ከሞት አተረፈ።

## የማይረግፍ ውበት

መጽሐፍ ቅዱስ ውበት «ከንቱ» እንደሆነና «አንድ ቀን እንደሚጠፋ» ይነግረናል። አካላዊ ውበት ዘላቂ አይደለም፥ ይረግፋል። አንድ ቀን ይጠፋል። ውበትን ስናሳድድ ዘመናችንን ብንፈጅ የማያዘልቅን ነገር ፍለጋ ጊዜያችንን በከንቱ እናባክናለን።

*ዴቦራ በጣም ውብ ሴት ናት። ሰው ሁሉ ቁንጅናዋን ያደንቅላታል፥ የሰዎችን አድናቆትና በእርሷ በመሳባቸው ትደሰታለች። ውበቷን ለመጠበቅ ብዙ ገንዘብ በማውጣት ውድ ልብሶችና ጌጣጌጦችን ትገዛለች። ለጸጉሯም ትጨነቃለች! ትኩረቷ ሁሉ በራሷ ዙሪያ ስለሆነ*

ሌሎችን ለመርዳት ጊዜና ገንዘብ አልነበራትም፤ በዘመኗ ማለቂያ ላይ ውበቷ ሟሸሸ፤ ጓደኛም አልነበራትም። በብቸኝነትና በኀዘን ተቆራምዳ ሞተች።

ስለ ውጫዊ ውበትሽ በማሰብ ረጅም ጊዜ ታሳልፊያለሽን? የበለጠ ቆንጆ ለመሆን ትጥሪያለሽን? ምናልባት ትኩረትሽ በተሳሳተው የውበት አካል ላይ ነው ማለት ነው።

የማይረግፍ ወይም የማያረጅ ውበት አለ። እንዲያውም የዚህ ዓይነት ውበት በዕድሜ እየገፋን ስንሄድ የበለጠ የሚጎላ ነው። እግዚአብሔር እንዲኖረን የሚፈልገው ውበት ይሄ ነው። ይህ ውበት ምንድን ነው? 1ኛ ጴጥ. 3፡3-4ን አንብበሽ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሺ።

ውበትሽ መምጣት የሌለበት ከየት ነው? ______________________

______________________

በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ ውበት የትኛው ነው?

______________________

«የዋህና ዝግተኛ መንፈስ» ሲል ምን ማለቱ ይመስልሻል?

______________________

ከዚህ ምንባብ እንደምንረዳው የማይረግፍ ውበት ሊኖረን ይችላል ማለት ነው። ዞማ ፀጉር ይሸብታል፥ ይረግፋልም። ወርቅም ቢሆን ወይ ይጠፋል፥ አልያም ይሰረቃል። ገላችንም ቢሆን ይሟሽሻል፥ ይዋልላል። ነገር ግን የማይረግፍ ውበት የሚኖረው የአካላችን ክፍል አለ። ያ አካል ምንድን ነው? በድጋሚ 1ኛ ጴጥ. 3፡3-4ን አንብበሽ ይህ የማይጠፋ ውበት ከየት መምጣት እንዳለበት ጻፊ። ውበታችን መምጣት ያለበት ከውስጣችን ነው ወይስ ከውጪያችን?

______________________

በ1ኛ ሳሙ. 16፡7 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ቁመናን እንደሚያይ እግዚአብሔር ግን «ልብን እንደሚመረምር» ይናገራል። እግዚአብሔር ግድ የሚለው የመንፈሳችን ጉዳይ ነው— ውስጣዊ ማንነታችን። 2ኛ ቆሮ. 4፡16ን አንብቢ። ስለ ውስጣዊ አካልና ስለ ውጫዊው አካል ልዩነት ምን ይላል?

______________________

በልባችን ዕለት ዕለት እንታደሳለን። በውጫዊ ማንነታችን ላይ ምንም ዓይነት ነገር ቢፈጸም ልባችን ግን ሁሌም አዲስ፥ ንጹሕና የማይረግፍ ሊሆን ይችላል። ዓለም እንደምታየው ውጫዊ ውበት ባይኖረንም ውብ ልብ ግን ሊኖረን ይችላል።

*የአራት ዓመቷ ሕፃን ደስታ አንድ እሑድ ማለዳ ወደ እናቷ መጣች። ቆንጆ ልብሷን ለብሳለች፥ አዲሱን ጫማዋን ተጫምታለች፤ ፊቷን ታጥባ ፀጉሯ ደግሞ በፀጉር ማስያዥያ ሸብ ተደርጓል። ፈገግ ብላ እናቷን እንዲህ ስትል ጠየቀች «እማማ ቆንጆ ነኝ?» እናትየውም ደንግጣ «ቆንጆ ነሽ፥ ደስታ» አለቻት። እናትየዋም ቀጥላ ጥያቄ ጠየቀቻት «ልብሽ ምን ይመስላል? መልካም፥ የዋህና ዝግተኛ ልብ አለሽን? እግዚአብሔር እኮ ደስ የሚሰኘው በመልካም ልብ እንጂ በቆንጆ ልብስ አይደለም»።*

ስንት ጊዜ ነው እንደ ደስታ የምንሆነው? ምን ያህል ጊዜ ነው ከውስጣዊ ውበታችን ይልቅ ለውጫዊ ማንነታችን የምናስበው? ለውበት ሊኖርሽ የሚገባው ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖርሽ እንዲያስችልሽና ለማይረግፍ ውበት ትኩረት እንዲኖርሽ እግዚአብሔር ይረዳሽ ዘንድ ጊዜ ወስደሽ ጸልዩ።

## የእኔ ምላሽ

አሁን የዚህ መጽሐፍ መገባደጃ ላይ ደርሳችኋል። በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ እንደተገለጸው ልባም ሴት መሆን ጊዜ የሚፈጅና መሠራትን የሚጠይቅ ሂደት መሆኑን ተረድተናል። የከበረ ድንጋይ ተጠርቦና ተስተካክሎ ጌጠኛ ዕንቁ እንደሚወጣው ሁሉ እኛም ቀስ በቀስ እየተቀረጽን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ልባም ሴቶች እንሆናለን። ልባምና ምስጉን ሴት ለመሆን በነገር ሁሉ ፍጹም መሆን የለብንም። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተልና እግዚአብሔርን እንደሚገባ ለመፍራት ጥረትን በማድረግ ላይ ካለን በእርግጥ ልባም ሴቶች ነን።

የዚህ ፈለግ መሠረት ምንድን ነው? ቁልፉስ? መጽሐፈ ምሳሌ ምዕ. 31 ለዚህ መልስን ይሰጠናል። «እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት እርሷ ትመሰገናለች»። ቁልፉ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። እግዚአብሔርን በእውነት ብንወድና ብንፈራው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያጠናናቸው የልባም ሴት ባሕርያት ሕይወታችንን ያደምቃሉ፤ ኑሮአችን በእግዚአብሔር ጸጋ ይታጀባል፤ ለአመኔታ የምንበቃ ሰዎች እንሆናለን፥ ትጉሕ ሠራተኞች እንሆናለን፥ ስለ ነገ የማንሰጋ፥ በጥበብ የምንናገር፥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ሌሎችን የምናስተምር መልካም ሚስትና ለጋሾች እንሆናለን። እግዚአብሔርን ብንፈራ አጽንኦታችንን ውጫዊ

ገጽታችንና ችሎታችን ላይ ሳይሆን ነገር ግን በማይደበዝዘው ውስጣዊ ውበታችን ላይ ይሆናል። ልባም ሴት ሕይወቷን እግዚአብሔርን በመፍራት ላይ ትመሠርታለች። እድገታችን ቅጽበታዊ ባይሆንም መለወጣችን አይቀርም። ምሳሌ 4:18 «የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፥ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ያበራል» ይላል። ውስጣዊ ውበታችን በመጀመሪያ በገሀድ ላይታይ ይችላል። ነገር ግን እንደ ንጋት ብርሃን ሙሉ ቀን እስኪሆን እየጨመረ ይበራል። እኛም እግዚአብሔርን እንደምትፈራው ልባም ሴት የማይደበዝዘው ውስጣዊ ውበታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደመቀ ይሄዳል።

እግዚአብሔርን ከልብሽ የምትፈሪ ይመስልሻል? ለምን?

---

---

---

አንቺ በእድገትና ለውጥ ፈለግ (ጎዳና) ላይ ነሽን? ምላሽሽ አዎን ከሆነ በእግዚአብሔር ዓይኖች የከበርሽ ልባም ሴት ነሽ። ለጥቂት ጊዜ በጸሎት ልባም ሴት ለመሆን ራስሽን ለእግዚአብሔር ደግሞ አስረክቢ። እግዚአብሔር እርሱን መፍራትንና እንደ ፀሐይ የሚያበራውን ውስጣዊ ውበትን እንዲሰጥሽ ጸልዪ።